ሰኔ_____ ቀን 2015 ዓ.ም

የዉሳኔ ሀሳብ ቁጥር ______11_____/2015 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሥነ-ስርአት እና የማስረጃ ሕግ ረቂቅ አዋጅ ቁጥር **4/2013**

በተመለከተ ከሕግና ፍትህ ጉዳዩች ቋሚ ኮሚቴ የቀረበ ሪፖርት እና የውሳኔ ሀሳብ

# **I.** ሪፖርት

## **1.** መግቢያ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ አምስተኛው ዙር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በስድስተኛ ዓመት የስራ ዘመኑ መስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም ባካሄደው አንደኛ መደበኛ ስብሰባ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሥነ-ስርዓት እና የማስረጃ ሕግ ረቂቅ አዋጅ ላይ የመጀመሪያ ንባብ ካካሄደ በኋላ ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 4/2013 ሆኖ ለዝርዝር እይታ ለሕግ፣ ፍትህ እና ዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መመራቱ ይታወሳል።

በዚሁ መሰረት ቋሚ ኮሚቴው በም/ቤቱ የአሰራር እና የአባላት ስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 አንቀጽ 163 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) እና 172 (2) (እንደተሻሻለው) መሰረት የሚከተለውን ሪፖርት እና የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።

## **2.** በረቂቅ አዋጁ ምርመራ ሂደት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

2.1. ቋሚ ኮሚቴው በረቂቅ አዋጁ ላይ አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረገ ቆይቶ ሕዳር 21 ቀን 2013 ዓ.ም ዝርዝር ውይይት አድርጐ ለአስረጂዎች መቅረብ የሚገባቸውን ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ለይቷል፤

2.2. በመቀጠልም ቋሚ ኮሚቴው ህዳር 25 ቀን 2013 ዓ.ም ከአስረጂዎች ጋር መድረክ በማዘጋጀት ከጠቅላይ ዓቃቤ ሕግና ከተለያዩ ተቋማት የተጋበዙ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር ውይይት አድርጓል። በውይይቱ አስረጂ የስራ ኃላፊዎች ስለረቂቅ አዋጁ አስፈላጊነት ገለጻ ያደረጉ ሲሆን ከቋሚ ኮሚቴው፣ ከምክር ቤት አባላት እና ከም/ቤቱ የሕግ ጥናት ኬዝቲም ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች እና አስተያየቶች በቂ ምላሽ እና ማብራሪያ ሰጥተዋል። (የዉይይቱ ቃለ-ጉባዔ አባሪ ተደርጓል።)

2.3. በረቂቅ አዋጁ ላይ ባለድርሻ አካላት እና የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ እና በማወያየት ግብአት ማሰባሰብ አስፈላጊነቱ በመታመኑ ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ማስታወቂያ በማስነገር በአካል መገኘት የሚችሉ በአካል እንዲገኙ እና በአካል መገኘት የማይችሉ በኢሜል፣ በፋክስ፣ በነጻ ስልክ መስመር ጥያቄና አስተያየት እንዲያቀርቡ ጥሪ በማስተላለፉ ቋሚ ኮሚቴው ታህሳስ 12 ቀን 2013 ዓ.ም ይፋዊ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ከጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና ከተለያዩ ተቋማት ከተጋበዙ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር ውይይት አድርገዋል። በውይይቱም አስረጂ የስራ ኃላፊዎች ስለ ረቂቅ አዋጁ አስፈላጊነት ገለጻ ያደረጉ ሲሆን ከተሳታፊዎቹ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች እና አስተያየቶች በቂ ምላሽ እና ማብራሪያ ሰጥተዋል። (የውይይቱ ቃለ-ጉባኤ አባሪ ተደርጓል።)

2.4. በመቀጠልም ቋሚ ኮሚቴው ጥር 14 ቀን 2013 ዓ.ም በድጋሚ ሰፊ የባለድርሻ አካላት የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ረቂቅ አዋጁ ላይ ውይይት ተደርጓል። በውይይቱም ረቂቅ አዋጁን ለማዳበር የሚያስችሉ ግብአቶች ማግኘት ተችሏል። (የውይይቱ ቃለ-ጉባኤ ተያይዞ ቀርቧል።)

2.5. ታህሳስ 2014 ዓ.ም አሁን ያለው ቋሚ ኮሚቴ አሁን ካለው ም/ቤት የተመራለት ባለመሆኑ ምክንያት ነባሩ ቋሚ ኮሚቴ አዋጁን ሲመረምር ያከናወናቸው አበይት ተግባራትን በመለየት ስራው ያለበት ደረጃ በማወቅ ቀጣይ መከናወን የሚኖርባቸውን ስራዎች ለይቷል።

2.6. ጥር 2014 ዓ.ም ረቂቅ ህጉ አሁን ላለው ም/ቤት ባለመቅረቡ እና በዚህ ም/ቤት ባለመመራቱ ምክንያት አሁን ላለው ም/ቤት አባላት በረቂቅ ህጉ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።

2.7. ቋሚ ከሚቴው በሰኔ 03 ቀን 2014 ዓ.ም በድጋሚ ከፍትሕ ሚንስቴር ከፍተኛ አመራሮች ጋር የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ረቂቅ አዋጁ ላይ ውይይት ተደርጓል። በውይይቱም ረቂቅ አዋጁን ለማዳበር የሚያስችሉ ግብአቶች ማግኘት ተችሏል። (የውይይቱ ቃለ-ጉባኤ ተያይዞ ቀርቧል።)

2.8. ግንቦት 2014 ዓ.ም ለነባሩ ቋሚ ኮሚቴ የተገኘውን ግብአት መነሻ በማድረግ ተጨማሪ አስተያየቶችና ጥያቄዎች በመለየት እና በማደራጀት ከፍትህ አካላት ጋር ለሁለት ቀን የቆየ ሰፊ ውይይት አካሂዷል። የረቂቅ አዋጁም ለማዳበር እንዲረዳ ተጨማሪ ግብአት ማግኘት ተችሏል።

2.9. መጋቢት 2014 ዓ.ም ረቂቅ አዋጁ ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ ተጨማሪ የግንዛቤ ስልጠና በማስፈለጉ ከፍትህ ሚኒስቴር ሀላፊዎችና ባለሙያዎች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲሁም አርቃቂ ኮሚቴዎች በተገኙበት አራት ቀን የፈጀ አውደ ጥናት ተካሂዷል።

2.10. በመቀጠልም ቋሚ ኮሚቴው ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአስራ ሶስቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ እንዲሁም ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሴቶች ኮከስ ስራ አስፈፃሚዎች በተጨማሪም ለተለያዩ ተቋማት ረቂቅ ህጉ እንዲደርሳቸው በማድረግ ከተቋማቸው ባህሪ አንጻር በህጻናት፣በሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ዙሪያ ያላቸውን አስተያየት አስቀድመው በጽሁፍ እንዲልኩ በማድረግ በታሕሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም ፍትህ ሚኒስቴር በአስረጂነት በተገኘበት ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች፣ ከፌዴራል ፖሊስ፣ ከሲቪክ ማህበራት፣ከሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ከፌዴራል ህግ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት፣ከሴቶች የህግ ባለሙያ ማህበር፣ከሴቶችና ህጻናት ሚኒስቴር፣ከአካል ጉዳተኞች ማህበር ፣ከጠበቆች ማህበር እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ረቂቅ አዋጁ ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጓል። በውይይቱም ረቂቅ አዋጁን ለማዳበር የሚያስችሉ ግብአቶች ማግኘት ተችሏል። (የውይይቱ ቃለ-ጉባኤ ተያይዞ ቀርቧል።)

2.11. ቋሚ ከሚቴው በ 2015 ዓ.ም ከጠበቆች ማሕበር ከፍተኛ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ተሰባስበው ረቅቅ ህጉ ላይ ምርመራ በማድረግና ሙያዊ አስተያየቶችን በማዘጋጀት በጽሁፍ ያቀረቡ ሲሆን በጽሁፍ ያዘጋጁትን

ሙያው አስተያየቶች ላይ መድረክ ተዘጋጅቶ ውይይት ተደርጓል። የተገኙ ግብአቶችና አስተያየቶችን ለፍትህ ሚኒስቴር በመላክ ፍትህ ሚኒስቴር በማሻሻያ ሀሳቡ እንዲካተት አድርጓል።(የውይይቱ ቃለ ጉባኤ ተያይዟል)

2.12. ቋሚ ኮሚቴው ከግንቦት 1 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ሰኔ 20 ቀን 2015 ዓ.ም ቋሚ ኮሚቴ ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ በማደራጀት ለምክር ቤቱ ልኳል።

2.13. በመጨረሻም ቋሚ ኮሚቴው ለ 3 ተከታታይ አመታት ግለሰቦችና ተቋማት የሰጡትን ግብአቶች፣ፍትህ ሚኒስቴር በተለያዩ ጊዜያት የላካቸውን ማሻሻያዎች እና በተለያዩ የውይይት መርሀግብሮች የተገኙትን ግብአቶች መርምሮ ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ የሚያዘጋጅ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ የሚመሩት ከቋሚ ኮሚቴው እና ከምክር ቤቱ ጽ/ቤት ከህግ የስራ ክፍል የተውጣጣ ቡድን በማዋቀር ሙሉ ግንቦትና ሰኔ 2015 ዓ.ም ተጠቅሞ ይህንን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ አደራጅቶ ለቋሚ ኮሚቴ በማቅረብ በማፀደቅ ለምክር ቤቱ ልኳል።

## 3. <u>በአስረጂነት የተገኙ የስራ ኃላፊዎች</u>

1. ክቡር ዶ/ር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ — የኢፊዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር
2. ክቡር አቶ አለምባንተ አግደው — የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዲኤታ
3. አቶ በላይሁን ይርጋ — በጠ/አ/ሕግ የሕግ ጥናት ማርቀቅ እና ማጠናቀቅ ዳይሬክተር ጀነራል
4. ወ/ሮ ትዕግስት መሀቤ — በጠ/አ/ሕግ የወንጀል ስነስርአት እና ማስረጃ ህግ ማስፈጸሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊ
5. ዶ/ር ውብሸት ሽፈራው — ጠበቃ እና የሕግ አማካሪ የአርቃቂ ቡድኑ አባል
6. ዶ/ር ስሜነህ ቢሮስ — የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህግ መምህር የአርቃቂ ቡድኑ አባል
7. አቶ እሸቱ ወ/ሰማያት — በግል የህግ ባለሙያና ጠበቃ የአርቃቂ ቡድኑ አባል

8. ሌሎች የአርቃቂ ቡድን አባላት

## 4. <u>በምርመራ ሂደት የተለዩ ዋና ዋና ጭብጦች</u>

4.1. ረቂቅ ሕጉ የወንጀል ፍትህ ሂደቱን ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት እና ኢትዮጵያ ከተቀበላቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ መርሆች እና እሴቶች እንዲሁም ከወንጀል ህጉ ጋር ለማጣጣምና ለማስፈጸም የሚያስችል ዘመናዊና ጠቀሜታው የጐላ ሕግ መሆኑን፤

4.2. ረቂቅ ሕጉ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት የወንጀል ፍርድ ሂደት የተጠርጣሪን እና የተከሳሽን እንዲሁም በወንጀል ምክንያት የተጐዱ ሰዎችን ሰብአዊ መብቶች ለማክበር እና ለማስከበር፣ የሕግ የበላይነት ለማስፈን የሚያስችል አሰራር ለመገንባት የተሟላና የጥፋተኝነት ድርድር፣ እውነትን የማውጣት ሂደት ዓለም አቀፍ መርህን የተከተለ እንዲሆን፣ ልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴንና ለተጎጂዎች ካሣ የሚከፈልበት አግባብ ያካተተ ዘመናዊ ሕግ መሆኑን፤

4.3. ረቂቅ ሕጉ ሀገሪቱ በወንጀል ፍትሕስርዓት በዓለም አቀፍ ሕግ ያሏትን መብቶች ለማስከበር እና የተጣሉባትን ግዴታዎች በመወጣት በኩል የፍትሕ አካላት ሊኖራቸው የሚችለውን የትብብር ድርሻ የሚያስቀምጥ እና ይህንን ድርሻቸውን በአግባቡ መወጣት የሚችሉበትን ቅንጅታዊ አሰራር ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑን፤

4.4. የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስርዓቱ ለጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም የሚሰራ ለማድረግ የሚያስችል የስነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ መሆኑን የሚሉት በጭብጥነት ተለይተዋል።

4.5. ረቂቅ ህጉ በህገ መንግስቱ በወንጀል ህጎች፣ አለም አቀፍ ህጎች እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተረጋገጡ ልዩ ትኩረት ለሚያሻቸው ለሴቶች፣ ህፃናት እና አካል ጉዳተኞች የተሰጣቸውን መብቶች ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ መሆኑን።

4.6. ተበታትነው የነበሩትን የማስረጃ ህጎች ወጥ በሆነ መልኩ ማሰባሰብ፣ ዘመኑን የዋጀ እና በማስረጃ ህጎች ላይ ይታዩ የነበሩ ክፍተቶችን የሞላ መሆኑን።

## 5. <u>በዋናው ሕግ ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች</u>

5.1. በረቂቅ ሕጉ መግቢያዉ ላይ የመጀመሪያ ፓራግራፍ "ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብክ ሕገ መንግሥት እና ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ መርሆች እና እሴቶች ጋር ለማጣጣምና ለማስፈፀም የሚያስችል ዘመናዊ የወንጀል ፍትሕ ሂደት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል።"

ምክንያቱም ፓራግራፉ የቃላትና የሰዋሰዉ ችግር የነበረበት በመሆኑ ነው።

5.2 የረቂቅ ሕጉ መግቢያ /Preamble/ አራተኛው **ፓራግራፍ በሚከተለው አግባብ ተስተካክሏል።**

**የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ለጠቅላለው ጥቅም እንዲሰራ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑና የሥነሥርዓትና የማስረጃ ድንጋጌዎች በጠቅላለው የሚመሩበትን ዓላማ እና መርህ መደንገግ በማስፈለጉ፣**

**ምክንያቱም በልዩ የወንጀል ሕጎች ተበታትነው ይገኙ የነበሩት ወደዚህ ሥነሥርዓት ይካተታሉ በሚል እሳቤ የተረቀቀ ስለነበረ እና ድንጋጌዎቹ በልዩ ሕጎች እንዲቆዩ ስለተደረገ ማጣጣም በማስፈለጉ ነው።**

**5.3** በረቂቅ ሕጉ 2013 ዓ.ም ተብለው የተገለጹት ዓመተ ምህረቶች 2015 ዓ.ም በሚለው ተተክተዋል።

ምክንያቱም ረቂቅ ሕጉ የተመራበት ዓ.ም ሳይሆን ይጸድቃል ተብሎ የሚታሰብበት ዓ.ም መጻፍ ስላለበት ነው።

5.4. ረቂቅ ሕጉ ማዕደቂያ አንቀፅ 2(2) ስር ከፊደል (ሀ) እስከ (ሸ) ያሉት የተሻሩ ሕጎችን የሚዘረዝሩት ድንጋጌዎች ሙሉ በሙሉ እንዲወጡ በማድረግ ንዑስ አንቀፁ እንደሚከተለው ተስተካክሏል፥

አንቀጽ 2(2) በሌሎች አዋጆች የተመለከቱ የወንጀል ምርመራ፣ የዳኝነት ስልጣን፣ የወንጀል ሥነ ሥርዐት፣ የማስረጃ እና ዓለም አቀፍ ትብብርን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

ምክንያቱም ይህኛው አገላለፅ የተሻለ በመሆኑ ነው።

5.5. በረቂቅ ሕጉ ማፅደቂያ አንቀጽ 2(3) ድንጋጌ ውስጥ ያለው ልማዳዊ የሚለዉ ቃል እንዲወጣ ተደርጓል።

ምክንያቱም ልማዳዊ አሰራር የሕግ ደረጃ የሌለዉ በመሆኑ ልማድን መሰረት በማድረግ ሕጋዊ ስርዓት መዘርጋት ስለማይቻል ነው።

5.6. በረቂቅ ሕጉ ማፅደቂያ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 ሆኖ የሚከተለው አዲስ ድንጋጌ ተጨምሯል።

አንቀጽ **2(4)** በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም የሽብር ወንጀል፣ የሙስና ወንጀል፣ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል የኮምፒውተር ወንጀል በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ላይ ያሉ እና የሚወጡ ልዮ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው።

ምክንያቱም በፋይናንስ ድርጊት ግብረ ሃይል እና መሰል ተቋማት የሚሰጡ ምክረ ሃሳቦችን ለማካተት ሲባል በየጊዜው እነዚህ አዋጆች ተቀያያሪ ሃሳቦችን የሚያስተናግዱ ስለሆነ እና ሁሉንም በሥነ ስርዓት ሕጉ ማካተት ስለማይቻል ባሉበት እንዲሰሩ ለማስቻል ነው።

5.7. በረቂቅ ሕጉ ማፅደቂያ 3(2) ድንጋጌ ውስጥ ያለው የወንጀል ጉዳይ ከሚለው ቀጥሎ ተጠርጣሪውን ወይም የሚል ቃል ተጨምሯል።

ምክንያቱም ድንጋጌው ከክስ በፊት ያለውን ሂደት ለማካተት ነው።

5.8. **በረቂቅ ሕጉ ማፀደቂያ አዋጁ አንቀጽ** 3 **የመጨረሻ ንዑስ አንቀፅ ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል፡፡**

**አንቀፅ 3(7) የተለዋጭ ቅጣት አስፈፃሚ ቦርድ እስከሚቋቋም ድረስ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች እና የተከላካይ ጠበቃ ተቋም እስከሚቋቋም ድረስ ጠቅላይ ፍርድቤት ተግባራቱን እያከናወኑ ይቆያሉ የሚል ተጨምሯል፡፡**

**ምክንያቱም ተቋማቱም እስከሚቋቋሙ ድረስ ተግባራቱ የማከናወን ኃላፊነት የሚወስድ ተቋም ስለሚያስፈልግ ነው፡፡**

5.9. **በረቂቅ ሕጉ**አንቀጽ 1(1) እንደሚከተለው ተስተካክሎ አንቀጽ 1 (2) የነበረው ወደ አንቀጽ 2(1) ላይ ተወስዷል።

አንቀጽ **1** ይህ ሕግ 1996 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ እና በሕጉ አንቀጽ 3 መሰረት የወጡ እና የሚወጡ ልዩ የወንጀል ሕጎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

ምክንያቱም የተፈፃሚነት ወሰኑን በግልጽ ለማስቀመጥና የወንጀል ሕግ ትርጉሙን በትርጉም ክፍል ለማካተት ነው።

5.10. **በረቂቅ ሕጉ**አንቀጽ 1 (2) የነበረው ወደ አንቀጽ 2(1) በማምጣት በሚከተለው መልኩ ተደንግጓል። አንቀጽ 2(1) የነበረው ወደ አንቀጽ 2 (2) ተሸጋሽጓል።

አንቀጽ 2(1) የወንጀል ሕግ ማለት በ 1996 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ እና በሕጉ አንቀጽ 3 መሰረት የወጡ እና የሚወጡ ልዩ ሕጎች ማለት ነው።

ምክንያቱም ለሁሉም አዋጁ ላይ ላሉት ድንጋጌዎች እንዲያገለግል በትርጉም ክፍል ለማካተት እና በተፈፃሚነት ወሰን ስር መካተቱ ትክለለኛ ቦታው ስላልሆነ ነው።

5.11. **በረቂቅ ሕጉ** አንቀጽ 2(1) የነበረው በተሸጋሸገው አንቀጽ 2(2) እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

አንቀጽ 2(2)"ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ፵፯ መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ ዓላማ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል።

ምክንያቱም ወደፊት ሊመሰረቱ የሚችሉ ክልሎችን ለማካተት እንዲቻል ነው።

5.12. **የረቂቅ ሕጉ**አንቀጽ 2(2) ቀጥሎ አዲስ አንቀጽ 2(3) እንደሚከተለው ተጨምረዋል።

2(3) "የፖሊስ ተቋም" ማለት የፌደራል እና የክልል ፖሊስ ተቋም ማለት ነው

ምክንያቱም የተተረጎመው ግለሰቡ ሳይሆን ተቋሙ ስለሆነ ነው።

5.13. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 2(3) የነበረው በሚከተለው መልኩ ተስተካክሎ አንቀጽ 2(4) ሆኖ ተሸጋሽጓል።

አንቀጽ 2(4) "ፖሊስ" ማለት መሰረታዊ የሆነ የፖሊስ ሙያ ሥልጠና ተሰጥቶት በፌደራል ወይም በክልል ፖሊስ ተቋም ተቀጥሮ የሚሰራ የተፈጥሮ ሰው ነው።

ምክንያቱም የፖሊስ ትርጉም መካተት ስላለበት ነው።

5.14. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 2(2) የነበረው ወደ አንቀጽ 2(5) እና 2(4) እና ቀጥሎ ያሉት ንዑሰ አንቀጾች የነበሩት 2(6) ጀምሮ እንደየቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል።

ምክንያቱም አዲስ የተጨመሩ ንዑስ አንቀፆች ስላሉ በቅደም ተከተላቸው መሰረት ለማሸጋሸግ ነው።

5.15. በረቂቅ ሕጉ 2(5) በተሸጋሸገው 2(7) እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

አንቀጽ 2(7) "የዓቃቤ ተቋም" ማለት የፌደራል ፍትሕ ሚኒስቴር ወይም የክልል ፍትሕ ቢሮ ወይም የክልል ዓቃቤ ሕግ ተቋም ነው።

ምክንያቱም በፌደራሉ እና በክልል ደረጃ ያለውን የዓቃቤ ሕግ አደረጃጀት ለማካተት ነው።

5.16. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 2(8) በተሸጋሸገው 2(10) ድንጋጌ ላይ ያለው የፌደራል ወይም የክልል

የሚለዉ ሀረግ እንዲሰረዝ ተደርጓል። እንዲሁም ፍርድ ቤት የሚለው አካል ነው በሚል ተተክቷል። የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 2(9) የነበረው አንቀጽ 2(11) ሆኖ ተሸጋሽጓል።

ምክንያቱም የፌደራል ወይም ክልል ብሎ መገደቡ ከነዚህ መንግስት መዋቅር ዉጪ የሚኖሩ ፍ/ቤቶችን ለምሳሌ የጦር ፍርድ ቤት በዳኝነት የመንግስት አካል የማይካተትና በአስፈጻሚዉ አካል ዉስጥ የሚገኝ የዳኝነት ስራ የሚሰራ አካል በመሆኑ ለትርጉም በር የሚከፍት ስለሆነ ነው።

5.17. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 2(9) በተሸጋሸገው 2(11) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ተጨምሯል። አንቀጽ 2(10) የነበረው 2(13) እና ሌሎቹም እንደየ ቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል።

አንቀጽ 2(12) "የጥብቅና ተቋም" ማለት በወንጀል ጉዳይ ለተጠረጠረ፣ ለተከሰሰ ወይም ለተፈረደበት ግለሰብ በግል ወይም በተቋም የጥብቅና አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው።

ምክንያቱም የጥብቅና ተቋም ከሚሰራው ስራ አንጻር በግልጽ መተርጎም ስላለበት ነው።

5.18. በረቂቅ ህጉ አንቀፅ 2(15)፣ 2(16) እና 2(17) በተሸጋሸገው አንቀፅ 2(18)፣ 2(19) እና 2(20) እንደሚከተለው ተስተካክለዋል።

2(18) “ከባድ ወንጀል” ማለት በወንጀል ሕግ መሠረት የቅጣት መነሻው ከግምት ውስጥ ሳይገባ ከአስራ አምስት ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል የወንጀል አይነት ነው፤

2(19) “መካከለኛ ወንጀል” ማለት በወንጀል ሕግ መሠረት የቅጣት መነሻው ከግምት ውስጥ ሳይገባ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ የወንጀል አይነት ነው፤

2(20) “ቀላል ወንጀል” ማለት በወንጀል ሕግ መሠረት የቅጣት ጣሪያው አምስት ዓመትና ከዛ በታች በሆነ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ የወንጀል አይነት ነው።

ምክንያቱም በነባሩ ረቂቅ የወንጀል አይነቶችን ከባድ፣ መካከለኛ እና ቀላል ብሎ ትርጉም ለመስጠት መሰረት የተደረገው የቅጣቱን መነሻ ሲሆን፣ ነገር ግን በተግባር የቅጣት መነሻቸው በዚህ መልኩ የተቀመጠላቸው የወንጀል አይነቶች በጣም አነስተኛ በመሆናቸው የቅጣት መነሻቸውን እንደ መስፈርት ከመውሰድ ይልቅ የቅጣት መጠናቸው እስከ ስንት አመት ድረስ የሚያስቀጡ የሚለውን እንደ መስፈርት መውሰድ አግባብ በመሆኑ ነው በተጨማሪም ወደ ሰንጠረዡ ከማመልከት ይልቅ በዚህ መንገድ ግልፅ አድርጎ ማስቀመጡ በቀላሉ ለመረዳት ስለሚያስችል ነው።

5.19. ከረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 2(17) በተሸጋሸገው አንቀፅ 2(20) ቀጥሎ ሦስት አዳዲስ ንዑስ አንቀፆችን በመጨመር የሚከተሉት ሦስት ሀሳቦች ትርጉም የተሰጣቸው ሲሆን በረቂቅ ህጉ አንቀፅ 2(18) እና ከዚያ በኋላ የነበሩት ንዑስ አንቀፆች እንደ ቅደም ተከተላቸው እስከ 2(32) ድረስ በመሆን ተሸጋሽገዋል።

2(21) “ምርመራ” ማለት ተፈጸመ የተባለውን ወንጀል አስመልክቶ በዚህ ሕግ መሠረት መረጃና ማስረጃ የመሰብሰብና ተያያዥ ተግባራትን ማከናወን ነው።

2(22) "ምርመራ መምራት" ማለት የምርመራ ሂደት ሕጋዊነትን ለማረጋገጥ በዐቃቤሕግ የሚከናወን የምርመራ ክትትል፣ የሕግ ምክር፣ ምርመራ እንዲጀመር እና ሌሎች ትዕዛዞችን የመስጠት ተግባር ነው።

2(23) "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት አንድ ምክንያታዊ ሰው አስቀድሞ ሊገምተው እና ሊያስቀረው የማይችል ነገር ነው ።

ምክንያቱም ቃላቶቹና ሀረጎቹ መተርጎማቸው ግልፅነትን ስለሚፈጥር ነው።

5.20. የረቂቅ ሕጉ 2(18) ላይ በተሸጋሸገው ድንጋጌ ደግሞ 2(24) ላይ ያለው ማስረጃ የሚለው ቃል በሚከተለው መልኩ ተስተካክሎ ተተርጉሟል።

2(24) "ማስረጃ" ማለት በጭብጥ የተያዘን አግባብነት ያለውን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል የሚያስችል ማንኛውም ነገር ነው።

ምክንያቱም ከድንጋጌው የወጡት ሀሳቦች መግባታቸው ለድንጋጌው ምንም የሚሰጡት ጥቅም የሌለ ሲሆን እንዲያውም ግልፅ እንዳይሆን አድርገውታል።

5.21. በረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 2(25) በተሸጋሸገው ንኡስ አንቀፅ 2(31) እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

2(31) ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው።

ምክንያቱም ትክክለኛው አተረጓገም ይኼ ስለሆነ ነው።

5.22. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 3 እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

<u>አንቀፅ **3** ዓላማ</u>

የዚህ ሕግ ዓላማ

1/ በኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት የተረጋገጡና እውቅና ያገኙ የዜጎችን የሰብአዊ መብቶች መርሆችና ድንጋጌዎች በወንጀል ምርመራ ክስ ፍርድና ውሳኔ ሂደት ውስጥ ማክበር፣ማስከበርና መከበራቸውን ማረጋገጥ፣

2/ የወንጀል ጉዳይ ምርመራና ስርአታዊ ክንውኑ በህግ መሰረት እውነታን ማውጣት፣ውጤታማና ፍትሐዊ እንዲሆን ማድረግ

3/ በወንጀል ፍትህ ስርዐቱ ውስጥ የመንግስትን ኃይል የመጠቀም ብቸኛ ስልጣን መገደብ፣የሕግ የበላይነት ማረጋገጥ

ምክንያቱም የመንግስት ሥልጣን የሚመነጨው ከሕገመንግስት ነው፤ ሕገመንግስት የሚሰጠው የተገደበ ስልጣን ነው። ስለሆነም የሕግ የበላይነት የሚኖረው የተገደበ ስልጣን ሲኖር ስለሆነ የዚህ ህግ ድንጋጌዎች ስልጣን ሲሰጥ የተገደበ መሆን ስላለበትና ሃሳቡን በአዲስ መልክ ለማደራጀት ነው።

**5.**23 የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 5 ነፃ ሆኖ የመገመት መብት የሚለው ርዕስ እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት በሚል ተስተካክሏል። የዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 ከአራት ነጥብ በኋላ ያለው ሀሳብ ንዑስ አንቀጽ 3 ሆኖ እንደሚከተለው ተደንግጓል።

5(3) ተከሳሽ ከቀረበበት ክስ ራሱን የመከላከል መብት አለው።

ምክንያቱም ከሕገ መንግስቱ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አገላለፅ መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

5.24. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 6 ርዕሱና ድንጋጌው በሚከተለው መልኩ ተስተካክሎ ቀርቧል።

<u>አንቀጽ **6**. በአንድ ወንጀል ድጋሚ ክስ እና ቅጣት ስለመከልከሉ</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ ሕግ እና በወንጀል ሕግ መሠረት በተቀጣበት፣በነፃ በተለቀቀበት ወይም በአማራጭ መንገድ እና ተለዋጭ መፍትሄ እልባት ባገኘበት የወንጀል ጉዳዩ እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም።

ምክንያቱም የሕገ መንግስቱን ድንጋጌ እና የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 2(5) በመከተል የረቂቅ ሕጉ ይዘት "እንደገና አይከሰስም" ብቻ ሳይሆን "እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም" በሚል መስተካከሉ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

5.25 የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 9 ላይ "ጭካኔ የተሞላበት ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "የማሰቃየት ተግባር" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል።

ምክንያቱም በፍርድ ሂደቱ ውስጥ የማሰቃየት ተግባር መፈጸም የተከለከለ መሆኑን በግልፅ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

5.26 የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 10(3)(ሐ) በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል።

10(3)ሐ) ተከሳሹ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በራሱ ለመከራከር ካልመረጠ በስተቀር በከባድ ወንጀል የተከሰሰ ሰው ፣ ወይም

ምክንያቱም ድንጋጌው በራሱ መከራከር የሚፈልግ ተከሳሽን መብትን እንዳያጣብብ ለማድረግ ነው።

5.27 በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 11 ርዕሱ የተፋጠነ ፍትህ ስለመስጠት ተብሎ ተስተካክሏል

ምክንያቱም የተሻለው አገላለፅ ይሄኛው ስለሆነ ነው።

5.28 የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 12/1/ ክስ የሚለው ክርክር ተብሎተተክቷል።

***ምክንያቱም*** በጊዜ ቀጠሮ ወቅትም ተግባራዊ እንዲሆን እና ከአንቀፁ ንዑስ 2 ጋር ተመሳሳይ እንዲሆን ነው።

5.29 ረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 12/2/ በሚከተለው ተስተካክሏል። 'በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በተከሳሹና በተጎጂው የግል ሕይወት፣በሕዝብ የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱ ደኅንነት ለመጠበቅ፣የሂደቱ ሚስጢራዊነት በሕግ የተደነገገ ሲሆን ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል።'

***ምክንያቱም*** በልዩ ዘዴ ማስረጃ የማሰባሰብ ሂደት ሚስጥራዊ እንዲሆን የተደነገገ ሲሆን ሚስጢራዊነቱ እንደተጠበቀ እንዲቀጥል የፍርድ ሂደቱም በዝግ ችሎት ሊሆን ይገባል።

5.30 በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 14(3) ድንጋጌ ላይ ወይም በምልክት ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ቋንቋ የሚል ቃል እንዲገባ ተደርጓል፡፡
ምክንያቱም የቃሉ አለመግባት የሰዋሰዉ ግድፈት ስለሚያስከትል ነው፡፡

5.31 በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 15(3) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 15(4) ሆኖ ተጨምራል፡፡
15(4) ተጠርጣሪው ቃል የሚሰጥበት ጊዜ፣ ቃል በመስጠት ሂደት የሚኖር የእረፍት ሰዓት፣ቃል የሚሰጥበት ቦታ ድባብ እና የመርማሪው ባህሪ እውነትን ለማውጣት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር መሆን አለበት፡፡
ምክንያቱም የተጠርጣሪዎችን መብት የበለጠ ለመጠበቅ በማሰብ ነው፡፡

5.32 በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 16(3) ድንጋጌ ላይ ጉዳዩ የሚታየው ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ በሕግ በተቋቋመ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እና በዚህ ሕግ በታወቀ ስርዓት ብቻ የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

ምክንያቱም ክስ መታየት ያለበት በሕግ በተቋቋመ አካል ብቻ መሆኑን አፅንዖት ለመስጠት እና አማራጭ መንገዶች በዚህ ሕግ እውቅና የተሰጣቸው በመሆኑ ነው፡፡

5.33. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 18(1) (ተ) ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል፡፡
ለሴቶች፣ ሕፃናት፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋውያን ወይም ለጥቃት የተጋለጡ ሌሎች የሕብረሰብ ክፍሎች በሕግ የተረጋገጡ መብቶቻቸው እውን እንዲሆኑ አስፈላጊውን ሁሉ ያመቻቻሉ፡፡
ምክንያቱም በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተዘረዘሩት መብቶቻቸው በሌላ ሕግ የተደነገገ በሆነ ጊዜ ሁሉም የፍትሕ ተቋማት የማስጠበቅ ግዴታ እንዳለባቸው ለማመላከት ነው፡፡

5.34. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 19 (3) በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል ፡፡

19(3) የመያዣና የብርበራ ትእዛዝ ከፍርድ ቤት በማውጣት የተርጣሪውን ሰብአዊ መብት ባከበረ መልኩ ብርበራ ያካሂዳል ፤የተገኘውንም ማስረጃ ይይዛል፣ ተጠርጣሪው በተጠረጠረበት ወንጀል ነጻ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃም ሲያገኝ ለተጠርጣሪው ወይም ለተከሳሽ ይሰጣል፡፡
ምክንያቱም ፖሊስ መገደድ ያለበት ተከሳሹን ነፃ የሚያወጣ ማስረጃ ማሰባሰብ ሳይሆን ካገኘ ዝም ሳይል መስጠት ያለበት መሆኑን ለማመልከት እንዲሁም ብርበራ ሲያካሂድ የተጠርጣሪውን መብት ባከበረ መልኩ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡

5.35. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 19(5) ላይ ያለው ኤግዚቢቶችን የሚለው ቃል ኢግዚቢትን በሚል ቃል እንዲተካ ተደርጓል፡፡
ምክንያቱም ትክክለኛው የሰዋሰው አገላለጽ ይህ ስለሆነ ነው፡፡

5.36. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 19(7)ላይ ከሀኪሙ ከሚለው ቃል ቀጥሎ ያለውን ወይም የሚለው ቃል በማውጣት በድርብ ሰረዝ እንዲተካ የተደረገ ሲሆን፣ ከሀይማኖት አባቱ ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ወይም ከሀይማኖት መሪው እንዲሁም ከቅርብ ዘመዶቹ ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ከልጆቹ የሚል ቃል እንዲገባ ተደርጓል።

ምክንያቱም ድንጋጌውን የተሟላና የተሻለ ለማድረግ ነው።

5.37. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 19(8) ቀጥሎ አዲስ አንቀፅ 9 ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል። ሌሎች ንኡስ እንደቅደምተከተላቸው ተሸጋሽጓል።

19(8) በሴቶች፣ህጻናት፣ አካልጉዳተኞችና አረጋዊያን ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዙሪያ ልዩ የምርመራ አሰራር ስርአት ይዘረጋል፤ ይተገብራል።

ምክንያቱም የሴቶችና ህጻናት እና የአካል ጉዳተኞችን በሚመለከት ልዩ ትኩረት በመስጠት አሰራር ስርአት ለመዘርጋት ነው።

5.38. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 20(1) ላይ የወንጀል ምርመራን ከሚለው ቀጥሎ ያለው በበላይነት የሚለው ቃል እንዲሰረዝ ተደርጓል።

ምክንያቱም አስፈላጊ ስላልሆነና የተለየ ትርጉም ስለሚሰጥ ነው።

5.39. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 20 (4) ላይ አማራጭ ከሚለው ቀጥሎ ያለው ስርዓት የሚለው ቃል እንዲሰረዝ ተደርጎ መንገድ በሚል ቃል እንዲተካ ተደርጓል።

ምክንያቱም ትክክለኛው ቃል መንገድ የሚለው በመሆኑ ነው።

5.40. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 20 (6) የነበረው ተሰርዞ የሚከተለው አዲስ ድንጋጌ ንዑስ 6 ሆኖ ገብቷል።

20(6) በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የሚገኙ ከወንጀል ጋር የተገናኙ ንብረቶች የማስመለስ ስራዎችን ይሰራል፤ ያስተባብራል፤

ምክንያቱም የአቃቤ ህግ ስልጣን ባለመሆኑ የበፊቱ አንቀፅ 6 እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን እንደ አዲስ የተካተተው ደግሞ በአስፈፃሚ አካላት አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት ይህ ስልጣን ለፍትህ ሚኒስቴር የተሰጠው በመሆኑ ነው።

5.41. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (6) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ 7 ተጨምሯል። ቀሪዎቹ ንዑስ አንቀፆች እንደ ቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል።

20(7) ከወንጀል ጋር የተገናኘ ንብረትን በሚመለከት አስቀድሞ የመለየት፣ መመርመር እንደ አግባብነቱ የማገድ ወይም ማሳገድ፣ የመያዝ፣ ወንጀል ተግባር የደረሰ ጉዳት የተገኘ ጥቅም ላይ ትንተና ማካሔድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግ፣ የንብረት ዋጋ እንዲገመት፣ በንብረት አስተዳደር ስር እንዲቆይ የማድረግ እና በፍርድ ቤት እንዲወረስ ያደርጋል።

ምክንያቱም በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 40(2)(ለ) ላይ ለፍትህ ሚኒስቴር የተሰጠ ኃላፊነት በመሆኑ እና አዋጁ ለማስተግበር ተግባርና ኃላፊነቱን ማካተት አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

5.42.የረቂቅ ሕጉአንቀጽ 20/9 / ቀጥሎ 20(10) ሆኖ የሚከተለው ንዑስ አንቀፅ ተጨምሯል። ሌሎቹ ንዑስ አንቀፆች እንደቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል።

20(10) ተከሳሽን ወይም ግብረ አበርን ወደ ምስክር ያዞራል'

**ምክንያቱም** በርካታ ተጠርጣሪዎች ወይም ተከሳሾች በሚኖሩበት ጊዜ ጉዳዩን በይበልጥ በማስረጃ ለማጠናከር እንዲቻል እና አሁንም በተግባር እየተሰራበት የሚገኝ ስለሆነ ነው።

5.43. የረቂቅ ህጉ አንቀፅ በነባሩ አንቀፅ 20(12) በተሸጋሸገው 20(14) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀፅ 20(15) ሆኖ ተጨምሯል።

20(15) በሀገር ወስጥና በውጪ ሀገር የሚገኙ ከወንጀል ጋር የተገናኙ ንብረቶችን በተመለከተ ይመረምራል፣የማስመለስ ስራዎችን ይሰራል፣ያስተባብራል፤

**ምክንያቱም** በአስፈፃሚ አካላት አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት ይህ ስልጣን ለፍትህ ሚኒስቴር የተሰጠው በመሆኑ፣ ይህኛው ሕግ ከሌሎች ሕጎች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

5.44.የረቂቅ ህጉ አንቀፅ 21 እንደ ሚከተለው ተስተካክሏል።

<u>አንቀፅ **21** የፍርድ ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

ፍርድ ቤት፡-

1. ጊዜ ቀጠሮ፣የብርበራ፣የመያዣ እና ሌሎች ቅድመ ክስ ተግባራትን በተመለከተ አስፈላጊውን ትእዛዝ ይሰጣል።
2. የቀረበ ተጠርጣሪ፣ተከሳሽ፣ምስክር የፍርድ ቤቱን የሥራ ቋንቋ የማይረዳው ወይም በምልክት ቋንቋ መግለጽ አስፈላጊ እንደሆነ አስተርጓሚ ይመድባል።
3. የቀረበ የወንጀል ክስን ይመረምራል፣ማስረጃ ይቀበላል፣ያከራክራል፣እንደ አግባብነቱ ትእዛዝ፣ብይን፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ ይሰጣል፣ የሰጠውን ውሳኔ ያስፈጽማል ወይም እንዲፈጸም ያደርጋል።

4. በያዘው ጉዳይ ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መኖሩን ሲረዳ ወይም አቤቱታ ሲቀርብለት ጉዳዩ እንዲጣራና ርምጃ እንዲወሰድ አስፈላጊውን ትዕዛዝ ይሰጣል ወይም በራሱ እርምጃ ይወስዳል።

5.የቀረበን የወንጀል ጉዳይ በነፃነት፣በገለልተኝነት፣አድሎ በሌለበት፣በብቃት እና በግልፅ ችሎት ይዳኛል።

6.በሕመም ምክንያት ችሎት መቅረብ የማይችልሰው ወይምለጥቃት የተጋለጠ ምስክር ችሎት ሳይቀርብ የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥበት ሁኔታ ያመቻቻል።

7.በእርቅ፣በጥፋተኝነት ድርድር፣በባህላዊ ሥርዐት እልባት የተሰጠባቸውን ጉዳዮች ከሕግና ሞራል ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ይመዘግባል። የተመዘገበው እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔሆኖ እንዲፈፀም ትዕዛዝ ይሰጣል።

8. በንብረት ላይ የእግድ ወይም የመያዝ ትእዛዝ ይሰጣል፣እንደ አስፈላጊነቱ የታገደ ንብረትን የሚያስተዳድር አካል ይሾማል፣ወይም ንብረቱ እንዲወረስ ትእዛዝ ይሰጣል።

9. በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶችን በዚህ ሕግ መሠረት ተፈፃሚ እንዲሆኑያደርጋል።

10. በዚህ ሕግ መሠረት በወንጀል ጉዳይ አለምአቀፍት ትብብር ጉዳዮች ላይ አስፈላውን ትዕዛዝ ይሰጣል።

ምክንያቱም ተጨማሪ የፍርድ ቤት ሃላፊነት የሆኑ አምስት ተግባራት ተጨምረውና ከአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ጋር እንዲናበብ ተደርጎ ተስተካክሏል።

5.45. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 22 በተስተካከለው አንቀፅ 21 ላይ ያለው የማረሚያ ቤት ተግባርና ኃላፊነት የሚለው ንዑስ አንቀፅ /2/ እንደሚከተለው ተስተካክሎ ቀርቧል።

/22/2/ ታራሚ ወይም ተከሳሽ ከሕግ አማካሪው፣ ከሐኪሙ ፣ ከኃይማኖት አባቱ ወይም ከኃይማኖት መሪው የጥብቅና፣ የጤና ወይም መንፈሳዊ አገልግሎት ለማግኘት እንዲሁም ከጓደኛው ወይም ከቅርብ ዘመዶቹ ፣ከልጆቹ፣ከትዳር አጋሩ ጋር በግል የሚገናኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

ምክንያቱም ታራሚዎች በሕግ ጥላ ስር ቢሆኑም ልጆች ከቤተሰቦቻቸዉ ማግኘት የሚገባቸዉ እንክብካቤ እንዲያገኙና ተከሳሹ ወይም ታራሚው ከትዳር አጋሩ ወይም አጋሯ ጋር መገናኘት እንዲችሉ ለማድረግ ነው።

5.46. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 22 ላይ የሚቀጥሉት አዲስ ንኡስ አንቀጽ 6 እና 7 ተጨምሯል። ንኡስ አንቀፅ 6 የነበረው ንዑስ አንቀፅ 8 ሆኖ ተሸጋሽጓል።

22(6) በማረፊያ ወይም በማረሚያ ቤት የሚቆዩ ሰዎችን ለሚደርስባቸው ኢሰባዊ አያያዝ የተፋጠነ ምላሽ የሚሰጥ እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት ይዘረጋል

22(7)ሌሎች በፍርድ ቤት የሚሰጡ ትዕዛዞችን ይፈፅማል።

ምክንያቱም በማረፊያ ወይም በማረሚያ ቤት አያያዛቸውን በተመለከተ ቅሬታ ካላቸው የሚስተናገዱበት መንገድ ለመፍጠርና እንዲሁም ከተዘረዘሩት ውጭ ሌላ ትዕዛዝ ከተሰጠ ማስፈፀም እንዲቻል ነው።

5.47. በረቅቅ ህጉ አንቀፅ 23 ላይ ያለው የተከላካይ ጠበቃ ተቋም ተግባርና ኃላፊነት ይል የነበረው የጥብቅና ተቋም እና የተከላካይ ጠበቃ ተግባርና ኃላፊነት በሚል እንዲስተካከል የተደረገ ሲሆን፣ በንዑስ አንቀፅ 1 ላይ በተጠረጠረበት ከሚለው ቃል

ቀጥሎ  ወይም የሚለው ቃል ተሰርዞ ፣ ይሰጣል ከሚለው ቃል ቀጥሎ ያለው ጉዳዩን የሚለው ቃል የጉዳዩን ሂደትና በሚል ቃል እንዲተካ የተደረገ ሲሆን ከንዑስ አንቀፅ 2 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 3 እንዲገባ ተደርጓል።

23(3) የጥብቅና ተቋሙ በሚመራበት የሥነምግባር ደንብ መሠረት አገልግሎት ይሰጣል።

ምክንያቱም  የስነምግባር ደንቡን ተከትሎ አገልግሎት እንዲሠጥ ለማድረግ ነው።

5.48.በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 23/2/ የፍትህ ተቋም ሲተረጎም የተከላካይ ጠበቃ ተቋም ከሚለው በፊት የጥብቅና ተቋም የሚል ቃል እንዲገባ ተደርጓል።

ምክንያቱም ጠበቆችን ያካተተ ስላልነበረ እንዲያካትት ታስቦ ነው።

5.49. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 24(5) ለሁለት ተከፍሎ እና ሀሳቦች ተጨምረውበት 24(5) እና 24(6) ሆኖ በሚከተለው መልኩ የቀረበ ሲሆን 24(6) የነበረው 24(7) ሆኖ ተሸጋሽጓል።

**24(5)** ዘር ማጥፋት፣ በሠው ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፣ ያለ ፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ መውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን መሠወር፣የጦር ወንጀል፣ የባህር ላይ ዘረፋ እና ሌሎች ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለምአቀፍ ሕጎችን በመጣስ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ላይ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን አላቸው።

**24(6)** የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 269 እስከ 322 ድንጋጌን በመጣስ በተፈፀሙ ወንጀሎች ላይ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን አላቸው።

ምክንያቱም የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በተስተካከለው አንቀፅ 24/5/ እና 24/6/ በተመለከቱት ወንጀሎች ላይ የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው በግልፅ ለማመልከት ነው።

5.50. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 25 (1) ላይ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (ሰ) እንዲገባ የተደረገ ሲሆን አስቀድሞ ሰ የነበረው ድንጋጌ ወደ ሸ እና ሌሎችም እንደ ቅደም ተከተላቸው ቀ እና በ ሆነው ተሸጋሽገዋል።

**25/1/**/ሰ/ በብሔርና ብሔረሰቦች መካከል ከተፈጠረ ግጭቶች ጋር የተያያዘ ወንጀሎች፣

ምክንያቱም እነዚህ የወንጀል አይነቶች ክልል ተሻጋሪ ባህርይ ስላላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን እንዲሆኑ ታስቦ ነው።

5.51. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 25 (1（ረ）ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል።

25(1（ረ）በፌደራልና በክልል መንግስታት መካከል በጋራ የሚቋቋሙ ድርጅቶችን በተመለከተ፤

ምክንያቱም  በሁለቱም መንግስታት ስለሚቋቋሙ ሥልጣኑ የፌደራል መንግስት እንዲሆን ነው።

5.52. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 25(2) "ለ" ተሰርዟል። እንዲሁም መደምደሚያው ላይ የወል የሚለው ቃል ተሰርዟል።

ምክንያቱም በ "ለ " የነበረው ሀሳብ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከተሰጠው ስልጣን ጋር ስለሚጋጭ ነው።

5.53. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 25 (3) እንደሚከተለው ተስተካክሏል። እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4 እንደሚከተለው ተጨምሮ ነባሩ ንኡስ አንቀጽ 4 የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5 ሆኖ ተሸጋሽጓል።

አንቀጽ 25 ንኡስ አንቀጽ (3) የኦሮሚያ ክልል የስራ ሃላፊዎች እና ሰራተኞች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ከስራ ሃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ በክልሉ መንግስት ጥቅም ላይ በሚፈጽሙት ወንጀል ላይ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ይኖራቸዋል።

አንቀጽ 25 ንኡስ አንቀጽ(4) የሌሎች ክልል የስራ ሃላፊዎች እና ሰራተኞቻቸው በአዲስ አበባ ከተማ ከስራ ሃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ በክልል መንግስት ጥቅም ላይ በሚፈጽሙት ወንጀል ላይ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ይኖራቸዋል።

**5.34.** በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 25(4) በተሸጋሸገው 25/5/ እንደ ሚከተለው ተስተካክሏል

25(**5**) በልዩ ህጎች ተለይተው ለፍርድ ቤት የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ህግ የተመለከተው የዳኝነት ስልጣን የዚህ ህግ አካል በሆነው ሰንጠረዥ ተደልድሏል።

ምክንያቱም በልዩ ሕጎች የፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን የያዙ በርካታ አዋጆች ስላሉ እና እያንዳንዱን አዋጅ ወደ ሠንጠረዡ ማምጣት ስለማይቻል በድንጋጌ ማስቀመጥ ስለሚያስፈልግና አጠቃላይ ሕጉን መጥቀስ ክፍተት እንዳይፈጠር ስለሚያግዝ ነው።

5.35. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 27፣ 28፣33፣34(1 እና 2)፣ 36(1)፣ 41(1 እና 4)፣ 130(1) ድንጋጌዎች ላይ ያለው በሰንጠረዥ "ሀ" የሚለዉ ሀረግ ተሰርዞ በሰንጠረዡ በሚል ቃል ተተክቷል።

ምክንያቱም በሰንጠረዥ ሀ ይል የነበረው ሰንጠረዡ በሚል ቃል በመተካቱ ነው።

5.36. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 26 ስለ ሕገ መንግስት ትርጉም አስመልክቶ የተደነገገዉ እንዲሰረዝ ተደርጎ አንቀፅ 27 የነበረው ድንጋጌ ወደ 26 እንዲሸጋሸግ የተደረገ ሲሆን ሌሎቹም ድንጋጌዎች በዚሁ አግባብ ተሸጋሽገዋል።

ምክንያቱም ከአዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀፅ 4 ድንጋጌ ጋር በንፅፅር ሲታይ ፍ/ቤቶች ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና የሚገድብ ስለሆነ ነው።

5.37. በረቂቅ ሕጉ በነባሩ አንቀፅ 28(2) በተሸጋሸገው አንቀፅ 27/2/ ላይ ስምምነቶች ከሚለው ቀጥሎ በመጣስ የተፈፀሙ ወንጀሎች በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ትክክለኛው አገላለፅ ይህ በመሆኑ ነው።

5.38. በረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 28 (4) በተሸጋሸገው አንቀፅ 27/4/ የተሰረዘ ሲሆን ንዑስ አንቀፅ 5 የነበረው ወደ ንዑስ አንቀፅ 4 ተሸጋሽጓል።

ምክንያቱም ስልጣኑ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስልጣን ስለሆነ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መስጠቱ ህገ መንግስታዊ ስላልሆነ ነው ነው።

5.39. በረቂቁ ህጉ አንቀጽ 30 /2/ በተሸጋሸገው 29/2/ ድንጋጌ ውስጥ ሌላ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም ወደ የሚለው ሀረግ እንዲሰረዝ ተደርጓል።

ምክንያቱም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስልጣን ስላልሆነ ነው።

5.40. በረቂቁ ህጉ አንቀጽ 32 (1) በተሸጋሸገው 31(1) እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

31(1) የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ውሳኔን ባፀናባቸው የወንጀል ጉዳዮች፤

ምክንያቱም ትክክለኛ አፃፃፍ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠበት ሳይሆን ካፀናበት መሆን ስላለበት ነው።

5.41. በረቂቅ ህጉ አንቀፅ 33 በተሸጋሸገው 32 ላይ ርዕሱ እና ድንጋጌው መግቢያ ላይ የክልል ከሚለው ቃል ቀጥሎ ወረዳ ፍርድ ቤት ወይም የሚል ሀረግ እንዲጨመር ተደርጓል፡

ምክንያቱም በክልል መዋቅር የመጀመሪያ ፍ/ቤት አደረጃጀት የያዘዉ የወረዳ ፍርድ ቤት በመሆኑ እሱን በግልፅ ለማመላከት ነው።

5.42. በረቂቅ ህጉ አንቀፅ 35 በተሸጋሸገው 34 የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ወይም የክልል ወረዳ ፍ/ቤት የሚል ሀረግ ተጨምሯል።

ምክንያቱም የወረዳ ፍ/ቤት በክልሎች አደረጃጀት በመኖሩ ነው

5.43. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 39 በተሸጋሸገው 38 ድንጋጌ እንደሚከተለው ተስተካክሏል፡

<u>አንቀጽ **38** በግልጽ ስላልተደነገገ ወንጀል የሥረ -ነገር የዳኝነት ሥልጣን</u>

የወንጀል የዳኝነት ስልጣን በግልፅ ባልተደነገገ ጊዜ የቀላል ወንጀልን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣መካከለኛ እና ከባድ ወንጀል ሲሆን የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድቤት የሥረ-ነገር የዳኝነትሥልጣን ይኖራቸዋል።

ምክንያቱም ሁሉንም የት እንደሚታዩ በግልፅ ያልተመለከቱ የወንጀል አይነቶችን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን መስጠቱ አግባብነት ስለሌለው ነው።

5.44. የረቂቅ ህጉ አንቀጽ 44 በተሸጋሸገው 43 ርዕሱና ድንጋጌው ላይ ወንጀል የተሰራበት የሚለው ሀረግ ወንጀል የተፈፀመበት በሚል ቃል ተተክቷል።

ምክንያቱም ትክክለኛው መጠሪያ ይህ በመሆኑ ነው

5.45. በረቂቁ ህጉ አንቀጽ 47(1) በተሸጋሸገው 46(1) ላይ ስልጣን ወደሌለው ፍርድ ቤት ከሚለው ቀጥሎ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት የሚል ሀረግ ተጨምሯል። እንዲሁም 46(2)(ለ) ሲታምን የሚለው ሲታመን በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ክስ የማዞር አቤቱታ የሚቀርብበትን ጊዜ በግልፅ ለማስቀመጥ ነው።

5.46. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 49 በተስተካከለው አንቀጽ 48/3/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

48/3/ የክልል ማረሚያ ቤቶች በክልል ፍርድ ቤቶች የሚሰጥ ውሳኔን ማስፈፀማቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል ፍ/ቤቶች የሚሰጡዋቸውን ትእዛዞች ያስፈፅማሉ።

ምክንያቱም የፌዴራል ፍርድቤቶችን ትዕዛዝ የሚያስፈፅሙ የክልል ማረሚያ ቤቶች አሉ ስለሆነም የክልል ማረሚያ ቤቶች የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ትዕዛዝ እንደሚያስፈፅሙ ለማመላከት ነው።

5.47. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 50 በተስተካከለው አንቀጽ 49/2/ በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል። አንቀፅ **49(2)** በዚህ ክፍል *መሠረት* የክልል የፍትሕ አካላት ለሚያከናውኑት የፌዴራል ተግባር የፌዴራል ፍትሕ አካላት አስፈላጊውን ወጪ ይሸፍናሉ።

ምክንያቱም የፌዴራል እና የክልል ፍትህ አካላት በውክልና ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች በርካታ ጉዳዮች ስለሚገናኙ ወጪው ሁሉንም ያካተተ መሆን ስላለበት ነው።

5.48. በረቂቅ ህጉ አንቀፅ 56(2) በተሸጋሸገው 55(2) ተገቢውን ይወስናል የሚለው ሀረግ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም ትክክለኛ አገላለጽ ይህ በመሆኑ ነው

5.49. በረቂቁ ህጉ አንቀጽ 57(2) እና 56(2) በሚከተለው ተስተካክሏል።

56(2) ማንኛውም ተከላካይ ጠበቃ ወይም ጠበቃ፡-

ሀ. ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል በዳኝነት በአቃቤ ሕግነት በተመራማሪነት በተከላካይ ጠበቃነት ወይም በጠበቃነት፣ በአስታራቂነት፣ በምስክርነት ወይም በልዩ አዋቂነት በጉዳዩ ላይ ተሳትፎ ሲያደርግ የቆየ ከሆነ፤

ለ. በጠበቆች የስነምግባር ደንብ መሰረት የጥቅም ግጭት ሊያስነሳ የሚችል ከሆነ፣

ከፍርድ ሂደቱ ተነስቶ በሌላ ተከላካይ ጠበቃ ወይም ጠበቃ ይተካል።

ምክንያቱም የተከላካይ ጠበቃን ብቻ ሳይሆን የግል ጠበቃንም እንዲያካትት ታስቦ ነው።

5.50. በረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 58(2) በተሸጋሸገው አንቀፅ 57(2) በፍትሐብሔር ወይም በስነምግባር ወይም በሌሎች መሰል ጉዳዮች የሚለው ሀረግ ተሰርዟል።

ምክንያቱም በፍትሐብሔር ወይም በስነምግባር መሰል ጉዳዮችን ማለት በፍትሀብሔር ላይ ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳዩ መልሶ በወንጀል ተሰይሞ እንዲያይ መፍቀድ ተገቢነት ስለሌለው ነው።

5.71. በረቂቁ ህጉ አንቀጽ 60 በተሸጋሸገው 59 ላይ ያለው ድንጋጌ እንደሚከተለው ተስተካክሎ ቀርቧል።

<u>አንቀጽ **59** አቤቱታው የሚቀርብበት ጊዜ</u>

አቤቱታ የሚቀርበው አቤቱታውን ለማቅረብ ምክንያት መኖሩ እንደታወቀ ወዲያውኑ መሆን ይኖርበታል።

ምክንያቱም ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሽ የሚለው ሀረግ አስፈላጊ ስላልሆነ ነው።

5.72. ከረቂቅ ህጉ ከአንቀፅ 63 ከተሸጋሸገው አንቀፅ 62 በላይ ያለው ርዕስ በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል። የወንጀል አቤቱታ እና አቤቱታን ማጣራት።

ምክንያቱም ትክክለኛ አገላለጽ ይህ በመሆኑ ነው

በረቂቁ ህጉ አንቀጽ 63 (3) በተሸጋሸገው 62 (3) ላይ ያለው 1 የሚለው ማጣቀሻ 2 በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ትክክለኛው ማጣቀሻ 2 ስለሆነ ነው።

5.73. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 64(2) በተሸጋሸገው 63(2) ላይ በፍሬ ሕጉ የሚለው በወንጀል ሕጉ በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም ትክክለኛው የፍሬ ሕግ ሳይሆን የወንጀል ሕጉን መሆን ለማሳየት ነው።

5.74. በረቂቁ በነባሩ አንቀጽ 65(2) በተሸጋሸገው 64(2) ላይ በትዳር ጓደኛ የሚለው ሀረግ በሚች ልጅ ከሚለው ሀረግ ቀድሞ እንዲመጣ ተደርጓል።

ምክንያቱም አቤቱታ የሚያቀርቡት ሰዎች ቅደም ተከተል ለሟቹ ባላቸዉ ቅርበት ሲቀመጥ የትዳር ጓደኛ መጀመሪያ ላይ መቀመጥ ስለሚገባው ነው።

5.75. በረቂቁ በነባሩ አንቀጽ 65(4) በተሸጋሸገው 64(4) ድንጋጌ መጨረሻ ላይ አቤቱታው ይሰረዛል ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ በጉዳዩ ላይ ድጋሚ አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም የሚል ሀረግ እንዲጨመር ተደርጓል።

ምክንያቱም ወንጀሉ በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚቀርብ በመሆኑና በጉዳዩ ላይ ድጋሜ አቤቱታ ማቅረብ እንደማይቻል ለማመልከት ነው።

5.76. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 66(3) በተሸጋሸገው 65(3) ስም ከሚለው በማስከተል እና አድራሻ የሚል ተጨምሯል።

ምክንያቱም የሚፈለገው ስሙ ብቻ ሳይሆን አድራሻውም ስለሆነ ነው።

5.77. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 68/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 67/1/ ይቻላል ከሚለው ከአራት ነጥብ በኋላ የሚከተለው ተጨምሯል። ሆኖም ጉዳዩ ሕፃናትን እና ጾታዊ ጥቃት የሚመለከት እንደሆነ ፍርድቤቱ የዐቃቤ ሕግን አስተያየት ይቀበላል።

ምክንያቱም የሕፃናትና የሴቶች ጥቃት በአብዛኛው በቅርብ ሰው የሚፈፀሙ በመሆኑ በፍርሀት አቤቱታውን እንዳያነሱ ለማድረግ ነው።

5.78. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 68(3) በተሸጋሸገው 67(3) መጨረሻ ላይ ያለው ሊቀጥል ይችላል የሚለው ሀረግ ይቀጥላል በሚል እንዲተካ ተደርጓል።

ምክንያቱም ሀረጉ ድንጋጌዉን ለትርጉም የሚያጋልጥ በመሆኑ ነው።

5.79. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 71 በተስተካከለው አንቀፅ 70 ንኡስ 2 ውሳኔውን የሚለው ቃል የምርመራ ውጤቱን በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ፖሊስ በመዝገብ ላይ ውሳኔ ሳይሆን የሚሰጠው መመርመር እና የምርመራ ግኝቱን ለዐቃቤ ሕግ ማሳወቅ ነው።

5.80. በረቂቅ ህጉ 73(1) በተሸጋሸገው 72(1) ድንጋጌ መጨረሻ ላይ ያለው መላክ አለበት የሚለው ሀረግ ይልካል በሚል ቃል ተተክቷል።

ምክንያቱም ትብብራዊና ግንኙነትን በሚያሳይ መልኩ ማመላከት ስላለበት ነው።

5.81. በረቂቅ ህጉ 73(2) በተሸጋሸገው 72(2) ላይ የነበረው ድንጋጌ ሙሉ ለሙሉ እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን ንዑስ አንቀፅ 1 ብቻውን ስለሚሆን (1) የሚለው ወጥቶ ያለ ቁጥር ይቀመጣል።

ምክንያቱም ቁጥር የማይሰጠው ንዑስ አንቀጽ ስለማይኖር ነው።

5.82. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 75(2 እና 3) በተሸጋሸገው 74 (2 እና 3) ላይ መርማሪ ከሚለው ቃል ቀጥሎ ያለው አካል የሚለው ቃል ፖሊስ በሚል ቃል እንዲተካ ተደርጓል።

ምክንያቱም መርማሪ ማን እንደሆነ በግልፅ ለማመልከት ነው።

5.83. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 75(4) በተሸጋሸገው 74(4) መጨረሻ ላይ ያለው የመፈጸም ወይም የማስፈጸም ግዴታ ይኖርበታል የሚለው ሀረግ ይፈፅማል በሚል ቃል እንዲተካ ተደርጓል።

ምክንያቱም ትብብራዊ አሰራርን በሚያመለክት አግባብ ለማስቀመጥ ነው።

5.84. በረቂቅ ህጉ አንቀፅ 76(1)(ለ) በተሸጋሸገው 75(1)(ለ) ላይ ያለው ፍተሻ የሚለዉ ቃል ብርበራ በሚል ቃል ተተክቷል።

ምክንያቱም ተገቢ የሆነዉ የሕግ ቃል ብርበራ ስለሆነ ነው።

5.85. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 76 **በተስተካከለው** አንቀፅ 75 (1)(ሸ) ላይ ከተጠርጣሪ ቃል መቀበል ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ እና መሰል ተግባራትን በመፈጸም የሚል ሀረግ ተጨምሯል።

**ምክንያቱም** የወንጀል ምርመራ ስራ የሚባሉት በቀጣይ ሌሎች ተጨማሪ የሚደረጉ ካሉ እነሱን ለማካተት ነው።

5.86. በረቂቅ ህጉ አንቀፅ 76(2) በተሸጋሸገው 75(2) ላይ ያለው መረጃ እና የሚለው ቃል እንዲወጣ ተደርጓል።

ምክንያቱም መረጃ ምርመራ ለማስጀመር በቂ ስላልሆነ ነው።

5.87. በረቂቅ ህጉ አንቀፅ 77/2/ በተስተካከለው አንቀፅ 76/2/ ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀፅ 3 ተጨምራል።

76(3) በኃይል አጠቃቀም ወቅት ጥንቃቄ የማድረግ፣የሕጋዊነት፣አድሎ ያለማድረግ መርሆችን ያከበረ መሆን ይኖርበታል።

ምክንያቱም የኃይል አጠቃቀምን ከተመጣጣኝነት መርህ አንፃር የተወሰኑትን ማመላከት አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

5.88. የረቂቅ ህጉ አንቀፅ 79 (2) (ሀ) በተሸጋሸገው 78(2)(ሀ) ሙሉ ስም ከሚለው ቀጥሎ አድራሻ የሚል ተካቷል።

ምክንያቱም መጥሪያው አድራሻውን መያዝ ስላለበት ነው።

5.89. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 80(2) በተሸጋሸገው 79(2) መጨረሻ ላይ ያለው "ይቻላል" የሚል ቃል ተሰርዞ "ይችላል" በሚል ቃል ተተክቷል። እንዲሁም በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 80(3)(ለ) በተሸጋሸገው 79(3) (ለ) ላይ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተፈፀመበት ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ወይም ዖታዊ ጥቃት የተፈጸመበት የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል። እንዲሁም ንዑስ 4(ሐ) ላይ ተነቦለት ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ወይም አንብቦ የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል።

ምክንያቱም ዖታዊ ጥቃትንም ማካተት አስፈላጊ በመሆኑ እና ማንበብ የሚችል ሰው ከሆነ ራሱ እንዲያነበው ሊደረግ ይችላል።

5.90. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 81 በተሸጋሸገው 80 ላይ ርእሱ የተከለከለ ተግባር በሚል ተስተካክሏል። እንዲሁም የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጨመረ ሲሆን ቀድሞ የነበረው ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ 2 ሆኖ ቀጥሏል።

80(1) መርማሪ ፖሊስ የምስክርነት ቃል በሚቀበልበት ጊዜ ዛቻ፣ ማታለያ፣የተስፋ ቃል ፣ ኃይል ፣ ማስገደድ እና ሌላ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሰል ተግባራትን መፈፀም የለበትም።

ምክንያቱም መርማሪ ፖሊስ ቃል በሚቀበልበት ጊዜ ማድረግ የሌለበትን ተግባራት በዝርዝር ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

5.91. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 82 በተሸጋሸገው 81 ላይ ርእሱ ላይ ያለው እቃ የሚለው ማስረጃ በሚል ቃል ተተክቷል። በንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የሚያዘውን እቃ ከሚለው ቀጥሎ ወይም ዳታ የሚለው ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል፣ በንዑስ አንቀፅ 4 መጨረሻ ላይ ያካትታል የሚል ቃል እንዲገባ ተደርጓልእንዲሁም የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 6 እንዲገባ ተደርጓል።

**81(6)** ፍርድ ቤቱ የሠጠው የብርበራ ትዕዛዝ በስህተት መሆኑን ሲረዳ ወይም በማንኛውም ወገን አቤቱታ ሲቀርብለት ሊሰርዘው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል።

ምክንያቱም በብርበራ ሂደት የተሰጠው ትዕዛዝ ስህተት ሲሆን ለማረም የሚቻልበት ስርአት ለመዘርጋት ነው።

5.92. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 84(1) በተሸጋሸገው 83(1) ላይ ደህንነቱን በማይጎዳ ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ እና ሰብዓዊ ክብሩን በማይነካ የሚል ሀረግ ተጨምሯል።

ምክንያቱም ለሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ትኩረት ለመስጠት ነው።

5.93. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 85(4)፣(5) እና (6) በተሸጋሸገው 84(4)፣(5) እና (6) በሚከተለው መልኩ ተስተካክለው ቀርበዋል።

84(4) መርማሪው የተያዘውን ዕቃ ትክክለኛነት ከሁለት ባላነሱ ምስክሮች ፊርማ እንዲረጋገጥ ያደርጋል። የሚቻል እንደሆነም የብርበራው ሂደት በምስልና በድምፅ ተቀርፆ ይቀመጣል።

84(5) መርማሪ ፖሊስ የተያዘውን ዕቃ ዝርዝር ባለመብቱ እንዲፈርምበት እና ደረሰኝ እንዲሰጠው ያደርጋል። ባለመብቱ ለመፈረም ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ወይም ከሌለ ይኸው ይመዘገባል።

84(6) መርማሪ ፖሊስ ከተያዙት ዕቃዎች ለማስረጃነት የሚያስፈልጉትን ይይዛል፤ ለማስረጃነት የማያስፈልጉትን ለተወሰደበት ሰው አስፈርሞ ይመልሳል።

ምክንያቱም ንዑስ አንቀፆቹ የግልፅነት ችግር ስለነበረባቸውና የጎደሉ ጉዳዮችም ስለነበሩ የተሟሉ ለማደረግ ነው።

5.94. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 87 በተስተካከለው 86 ንዑስ አንቀጽ 5 ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል።

አንቀፅ **86(5) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ቢኖርም** መርማሪ ፖሊስ በብርበራ እንዲያዝ የተፈለገውን የኮምፒዩተር ዳታ የብርበራ ፈቃድ በወጣበት የኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት ሊገኝ በሚችል ሌላ የኮምፒዩተር

ሥርዓት ውስጥ የተከማቸ መሆኑን በበቂ ምክንያት ሲያምን ለፍርድ ቤት በማሳወቅ የብርበራ ሥራውን ማከናወን ይችላል፡፡

ምክንያቱም ዘመኑ የደረሰበት ቴክኖሎጂ እጅግ ሠፊ እና የተራቀቀ ከመሆኑ አንፃር አንድ ኮምፒውተር ለመበርበር ፈቃድ አግኝቶ ነገር ግን የሚፈለገው ማስረጃ በአይክላውድ ወይም መሠል የዳታ ማከማቻ ነገሮች ቢገኝ ወዲያውኑ መያዝ እንዲቻል ነው፡፡

5.95. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 88 በተሸጋሸው 87 እንደሚከተለው ተስተካክሏል፡፡

መርማሪ ፖሊስ በዚህ ህግ መሰረት በተደረገ ብርበራ እንዲያዝ ከተፈለገው እቃ ውጭ በግለሰብ እጅ እንዲያዝ ያልተፈቀደ እቃ ያገኘ እንደሆነ ወይም ይኸው እቃ ለህዝብ ጤንነት ወይም ደህንነት አደገኛ መሆኑን ከተረዳ መያዝ ይችላል፡፡

ምክንያቱም በግለሰብ እጅ እንዲገባ ያልተፈቀደ እቃ መያዝ በራሱ ወንጀል በመሆኑ እና እቃውም ለህዝብ ደህንነት አደገኛ መሆኑ በራሱ ለመያዝ በቂ ስለሆነ ነው፡፡

5.96. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 90(4) በተስተካከለው 89/4/ በሚከተለው መልኩ ተስተካክላል፡፡

89(4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት የኢግዚቢቱን ባለቤት ወይም ባለይዞታ ማን እንደሆነ ማወቅ የማይቻል እንደሆነ ጉዳዩ በፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ክርክር ይወሰናል፡፡

ምክንያቱም ጉዳዩን ወደ ፍትሐብሔር ችሎት የሚወሰደው ዐቃቤ ሕግ ላይሆን ይችላል፤ በንብረቱ ላይ ጥቅም አለን ወይም ባለቤት ነኝ የሚል ሰው መውሰድ እንዲችል ለመፍቀድ ነው፡፡

5.97. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 91(1) በተሸጋሸገው 90(1) መጨረሻ ላይ ያለው ትዕዛዝ ይሰጣል የሚለው ሀረግ ተሰርዞ ሊጠይቅ ይችላል የሚል ሀረግ ተጨምሯል፡፡

ምክንያቱም ትክክለኛው አገላለፅ ይህ ስለሆነ ነው፡፡

5.98. በረቂቅ ህጉ አንቀፅ 92(1) በተሸጋሸገው 91(1) መጨረሻ ላይ ያለው ይጠይቃል የሚለዉ ሀረግ ተሰርዞ ሊጠይቅ ይችላል በሚል ሀረግ፣ እንዲሁም በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መጨረሻ ላይ ያለው መስጠት ይኖርበታል የሚለው ሀረግ ተሰርዞ ይሰጣል የሚል ቃል የገባ ሲሆን፣ በዚሁ አንቀፅ መጨረሻ ላይ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 3 እንዲጨመር ተደርጓል፡፡

91(3) ተቋሙ ማስረጃውን ለማስረከብ ፈቃደኛ ካልሆነ መርማሪ ፖሊስ ማስረጃው እንዲሰጠው እንዲታዘዝለት ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

ምክንያቱም ፖሊስ የሚመለከታቸው አካላት ማስረጃ እንዲሰጡት ሲጠይቅ በትብብር እንዲሆንና ካልተባበሩ በፍርድ ቤት የሚያስገድድበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው፡፡

5.99. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 93 በተስተካከለው አንቀፅ 92 በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል፡፡

<u>አንቀጽ 92 በፋይናንስ ተቋም ወይም በባንክ የሚገኝ ማስረጃ</u>

1. በፋይናንስ ተቋም ወይም በባንክ የሚገኙ በማስረጃነት የሚፈለግ የባንክ ሂሳብ ወይም የገንዘብ እንቅስቃሴን የሚመለከት መግለጫ እዲሰጥ ጉዳዩን የሚከታተለው ዐቃቤ ሕግ የስራ ክፍል ሀላፊ ትእዛዝ መስጠት ይችላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚሰጥ ትእዛዝ፣

   (ሀ) የተጠርጣሪን ሙሉ ስም እና አድራሻ፣

   (ለ) ተጠርጣሪው ፈጸመ የተባለው የወንጀል ድርጊት፣

   (ሐ) ከፋይናንስ ተቋም ወይም ከባንኩ የሚፈለግ ማስረጃ፣

   (መ) ትእዛዙን የሚፈጽመው ወይም የሚያስፈጽመው ዐቃቤ ሕግ ስም፤

   መያዝ ይኖርበታል።

   ምክንያቱም በባንክ አሰራር እጅ መሰረት በህግ መረጃ ወይም መስረጃ የሚጠይቅ አካል ከባንክ መረጃ ለመጠየቅ በሕግ ስልጣን የተሰጠው መሆን አለበት ስለሚል ባንክ የሚለውን ቃል ለመጠቀም እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት በወንጀል የተገኘ ንብረትን በተመለከተ የመከታተል እና የማስመለስ ሀላፊነት የዐቃቤ ሕግ ስልጣን መሆኑ በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ እና ከፋይናንስ ጋር የተገናኘ ምርመራ ከንብረት ማስመለስ ስራ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ በመሆኑ ሕጎቹ የተናበቡ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

5.100. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 95(2)(መ) በተሸጋሸገው 94(2)(መ) ድንጋጌ በሚከተለው መልኩ ተስተካክሎ ቀርቧል።

94(2)(መ) ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች አስፈላጊውን ጥበቃ እንዲያገኙ ማድረግ እና ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ያከናውናል።

ምክንያቱም ጥበቃ ማድረግም አንዱ ተግባር መሆኑን ለማመልከት ነው።

5.101. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 96(1) በተሸጋሸገው 95(1) ላይ የሞተ ሰው ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ያለው አካል የሚለው ቃል አስከሬን በሚል ቃል እንዲተካ ተደርጓል።

ምክንያቱም ትክክለኛው ቃል አስከሬን በመሆኑ ነው።

5.102. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 96 በተሸጋሸገው 95 ከንዑስ አንቀፅ 4 እስከ 7 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሙሉ በሙሉ እንዲሰረዙ ተደርጎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 4 ገብቷል።

95(4) ወንጀል በተፈፀመበት ቦታ የሚገኝ ማንኛውንም የኤሌክትሮኒክ ዳታ የያዘ ግለሰብ ወይም ተቋም ዳታው ለአንድ ወር ተጠብቆ እንዲቆይ መርማሪ ፖሊስ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

ምክንያቱም ንዑስ ድንጋጌዎቹ አስፈላጊ ስላልሆኑና የኤሌክትሮኒክ ማስረጃን በተመለከተ እንዴት ማቆየት እንደሚቻል መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

5.103. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 97 በተስተካከለው አንቀፅ 96 ላይ ርዕሱ ላይ ያለው የሞተ ሰዉ አካልን የሚለዉ ሀረግ ተሰርዞ አስከሬን በሚል ቃል፣ በንዑስ አንቀፅ 1 ላይ ያለው አካሉ የሚለው ቃል አስከሬኑ በሚል ቃል፣ በንዑስ አንቀፅ 2 ላይ ያለው የሞተ ሰው አካል የሚለው ሀረግ በአስከሬን በሚል ቃል እንዲሁም በንዑስ አንቀፅ 3 ላይ ያለው የተመረመረው አካል የሚለው የአስከሬኑ በሚል ሀረግ እንዲተካ ተደርጓል።

ምክንያቱም ትክክለኛው ቃል አስከሬን የሚለው በመሆኑ ነው።

5.104. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 100 በተስተካከለው አንቀፅ 99(3) መጨረሻ ላይ ያለው ቀርቦ ይመሰክራል የሚለው ሀረግ ቀርቦ መመስከሩ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ እንዲመሰክር ይደረጋል በሚል ሀረግ እንዲተካ ተደርጓል፤

ምክንያቱም የሙያ ምስክር በፅሑፍ ከሚሰጠው የሙያ ምስክርነት በተጨማሪ ሁልጊዜ ችሎት ላይ ቀርቦ መመስከር ላያስፈልገው ይችላል።

5.105. በረቂቅ ህጉ አንቀፅ 101 በተስተካከለው 100 ላይ ያለው ድንጋጌ አብዛኛዎቹን የድንጋጌውን ይዘቶች ወደ ሚቀጥለው አዲስ አንቀፅ በመውሰድ በሚከተለው መልኩ ተስተካክሎ ቀርቧል።

<u>አንቀጽ **100** ዓላማ</u>

የልዩ ወንጀል ምርመራ ዘዴ ዓላማ በመደበኛው የምርመራ ዘዴ ማስረጃ ማሰባሰብ ባልተቻለባቸው የወንጀል ዓይነቶች ምርመራውን መርዳት ነው።

ምክንያቱም ድንጋጌው ዓላማውን ብቻ መያዝ ስላለበት ነው።

5.106. ከረቂቅ ህጉ አንቀፅ 101 ከተሸጋሸገው አንቀፅ 100 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀፅ 101 ሆኖ የገባ ሲሆን በነባሩ አንቀፅ 102 የነበረው እንዳለ 102 ሆኖ ቀጥሏል።

<u>አንቀጽ **101** የልዩ የምርመራ ዘዴዎች ተፈፃሚነት</u>

ልዩ የምርመራ ዘዴ ተፈፃሚ የሚሆነው የተደራጁ ወንጀሎች፣ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች፣የሽብር ወንጀል፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትና ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር ወንጀል፣በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል፣ የሙስና ወንጀል፣ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል፣ የኮምፒውተር ወንጀሎች፣ የቤት ውስጥ ጥቃቶች፣ አስገድዶ መድፈር እና የጉልበት ብዝበዛ ወንጀሎች ላይ ነው።

ምክንያቱም ልዩ ምርመራ ዘዴዎች በምን የወንጀል አይነቶች ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በግልፅ ለማመልከት እና የወንጀሉ ባህሪ ውስብስብ በመሆኑ መደበኛ የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ በመጠቀም ብቻ ማስረጃ ማሰባሰብ ስለማይቻል ነው።

5.107. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 102 እንደሚከተለው ተሸሽሏል።

1. የልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃ ማሰባሰብ የሚቻለው ወንጀሉ በሰንጠረዡ በተመለከተው ወንጀሉን የማየት ስልጣን ያለው ፍ/ቤቶች በዚህ አንቀጽ 100 ለይ የተገለፀውን አላማ ያሳካል ብሎ ሲያምን እና ሲፈቅድ ነው።
2. ልዩ የምርመራ ዘዴ ሂደት ሚስጥራዊነት የተጠበቀ ይሆናል።

ምክንያቱም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወይም የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብቻ ሳይሆን ሌሎች በጉዳዩ ላይ ስልጣን ያላቸውን ፍ/ቤቶች ለማካተት ነው። እንዲሁም ሂደቱ ውስብስብ እና በባህሪው አስቸጋሪ እንዲሁም ከህዝቡ ሞራል ጋር የሚቃረኑ ጉዳዮች ሊይዝ ስሚችል ማስረጃዎች በሚስጥር እንዲያዙ ለማድረግ ነው።

5.108. በረቂቁ አንቀጽ 103 (1) መጨረሻ ላይ እና ከትትል በማድረግ የሚል ሀረግ የተጨመረ ሲሆን በንዑስ አንቀፅ 3 መጨረሻ ላይ ወይም የሚል ቃል ተጨምሯል። እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀፅ 5 ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል።

**103(5) ሕገወጥ ዕቃን ወይም ተጠርጣሪን ወደ አንድ የተከለከለ ቦታ ወይም ድንበር መግባትን እና መውጣትን መከታተል** በምስልና ድምፅ በመቅረጽ፣

ምክንያቱም የኮንትሮባንድ ጉዳዮችን ለመከታተል በግልፅ መደንገግ ስለሚያስፈልግና አንቀፁ የተሟላ እንዲሆን ነው፡

5.109. በረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 105 /1/ ላይ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሁለት ወር የነበረው ከሦስት ወር በሚል ተስተካክሏል። እዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ አንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል የሚለው አንድ ወር የሚለው ሦስት ወር በሚል ተተክቷል። በተጨማሪም እዚሁ አንቀጽ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል።

አንቀፅ **105 /3/** በዚህ አንቀጽ መሠረት ለልዩ ማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የሚፈቀድ የጊዜ ገደብ ከአስራሁለት ወራት ሊበልጥ አይችልም'።

***ምክንያቱም*** በልዩ ምርመራ ዘዴ የሚመረመሩ ወንጀሎች ውስብስብ በመሆናቸው እና በሥነሥርዓት ሕጉ እንደ አዲስ እየተዋወቀ ስለሆነ ምርመራውን በአጭር ጊዜ ማጠናቀቅ ሥለማይቻል ነው።

5.110. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 109 (1) እንደሚከተለው ተስተካክሏል። መርማሪ ፖሊስ ወንጀል ስለመፈፀሙ በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው ተጠርጣሪው በምርመራ ቦታ እንዲቀርብ በፅሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴ ሊጠራው ይችላል።

ምክንያቱም አመቺ በሆነ በማንኛውም መንገድ መባሉ አሻሚ ስለሆነ ነው።

5.111. በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 110 (2) ሁለተኛው መስመር ላይ ያለው የግድ የሚለው ቃል እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን፣ በአንቀፁ ላይ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 6 እንዲጨመር ተደርጓል።

አንቀጽ **110(6)** ፍርድቤቱ የተሠጠው የመያዣ ትእዛዝ በስህተት መሆኑን ሲረዳ ወይም በማንኛውም ወገን አቤቱታ ሲቀርብለት ሊሰርዘው ይችላል።

ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ የመያዣ ትእዛዝን በተመለከተ የበለጠ ስልጣን እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

5.112. በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 111(1) ሁለተኛው መስመር ላይ በስልክ ከሚለው ቃል ቀጥሎ ያለው ነጠላ ሰረዙ እንዲሰረዝ ተደርጎ ወይም የሚል አያያዥ የተጨመረ ሲሆን በሶስተኛው መስመር ላይ በአቅራቢያው ከሚለው ቃል ቀጥሎ ያለው ያለን የሚለው ቃል ተሰርዞ ለሚገኝ በሚል ቃል ተተክቷል።

ምክንያቱም ድንጋጌው የሰዋሰው ችግር ስለነበረበት ነው።

5.108 በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 111(2) አስቸኳይ ሁኔታ አንቀጽ (የሚጠየቅ) 24 ሰአት የተባለው 48 ሰአት በሚል ተሸሽሏል። ምክንያቱም የተያዘው በስራ ቀን ባልሆነ ጊዜ ሲሆን በ 24 ሰዓት ብቻ መገደብ በቂ ጊዜ ስላልሆነ ነው።

5.109 በረቂቁ ህጉ አንቀጽ 112/2/ ድንጋጌ ላይ ያለው ተጠርጣሪ ከሚለው ቃል ቀጥሎ ያለው በፖሊስ የሚለው ቃል እንዲወጣ ተደርጓል።

ምክንያቱም ማንኛውም ሰው በማህበረሰቡም በባለጉዳዩ አቤቱታ እጅ ከፍንጅ ወንጀል ሲኖርበት እንዲያዝ በፖሊስ ብቻ እንዳይገደብ ነው።

5.110 በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 114 (1) አስቀድሞ ማረጋገጥና ከሚለው ቀጥሎ የተያዘበትን ምክንያት ወዲያውኑ መንገር የሚል ተጨምሯል።

ምክንያቱም ተጠርጣሪው ለምን እንደተያዘ የማወቅ መብት ስላለው ነው፣

5.111 በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 114 ላይ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 2 የተጨመረ ሲሆን ንዑስ አንቀፆቹ እስከ 5 በመሆን እንደ ቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል።

**114(2**) ፖሊስ ለሚያዘው ሰው ያለመናገር መብት እንዳለው፣ በፈቃደኝነት የሚሰጠው ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል፣ጠበቃ ማቆም መብት እንዳለውና ጠበቃ ለማቆም አቅም የሌለው እንደሆነ መንግስት ጠበቃ እንደሚያቆምለት መንገር ይኖርበታል።

ምክንያቱም የዚህ ድንጋጌ መግባት ሕገ-መንግስቱን ለማስፈጸም ስለሚያስችል ነው።

5.112 በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 115(2) ላይ ድንጋጌው መጀመሪያ ላይ ያለው በፍትሐብሔር ሕግ በቁጥር 20 የተመለከተው ቢኖርም የሚለው ሀረግ እንዲሰረዝ ተደርጓል። እንዲሁም ተከሳሹ የሚለው ቃል ተጠርጣሪው በሚል ቃል፣ የተከሰሰበትን የሚለው ቃል የተጠረጠረበትን በሚል ቃል ተመልክቶ ከሚለው ቀጥሎ ተከሳሹ የሚለው ተጠርጣሪ በሚል ቃል እንዲተካ የተደረገ ሲሆን መሆኑን ከተረዳ ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ያለው የማከም የሚለው ቃል እንዲወጣ ተደርጓል።

ምክንያቱም የፍትሐብሔር ሕጉን መጥቀስ ለወንጀል ጉዳይ አስፈላጊ ባለመሆኑና ድንጋጌው የሚያወራው ስለተከሳሽ ሳይሆን ስለተጠርጣሪ በመሆኑ ነው።

5.113 በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 116(2) ላይ ያለው "ነጻ እንደሆነና" የሚለዉ ሀረግ ተሰርዞ "እንደማይገደድ" በሚል ቃል እንዲተካ ተደርጓል።

ምክንያቱም ትክክለኛው አገላለፅ ይህ በመሆኑ ነው።

5.114 በረቂቅ ሕጉ 116 (6) በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል።

116(6) መርማሪ ፖሊስ በተጠርጣሪው የተሰጠውን ቃል ብቻ ይመዘግባል፣ይህንንም መርማሪው ለተጠርጣሪው ተነቦለት ወይም አንብቦ እንዲፈረም ያደርጋል፣ተጠርጣሪው ለመፈረም ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ይህንኑ በመዝገብ ላይ ያሰፍራል።

ምክንያቱም ተጠርጣሪው ማንበብ የሚችል ከሆነ የሰጠውን ቃል ሊያነብ የሚችል ስለመሆኑ እና መርማሪውን ሲያነብለት እንደሚገባ ለማመልከት ነው።

5.115 አንቀጽ 116(7) እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

አንቀጽ 116(7) ተጠርጣሪው ቃሉን በማቆያ ቤት የምርመራ ክፍል ወይም ወንጀሉ በተፈፀመበት ቦታ ሊሰጥ ይችላል። ተጠርጣሪው ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ ጠበቃው በምርመራ ክፍሉ በመገኘት ተገቢውን የህግ ምክር አገልግሎት መስጠት ይችላል።

ምክንያቱም የተጠርጣሪውን በጠበቃ የመወከልና የህግ ሙያተኛ ምክር የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብቱ ለማስጠበቅ ነው።

5.116 በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 117(1) መነሻው ላይ ያለው ከዚህ በታች የሚለው ሀረግ ተሰርዟል፤

ምክንያቱም ሀረጉ አስፈላጊ ስላልሆነና የሚጨምረው ነገር ስለሌለ ነው።

5.117. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 117(2) አዲስ ንኡስ አንቀጽ (3) ተጨምሯል። የነባሩ ንዑስ አንቀፅ 3 እና ሌሎቹ እንደቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽጓል።

117(3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 እንደተጠበቀ ሆኖ ተፈጸመ የተባለው ወንጀል በሴቶችና ሕጻናት ላይ ከሆነ የዋስትና ጉዳይ የሚታየው በፍርድ ቤት ነው።

ምክንያቱም የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ትኩረት ስለሚሻ እና በሴቶችና ሕጻናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ካሉ ተጠርጣሪው በፖሊስ ዋስትና ከሚወጣ በፍርድ ቤት ዋስትና ቢወጣ ተገቢ ስለሚሆን ነው።

5.118. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 120 ላይ ያሉት ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 በአዲስ መልክ ተስተካክለው ቀርበዋል።

120(1) በአንቀጽ 119 በተቀመጠው ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ውስጥ የወንጀል ምርመራው ካልተጠናቀቀ ፍርድ ቤት ተጠርጣሪውን በዋስትና ይለቀዋል፤ ምርመራውም ይቀጥላል።

120(2) የወንጀል ምርመራው በተሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ካልተጠናቀቀ ፍርድ ቤት ከወንጀል ድርጊት መፈጸም ጋር በተያያዘ የታገደ ወይም የተያዘ ንብረት ሲኖር ተገቢ ነው ያለውን ትእዛዝ ይሰጣል።

ምክንያቱም ድንጋጌዎቹ ምርመራው በሕጉ የጊዜ ገደብ ካልተጠናቀቀ ተጠርጣሪዉ በዋስትና ሆኖ ምርመራው እንደሚቀጥል ማመልከት አግባብ በመሆኑ ነው።

5.119. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 120 /4/ ይመለስለታል ከሚለው ቀጥሎ ካለው ድርብ ሰረዝ በኋላ የዐቃቤ ሕግን አስተያየት በመጠየቅ የተጣለ እግድ ካለም ሊነሳ ይችላል። በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም እግዱ የማይነሳበት አግባብ ካለ ዐቃቤ ሕግ እንዲያስረዳ እድል ለመስጠት ነው።

5.120. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 121(2) ላይ በማረፊያ የሚለው በማቆያ በሚል ቃል እንዲተካ ተደርጓል። የትዳር ጓደኛውን ከሚለው ቃል ቀጥሎ ልጆቹን የሚል ቃል፣ ጓደኛውን የሚለው ቃል የቅርብ ጓደኛውን በሚል ቃል፣ የኃይማኖት አማካሪውን የሚለው ሀረግ የኃይማኖት አባቱን ወይም መሪውን በሚል ሀረግ እንዲተኩ ተደርጓል፡

ምክንያቱም  የተጠርጣሪዎችን  መብት ያከበረ እንዲሆን ለማድረግ ታስቦ ነው።

5.121. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 122 በንዑስ  /2/ መጨረሻ ላይ ያለው መመዝገብ ይኖርበታል የሚለው ሀረግ ተሰርዞ ያሰፍራል በሚል ቃል ተተክቷል። በንዑስ  (3) መጨረሻ ላይ ያለው አይኖርበትም የሚለው ቃል ተሰርዞ የለበትም በሚል ቃል እንዲተካ ተደርጓል። በንዑስ አንቀፅ (4) መጨረሻ ላይ ያለው ዳኛው ይፈርምበታል የሚለው ሀረግ ተሰርዞ በዳኛዉ ይፈረማል በሚል ሀረግ ተተክቷል። በንዑስ አንቀፅ 5 መጀመሪያ ላይ ያለው መርማሪ ፖሊስ የሚለው እንዲወጣ ተደርጓል፣ መጨረሻ ላይ ያለው ይልክለታል የሚለው ቃል ይላክለታል በሚል ቃል ተተክቷል።

ምክንያቱም የንብረት አስተዳደርን በተመለከተ በረቂቁ ስላልተካተተና ትክክለኛው የንዑስ አንቀፆቹ መደምደሚያ በዚህ መልኩ መሆን ስላለበት ነው።

5.122. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 122 ቀጥሎ ያለው ምዕራፍ ሦስት እና ከምዕራፍ 3 በታች  “የንብረት እግድ እና አስተዳደር የሚለው ርዕስ ተሰርዞ  ክፍል አንድ "ክፍል 7 በሚል ተሻሽሎ ርዕሱ “የንብረት እግድ እና አስተዳደር በሚለው ተስተካክሏል።እንዲሁም ሌሎች ምዕራፎች እንደቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል።

ምክንያቱም በአንቀጽ 123 ጀምሮ ስለ ንብረት እግድ ብቻ ሳይሆን ስለንብረት አስተዳደርም የሚደነግግ በመሆኑ ርእሱ ይህነን ማካተት ስላለበት ነው።

5.123. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 123 /1/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

123(1) ተፈጽሟል ከተባለው ወንጀል ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውም በሀገር ውስጥ እና በውጪ ሀገር የሚገኝ ንብረት ወይም ገንዘብ ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑ ባይረጋገጥም ተከሳሽ ያገኘው የማይገባ ጥቅም ወይም ያደረሰው ጉዳት ስለመኖሩ ሲረጋገጥ ከተገኘው የማይገባ ጥቅም ወይም ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ በተከሳሽ፣በትዳር ጓደኛው ወይም ከአስራ ስምንት አመት በታች በሆነ ልጁ ስም የሚገኝ ንብረት በፍርድ ቤት ትእዛዝ መሰረት ሊታገድ፣ሊያዝ እና አግባብነት ባለው አካል ሊተዳደር ይችላል።

ምክንያቱም በወንጀል የተገኘ ሀብት ሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ ሀገርም ስለሚደበቅ እና በሌሎች ሀገር የተደበቀ ንብረቶችን ማስመለስ እንዲቻል ለማድረግ እና የማካካሽ ውርስ በአዋጅ ቁጥር 882 መሰረት የተደነገገ ሲሆን ይህ ስነስርዐት ሕግ ሲወጣ የአዋጁ ድንጋጌዎች የሚሻሩ በመሆኑ በዚህ ሕግ ውስጥ ማካተት አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

5.124. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 123/2/ መጨረሻ ላይ ያለው ሊታገድ የሚለው ቃል ሊያዝ ወይም በንብረት አስተዳደር ስር ሊቆይ ይችላል በሚል ተተክቷል።

**ምክንያቱም** ሊታገዱ ስለሚችሉ ንብረቶች በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ ሲሆን በንዑስ አንቀፅ 2 የተቀመጡት በወንጀል ሕጉ መሰረት ሊያዙ የሚችሉ በመሆኑ ነው።

5.125. በረቂቅ ሕጉ  123 ላይ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፅ 5፣6 እና 7 ተጨምረዋል።

123(5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 መሠረት ንብረት የሚያዘው የንብረቱን መወረስ በሚመለከት የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ንብረቱን ከመጥፋት፣ ከመበላሸት፣ ለሌላ ወገን ከመተላለፍ

ለመጠበቅና ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በወንጀሉ ባገኘው ንብረት እንዳይጠቀም ወይም ተጨማሪ ወንጀል እንዳይፈጽም ለመከላከል የዕግድ ትዕዛዝ ብቻ በቂ በማይሆንበት ጊዜ ነው፤

123(6) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ፍርድ ቤት የንብረት አስተዳደር እንዲሾም ትእዛዝ የሚሰጠው በራሱ ተነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ሕግ ወይም በተጠርጣሪው ወይም በንብረቱ ላይ መብት አለኝ በሚል ሶስተኛ ወገን ጠያቂነት በዚህ ሕግ መሰረት የተያዘ ንብረት በንብረት አስተዳደሪ ስር እንዲቆይ በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት ከወንጀሉ ባህሪ እና ከንብረቱ አጠቃላይ ሁኔታ አንጻር የንብረት አስተዳደር መሾም ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን ነው።

123(7) ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል የንብረት አስተዳዳሪ ሆኖ ሊሾም ይችላል፤ ፍርድቤት የንብረት አስተዳዳሪ ሲሾም በማናቸውም ሁኔታ የጥቅም ግጭት የሌለ ስለመሆኑ እና የተሻለ አማራጭ ስለመኖሩ ያረጋግጣል፤ በዚህም ጉዳይ የዐቃቤ ህግን እና የንብረቱ ባለ መብቶችን አስተያየት መስማት አለበት።

**ምክንያቱም** በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ ፍርድ ቤት አንድን ከወንጀል ጋር ግንኙነት አለው ተብሎ የሚታመንን ንብረት እንዲያዝ ወይም እንዲተዳደር ሊወስን የሚችል መሆኑ የተደነገገ ቢሆንም እንዴት እንደሚያዝ ወይም አስተዳደርን በተመለከተ ምንም ድንጋጌ ስላልተካተተ ቢያንስ እነዚህን መሰረታዊ ድንጋጌዎች ማካተት አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

5.126. በረቂቅ ሕጉ 124(1)ወይም መርማሪ ፖሊስ የሚለው ተሰርዟል ።

ምክንያቱም ንብረቱን የመያዝ ሥልጣን ለፖሊስ የተሰጠ ሲሆን ነገር ግን እንዲታገድ የሚፈለገው ንብረት ተፈጽሟል ከተባለው ወንጀል ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት ያለው እንዲሁም በዚህ ሕግ እና በሌሎች ሕጎች መሰረት ሊታገድ የሚችል መሆኑን እንዲሁም በዚህ ሕግ እና በሌሎች በርካታ የሕግ ጉዳዩች ማጤን ስለሚያስፈልግ ነው።

5.127. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 125(3) ላይ የንብረቱ ዝርዝር ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ወይም የገንዘብ መጠን የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል።

ምክንያቱም ገንዘብም የንብረት አይነት በመሆኑ መካተት ስላለበት ነው።

5.128. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 126 ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ ያለው መርማሪ ፖሊስ የሚለው ዐቃቤ ህግ በሚል እንዲተካ ተደርጎ የሚከተለው ንኡስ 4 ተጨምሯል።

126(4) ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የፍርድ ቤቱን የእግድ ትዕዛዝ የጣሰ ወይም የእግዱን አላማ በሚያደናቅፍ መልኩ በታገደው ንብረት ላይ ጉዳት ወይም ለውጥ የሚያስከትል ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ ንብረቱ በዚህ ሕግ መሰረት ይያዛል፤

ምክንያቱም የንብረት ጉዳይን የመከታተል ሀላፊነት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት ለዐቃቤ ህግ የተሰጠ ሀላፊነት በመሆኑ ህጋዊና የተናበበ እንዲሆን ለማድረግ እና ንብረቶች ከታገዱ በኋላ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ወይም እንዳይባክኑ ለመከላከል ነው።

5.129. የረቂቅ ሕጉ  አንቀጽ 128 ቀሪ ከሚለው ቃል ቀጥሎ ሊያደርግ ይችላል የሚለው ሀረግ ተሰርዞ ያደርጋል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም በፍቃድ መልኩ ተደንግጎ ስለነበረ እሱን አስገዳጅ ለማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

5.130. የረቂቅ ሕጉ  አንቀጽ 131 ንዑስ /2/ የመጀመሪያ የሚለው ሀረግ የወረዳ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም በስህተት የተዘለለ ስለሆነ እና የፍርድ ቤቱ ሙሉ ስም መገለፅ ስላለበት ነው።

5.131. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 138  ንዑስ 2 እና 3 ሆነው የሚከተሉት ንዑስ አንቀፆች ተጨምረዋል። በዚሁ አግደባብ ንዑስ አንቀፆቹ ተሸጋሽገዋል።

**138(2)** በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው የተጠረጠበት ወይም የተከሰሰበት ወንጀል የሞት ቅጣትን የሚያስከትል እንደሆነ የዋስትና መብት አይፈቀድም።

**138(3)** በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው የተጠረጠበት ወይም የተከሰሰበት ወንጀል አሥራ አምስት ዓመት ወይም በላይ የሆነ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ከሆነ እና ወንጀል የተፈጸመበት ሰው በደረሰበት ጉዳት ሊሞት እንደሚችል አጠራጠሪ ከሆነ የዋስትና መብት አይፈቀድም።

ምክንያቱም አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ዋስትናን በህግ በተቀመጡ ጉዳዮች መሰረት ማስቀመጡ አሁን ላለው የፍትህ ስርአት  ስለሚጠቅም ነው።

5.132. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 138/2/ በተሸጋሸገው 138(4) የዋስትና ማረጋገጫ እንዲያቀርብ ከሚለው ቃል ተከትሎ እና ሌሎች የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚል ተጨምሯል።

ምክንያቱም በዋስትና ክፍሉ የጥንቃቄ እርምጃዎች አንዱ የዋስትና ዓይነት ሆኖ ስለተደነገገ ነው።

5.133. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 139 እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

<u>አንቀጽ 139 ዋስትና በፍርድ ቤት ስለሚከለከልበት ሁኔታ</u>

1. ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በዋስትና ቢለቀቅ ፤-

ሀ/ በተፈለገ ጊዜ እና ቦታ ሊቀርብ አይችልም ብሎ ሲያምን፣

ለ/ በማናቸውም ምክንያት ማስረጃን ያጠፋል፣ያበላሻል ወይም እውነተኛ ምስክርነት እንዳይሰጥ ያደርጋል ብሎ ሲያምን ፣

ሐ/ ሌላ ወንጀል ይፈጽማል ብሎ ሲያምን ዋስትና ሊከለክል ይችላል።

2. / ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀፅ መሠረት ለመወሰን ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ

ሀ/ በተደጋጋሚ በፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል የፈፀመ ከሆነ፣

ለ/ ከዚህ ቀደም የገባውን የዋስትና ግዴታ ያለበቂ ምክንያት በተደጋጋሚ ያላከበረ መሆኑ፣

ሐ/ ቋሚ አድራሻ የሌለው መሆኑ፣

መ/ የተፈፀመው ወንጀል የፆታ ጥቃትን የሚመለከት ሆኖ የወንጀሉን አፈፃፀም አፀያፊነት ወይም

ሠ/ የተከሳሹ የወንጀል አፈፃፀም አደገኛነት ወይም የተፈጸመው ወንጀል አፀያፊነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ተከሳሹ ለማህበረሰቡ ሰላምና ደህንነት አደገኛ በመሆኑ ምክንያት ተከሳሹን በዋስትና መልቀቅ ዜጎች በፍትህ ላይ ያላቸው አመኔታ የሚያሳጣ ነው ብሎ ሲያምን

ምክንያቱም አሁን ካለው ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ እነዚህ ምክንያቶች ፍርድ ቤቶች ዋስትና ለመከልከል እንደ ምክንያት እንዲጠቀምባቸው መፍቀድ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

5.134. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 140(1 እና 2) የምዕራፉ ርዕስ በዋስትና ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ በሚል የተስተካከለ ሲሆን 141(1 እና 2) መጨረሻ ላይ ያለው መስጠት ይኖርበታል የሚለው ሀረግ ይሰጣል በሚል ቃል እንዲተካ ተደርጓል ።

ምክንያቱም ትክክለኛው የህግ ቋንቋ ይሰጣል የሚለው በመሆኑ ነው።

5.135. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 142(1) መጨረሻ ላይ ያለው መወሰን ይኖርበታል የሚለው ሀረግ ይወስናል በሚል ቃል እንዲተካ ተደርጓል። በረቂቅሕጉ አንቀጽ 142 ዋስትናን መፍቀድ የሚለው ድንጋጌ ላይ ንዑስ 2 በሚከተለው አግባብ ተስተካክሏል። በተጨማሪም እዚሁ አንቀፅ ላይ ንዑስ 3 ሆኖ የሚከተለው የተጨመረ ሲሆን በዚሁ አግባብ ንዑስ አንቀፆቹ ቁጥራቸው ተሸጋሽጓል።

142(2) ‘እድሜው አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ወይም የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለበት ልጅ ያላቸው ባልና ሚስት በተመሳሳይ ወይም አንድ ላይ የተያዙ እንደሆነ ለልጆቹ አስተዳደግ የበለጠ ይጠቅማል የተባለው

ወላጅ፣ ነፍሰጡር የሆነች ሴት ወይም አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ወይም የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለበት ልጅ ብቸኛ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፤ የዋስትና መብት ይፈቀድለታል።

142(3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ /2/ የተመለከተው በውስብስብ የአካል ጉዳትና ሕመም ላይ የሚገኝ ልጅ ወይም ወላጅ ላለው እና ምንም ዓይነት ረዳትና አስታማሚ ለሌለው ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ተፈፃሚ ይሆናል።

ምክንያቱም ህጻናት እና ከላይ የተጠቀሱት የተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ላሉባቸው ተጠርጣሪዎች ወይም ተከሳሾች ዋስትና ተፈቅዶላቸው መከራከር እንዲችሉ ለማድረግ ነው።

5.134 በረቂቅ ህጉ 142(7) እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

142/7/ፍርድ ቤቱ ዋስትና የፈቀደለት ሰው በፀብ በአምባጓሮ፣በሴቶችና ህፃናት ላይ በተፈፀመ ወንጀል የተጠረጠረ ከሆነ ወይም ፍርድ ቤቱ ባመነበት ጉዳይ ላይ ተጠርጣሪው በመልካም ባህሪ ለመመራት የእጅ ጠብቅ ዋስ ግዴታ መግባቱን ቅድመ ሁኔታ ሊያደርገው ይችላል።

ምክንያቱም የንኡስ አንቀፁ ዓረፍተ ነገር አቀማመጥ ትክክለኛ ስላልነበረ ለማስተካከል ነው።

5.135 በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 143(1) ድንጋጌ መጨረሻ ላይ ያለው ግዴታውን ከፈጸመ ወዲያውኑ መልቀቅ ይኖርበታል የሚለው ሀረግ ሁኔታውን ካሟላ ወዲያውኑ ይለቀዋል በሚል ሀረግ እንዲተካ ተደርጓል።

ምክንያቱም ንዑስ አንቀፁ የበለጠ ግልፅ እንዲሆን ነው።

5.136 በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 144 ወይም ከሚለው ቀጥሎ ተከሳሹ የሚል ቃል ተጨምሯል።

ምክንያቱም የሰዋሰው ግድፈት ስለነበረበት ነው።

5.137 በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 147(1) ላይ ፍርድ ቤት በራሱ ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ያለው አነሳሽነት ወይም የሚለው ሀረግ አስተያየት፣ በሚል ቃል እንዲተካ ተደርጓል፡

ምክንያቱም ትክክለኛው አገላለፅ ይህ በመሆኑ ነው።

5.138 በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 148(1) ላይ ፍርድ ቤቱ ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ያለው ዋስትናዉ ግዴታ ገቢ የማይሆንበት ምክንያት አለመኖሩን አረጋግጦ የሚለው ሀረግ ዋስትናው በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም ለድንጋጌው አስፈላጊ ሀረግ ስለሆነ ነው።

5.139 በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 150 ላይ (1)(ሀ) ላይ መጀመሪያ ላይ ያለው በቀጠሮ ቀን የሚለው እንዲወጣ ተደርጓል። በንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 ላይ ያለው (ሀ) እና (ለ) እንዲሰረዝ ተደርጓል። በንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 ላይ ያለው ግዴታውን ያልተወጣበት ምክንያት በበቂ ሁኔታ የሚለው ሀረግ ተሰርዞ ግዴታውን ያልተወጣው በበቂ ምክንያት መሆኑን በሚል ሀረግ

እንዲተካ ተደርጓል። ንዑስ አንቀፅ 4 እና 6 ተሰርዘው ንዑስ አንቀፅ 5 የነበረው 4 በመሆን ተሸጋሽጓል። የአንቀፁ ንዑስ 1(ለ) በቀጠሮ ቀን የሚለው ተሰርዟል። እና ንዑስ 4 በተሸጋሸገው በሚከተለው መልኩ ተስተካክለው ቀርበዋል።

**150(4)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሠረት የተሰጠው ትእዛዝ ዐቃቤ ሕግ ተከታትሎ ያስፈፅማል።

ምክንያቱም  አንቀፁን በተቻለ መጠን ግልፅ እንዲሆን ለማድረግ ታስቦ ነው።

5.140 በረቂቁ ሕጉ 151 ላይ ርዕሱ "ዋስትናን ስለማዉረድ" በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል።

ምክንያቱም   ትክክለኛው አገላለፅ ይህ በመሆኑ ነው።

5.141 በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 152(1) በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል።

<u>አንቀጽ **152**፡ ይግባኝ ማቅረብ</u>

1. ዋስትናን በመከልከል፣ በመፍቀድ ወይም ዋስትና ተፈቅዶ በአይነቱ እና በመጠኑ በተሰጠ ትእዛዝ ተጠርጣሪ፣ተከሳሽ ወይም አቃቤ ህግ በሀያ ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማለት ይችላል።

ምክንያቱም  አቃቤ ህግም ይግባኝ እንዲጠይቅ እድል ለመስጠትና በመጠኑና አይነቱ ላይም ዋስትና እንዲፈቀድ ለማድረግ ነው

5.142 በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 153 እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የይግባኝ ማመልከቻውን በቀረበለት ከአምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከመረመረ በኋላ አልቀበልም ለማለት ወይም በሚወስነው ግዴታ መሰረት በዋስትና ለመልቀቅ ይችላል።

ምክንያቱም የመጨረሻ ነው የሚለው የይግባኝ መብትን የሚያጣብ በመሆኑ እንዲወጣ ተደርጓል።

5.143 በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 154 በፊት ምእራፍ አንድ ስር በምርመራ መዝገብ ላይ መወሰን የሚለው ርዕስ ጠቅላላ በሚል የተስተካከለ ሲሆን ንኡስ 4 ሙሉ በሙሉ ተሰርዟል።

ምክንያቱም  በመመሪያ የሚሸፈን ጉዳይ ስለሆነ ነው።

5.144 የረቅቅ ሕጉ  አንቀጽ 154/3/ ዓቃቤ ሕግ  ከሚለው ቀጥሎ ያለው መሠረት  የሚለው ቃል ተሰርዟል።

ምክንያቱም  የሰዋሰው ችግር ስለነበረበት ነው ።

5.145 በረቂቁ ሕጉ 154(3)(መ) ላይ ያለው አያስቀርብም የሚለው ቃል ተሰርዞ አያስከስስም በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም እነዚህ ጉዳዮች ሌላ ቦታ የተመለከቱ በመሆኑ ነው።

5.146 በረቂቁ ሕጉ  አንቀጽ 156(2) ላይ ዕድሜው ከሚለው ቀጥሎ ያለው ዘጠኝ ዓመት ያልሞላው የሚለው ሀረግ ተሰርዞ የወንጀል ኃላፊነት የማያስከትል በሚል ሀረግ ተተክቷል።

ምክንያቱም ወደ ፊት  በወንጀል  ሕጉ ላይ እድሜን በተመለከተ ሊኖር የሚችለውን ለውጥ ታሳቢ ለማድረግ ነው።

5.147 በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 157(6) መጨረሻ ላይ ያለው መስጠት ይኖርበታል የሚለዉ ሀረግ ተሰርዞ "ይሰጣል" በሚል ቃል ተተክቷል።

ምክንያቱም ትክክለኛው አገላለፅ ይህ በመሆኑ ነው።

5.148 በረቂቁ ሕጉ አንቀፅ 158 ንኡስ አንቀፅ 1 ተሰርዟል። በዚሁ መሰረት ንዑስ አንቀፅ 2 የነበረው 1 እና ሌሎችም በዚሁ አግባብ ተሸጋሽገዋል።

ምክንያቱም ንዑስ ድንጋጌው በዚህ አንቀፅ ውስጥ መካተት ስለሌለበት ነው።

5.149 በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 165 ንኡስ አንቀጽ 3 እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

አንቀጽ 165(3) እርቅ የሚደረገው ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሽ እና የግል ተበዳይ ጉዳዩን በእርቅ ለመጨረስ ሲስማሙ ነው። ስምምነታቸውም ከህግና ከሞራል የማይቃረን ሲሆን ነው።

ምክንያቱም የህግና የሞራል ጉዳይ በመርህ ደረጃ ማስቀመጥ አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

5.150 በረቂቁ ሕጉ አንቀፅ 166 ንዑስ አንቀፅ 3 ተጠርጣሪው ከሚለው ቃል ቀጥሎ ወይም ተከሳሽ የሚል እንዲሁም ተጠርጣሪዎች ከሚለው ቃል ቀጥሎ ወይም ተከሳሾች የሚል ተጨምሯል።

ምክንያቱም እርቅ ክስ ከተመሠረተ በኋላም ሊፈፀም ስለሚችል ነው።

5.151 በረቂቁ ሕጉ አንቀፅ 168 ንዑስ አንቀፅ 1 (ሀ) እና (ለ) የነበሩት ወደ ንዑስ 1 እና 2 የተሸጋሸጉ ሲሆን ንዑስ 2 የነበረው ንዑስ 3 ሆኗል።

ምክንያቱም ቅደም ተከተሉ መስተካከል ስላለበት ነው።

5.152 በረቂቁ ሕጉ አንቀፅ 169 በአዲስ መልክ ተስተካክሏል።

<u>አንቀጽ **169**፡ ዓላማ</u>

የጥፋተኝነት ድርድር ዓላማ ተከሳሹ ለተፈፀመው የወንጀል ድርጊት በራሱ ነፃ ፍቃድ እንዲፀፀት እና እንዲታረም እድል ለመስጠት ፣የወንጀል ጉዳዮችን በተቀላጠፈ ሂደት በመጨረስ ወንጀል ፈፃሚዎች ቅጣታቸውን እንዲያገኙ በማድረግ ሕብረተሰቡን ማስተማር ነው ።

ምክንያቱም የድርድሩ አላማ ተከሳሽ እንዲያምን ማድረግ ሳይሆን የወንጀል ፍትህ ሥርዓቱ ቀልጣፋ እንዲሆንና ማህበረሰቡም እንዲማር ማድረግ በመሆኑ ነው።

5.153 በረቂቁ ሕጉ አንቀፅ 170 የጥፋተኝነት ድርድር ስርአት የሚለው አንቀጽ ስር ድንጋጌው በሚከተለው ተስተካክሏል።

የጥፋተኝነት ድርድር የሚካሄደው ተከሳሽ ጥፋቱን አምኖ እና የድርጊቱን አፈፃፀም አሳማኝ በሆነ ሁኔታ በዝርዝር አስረድቶ የክስ ብዛት ወይም ቅጣት እንዲቀነስለት የቅጣቱ አይነት እንዲለወጥለት በፈቃደኝነት ሲስማማ ብቻ ነው።

ምክንያቱም የጥፋተኝነት ስርአትን በግልፅ ለማስቀመጥ እና ክስ ማንሳት የድርድሩ አካል ስላልሆነ ነው።

5.154 በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 171 ንኡስ (2) አንቀጽ ሆኖ እንደሚከተለው ተጨምሯል። እንዲሁም ቀድሞ የነበረው ድንጋጌ ንኡስ(1) ሆኗል።

በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የኢትዮጵያ ህጎች በሰው ልጅ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች የሰው ዘር የማጥፋት፣

ያለ ፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር ወይም ኢ-ሰብአዊ የድብደባ ድርጊቶች፣ ከባድ የሰው ግድያ ወይም አስገድዶ መድፈር ወንጀሎች በጥፋተኝነት ድርድር የሚታዩ ጉዳዮች አይደሉም።

ምክንያቱም እነዚህ ወንጀሎች ከአስከፊነታቸው እና ከአስቃቂነታቸው አንጻር በይቅርታ ወይም በምህረት እንኳን የማያሰጡ ወንጀሎች በመሆናቸው እና እንዲሁም ከባድ የሰው ግድያ እና አስገድዶ መድፈር በጥፋተኝነት ድርድር እንዲታይ ማድረጉ ከድርጊቶቹ ክብደት አኳያ በድርድር ከሚያልቅ ይልቅ በፍርድ ቤት ቢያልቁ ህብረተሰቡን ለማስተማር የበለጠ ጠቀሜታ ስላለው ነው።

5.155. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 172 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ መጀመሪያ ላይ ያለው የጥፋተኝነት ድርድር የሚለው ሀረግ ተሰርዞ በርዕሱ ስር ለሁለቱም ድንጋጌዎች በሚያገለግል አግባብ መንደርደሪያ እንዲሆን ተደርጓል። ከንዑስ አንቀፅ 2 የጥፋተኝነት ድርድር የሚለው ተሰርዟል።

ምክንያቱም ሀረጉ ለሁለቱም ድንጋጌዎች በሚያገለግል መልኩ ለማድረግ ነው።

5.156. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 173(1) ንዑስ አንቀፅ 1፣ 2 እና 5 በሚከተለው መልኩ ተስተካክለው ቀርበዋል።

<u>አንቀጽ **173** ቅድመ ሁኔታ</u>

1. የጥፋተኝነት ድርድር በማናቸውም ተከራካሪ ወገን አነሳሽነት ሊከናወን ይችላል፤የጥፋተኛ ድርድሩ ጥያቄ የተነሳው በተከሳሹ በኩል ከሆነ እና አቃቤ ለመደራደር ከተስማማ የድርድሩን ሂደት ያመቻቻል፡
2. የጥፋተኝነት ድርድር በዐቃቤ ሕግ እና በጠበቃው ይካሄዳል፤ ተከሳሹ በቻለ ጊዜ ሁሉ በድርድሩ ሊሳተፍ ይችላል።
3. ተከሳሹ በሕግ የተደነገጉ የተከሳሽ መብቶችን ለመተው የተስማማ መሆኑን በጽሑፍ መግለጽ ይኖርበታል።

ምክንያቱም ድንጋጌዎቹ የሀሳብና የሰዋሰው ችግር ያለባቸው በመሆኑ ነው።

5.157. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 173 ቅድመ ሁኔት በሚለው አንቀጽ ስር የሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀጽ 8 ተጨምሯል።

173(8) የጥፋተኝነት ድርድሩ ከመጀመሩ በፊት ዐቃቤ ህግ ክስ ማዘጋጀት አለበት።

ምክንያቱም ሀረጉ ለሁለቱም ድንጋጌዎች በሚያገልግል መልኩ መስተካከል ስላለበት ነው።

5.158. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 174 በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል።

<u>አንቀጽ 174 በድርድር ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ሥነ-ስርአት</u>

1. ዐቃቤ ህግ ጉዳዩን በጥፋተኝነት ድርድር ለመጨረስ ፈቃደኛ መሆኑን እና በበኩሉ ሊቀነስ የሚችል የክስ ብዛት፤የክስ አይነት ወይም የቅጣት መጠን በመግለጽ ካዘጋጀው ክስ ጋር አብሮ ለተከሳሽ ይሰጣል ወይም ይልካል።
2. ተከሳሹ ለአቃቤ ህጉ ጉዳዩን በድርድር ለመጨረስ ፈቃደኝነቱን ይገልጻል።

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረተ አቃቤ ህግና ተከሳሽ በጥፋተኝት ድርድር ለመጨረስ ሲስማሙ አቃቤ ህግ ለድርድር የሚበቃቸውን ጊዜ በመወሰን በቀጣይ የሚገናኙበት ጊዜ ይወስናል፡፡

4. ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር የጥፋተኝት ድርድር ለማካሄድ ከተስማሙበት ቀን ጀምሮ በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ ድርድሩ ይጠናቀቃል፡፡

ምክንያቱም የጥፋተኝነት ድርድር በአቃቤ ህግ እና በተከሳሹ መካከል ብቻ የሚደረግ መሆኑን ለማመልከት እና የፍርድ ቤት ሚና የድርድር ስምምነቱን በሚያፀድቅበት ጊዜ የሚመጣ ነው፡፡

5.159. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 175 ላይ የነበረው ማረጋገጫ እንዲሰጥ ማድረግ በሚል ርእስ ተደንግጎ መደምደሚያው ተሰርዞ ያስረዳዋል በሚል ቃል ተተክቶ አንቀጽ 175 የነበረው ወደ አንቀጽ 174 ተወስዶ 174 የነበረው አንቀጽ 175 ተዘዋውሯል፡፡

ምክንያቱም የአንቀፁ አቀማመጥ መደምደሚያው መስተካከል ስላለበት ነው፡፡

5.160. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 176 አንቀፁ ተሰርዞ እንደ አዲስ ተስተካክሏል፡፡

<u>አንቀጽ **176**፡ የጥፋተኝነት ድርድር ይዘት</u>

1. የጥፋተኝነት ድርድር በክስ ብዛት፣በክስ ዐይነት፣በፍሬ ነገር፣በቅጣት ዐይነት እና በቅጣት መጠን ሊደረግ ይችላል፡፡
2. የጥፋተኝነት ድርድር የወንጀሉን ክብደት፣የተከሳሹን ባሕርይ፣የቅጣትን ወጥነት፣ተገማችነትና አግባብነት ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

ምክንያቱም አንቀፁ አላስፈላጊ የነበሩ በርካታ ቃላትና ሀረጋትን የያዘ ስለነበር ግልፅና አጭር አድርጎ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

5.161. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 177 ላይ ያለው ድንጋጌ አንቀፁ በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል፡፡

<u>አንቀጽ **177** የፍርድ ቤት ሥልጣን</u>

1. የጥፋተኝነት ድርድር ስምምነት በጽሑፍ ወይም በቃል ለፍርድ ቤት ይቀርባል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ድርድሩ በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት የተከናወነ መሆኑንና ተከሳሹ በዚህ ሕግ አንቀፅ 174 መሠረት መረዳቱን ለማረጋገጥ የዐቃቤ ሕግን ወይም የተከሳሽን ወይም የጠበቃውን ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
3. የጥፋተኝነት ድርድር ስምምነት ሕግን እና ሞራልን የማይቃረን መሆኑን ሲያረጋግጥ ስምምነቱን ያፀድቃል፤ ስምምነቱም ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡
4. ፍርድቤቱ ስምምነቱ በዚህ ሕግ መሠረት ጉድለት ያለበት ሆኖ ካገኘው ተስተካክሎ እንዲቀርብ ወይም ውድቅ እንዲሆን ሊወስን ይችላል፡፡

ምክንያቱም አንቀፁን ግልፅና አጭር አድርጎ ማቅረብ አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

5.162. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 179 ንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 በሚከተለው መልኩ ተስተካክለው ቀርበዋል፡፡

**179(2)** ድርድር የሚካሄድበት የወንጀል ጉዳይ የፍትሐብሔር ኃላፊነትን የሚያስከትል እንደሆነ እና ዐቃቤ ሕግ ከተጎጂ ፈቃድ ካገኘ የፍትሐ ብሔሩን ጉዳይ ሊጨርስ ይችላል፡፡

**179(3)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ለተጎጂው ሊከፈል የሚገባውን የጉዳት ካሣ ወይም ሊተካ የሚገባውን ገንዘብ ወይም ሌላ ወጪ እና ኪሳራ ያካትታል ፡፡

ምክንያቱም ድንጋጌዎቹን ግልፅና አጭር አድርጎ ማቅረብ አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

5.163. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 179 ከንኡስ አንቀጽ 2 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀጽ 3 የተጨመረ ሲሆን ነባሩ ንኡስ አንቀጽ 3 ወደ ንኡስ አንቀጽ 4 ተሸጋሽጓል፡፡

179(3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ተጎጂው የፍትሐብሔሩን ጉዳይ በተመለከተ በድርድሩ ውጤት ያልተስማማ እንደሆነ ጉዳዩን በራሱ ፍርድ ቤት መውሰድ ይችላል፡፡

ምክንያቱም ተጎጂው አቃቤ ህግ ባደረገው ድርድር ውጤት ካልተስማማ ጉዳዩን በራሱ ጊዜ ወደ ፍርድ ቤት ይዞ መሄድ እንዲችል እድል ለመስጠት ነው፡፡

5.164. በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 181 በምርመራ የሚለው ቃል ተሰርዟል፤ ንኡስ አንቀፅ 1 ላይ ሂደት ላይ ያለ ከሚለው ሃረግ ቀጥሎ የግል ተበዳይ ያለበት የሚል እና የወንጀል ጉዳይ ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ማስረጃ ከመሠማቱ በፊት የሚሉ ሀረጎች ተካተዋል፡፡ እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ 2 በሚከተለው መልኩ ተስተካክሎ ቀርቧል፡፡

**181(2)** በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ሰብአዊ መብትን የሚጥስ፣ሴትን መጥለፍ ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች እና መሠል በሴቶች እና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፣ በሰው ልጅ ክብር እና በሀገር ደህንነት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ እንደሆነ ባህላዊ ስርአት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

ምክንያቱም በባህላዊ መንገድ የሚያልቁ ጉዳዮች ክስ ከተመሰረተ በኋላ ስለሆነና ጉዳዮቹም የግል ተበዳይ ያለባቸው ሆነው ማስረጃ ከመሠማቱ በፊት በባህላዊ እልባት ማግኘት ያለበት ሲሆን በተጨማሪም በባህላዊ መንገድ የሚታዩ ሁሉም ወንጀሎች አለመሆናቸውን ለማመልከት ነው፡፡

5.165. በረቂቁ ሕጉ አንቀጽ 182 (1) እና 185 መጀመሪያ ላይ ያለው ተጠርጣሪው ወይም የሚለው ቃል ተሰርዟል፡፡ በተጨማሪም በአንቀጽ 182 ንኡስ አንቀጽ 2 የሚከተለው ተጨምሯል፡፡

**182(2)** ተከሳሹ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ከሆነ ጉዳዩ በባሕላዊ ሥርዐት አይታይም፡፡

ምክንያቱም ደጋጋሚ ወንጀለኛ በተደጋጋሚ ተከሶ ለብዙ ጊዜ የተቀጣ ቢሆንም ያተሰጠው ቅጣት ያልተማረ በመሆኑ በባህላዊ መንገድ እልባት መሰጠቱ አስፈላጊ ስላልሆነ ነው፡፡

5.166. በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 183 (1) ተሰርዞ በሚከተለው መልኩ እንደ አዲስ ተስተካክሏል። እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀፅ 2፣ 3፤ 4 ተጨምሯል። በረቂቁ ህጉ ንዑስ 2 የነበረው ንዑስ 5 ሆኖ የቀጠለ ሲሆን በረቂቁ ንዑስ 3 የነበረው ከዚህ አንቀጽ ተሰርዟል።

**183(1)** ለጉዳዩ ዕልባት የሚሰጥ የታወቀ ባህላዊ ሥርዐት መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል።

**183(2)** ጉዳዩ በባህላዊ ሥርአት እንዲታይ በዚህ ሕግ መሰረት ጥያቄ ሊቀርብ ይገባል።

**183(3)** ተከሳሹ ጉዳዩ በባህላዊ ሥርአት ታይቶ እልባት እንዲያገኝ ፍቃደኛ ሊሆን ይገባል።

**183(4)** ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩ በባህላዊ ሥርዓት እንዲታይ ሲወስን ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል ማስረጃ መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

ምክንያቱም አንቀጹ ከላይ የተዘረዘሩት በርካታ ጉዳዮችን ባለማካተቱ ነው። መሠረታዊ ነገሩ የታወቀ ስርዓት መኖሩ ስለሆነ እና በባህላዊ መንገድ መታየት ያለበትና የሌለበት ጉዳይ ስለሚወሰን መጥቀሱ አስፈላጊ ስላልሆነ ነው እንዲሁም አንቀፁ የጎደለው በርካታ ጉዳዮች ስለነበሩ በአዲስ መልክ ተስተካክሏል።

5.167. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 184 ላይ ያለው በባህላዊ ሥርዐት እንዲታይ የሚቀርብ ጥያቄ አቀራረብ እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

<u>አንቀፅ **184** በባህላዊ ሥርዐት እንዲታይ የሚቀርብ ጥያቄ አቀራረብ</u>

1. ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ፣በግል ተበዳይ፤ በተከሳሽ ወይም በባሕላዊ ሥርዐት ሥልጣን ባለው ሰው፣አግባብ በሆነ የመንግስት አካል ወይም በዐቃቤ ሕግ አነሳሽነት ተከሳሹ ፈጸመ የተባለው የወንጀል ድርጊት በባሕላዊ መንገድ እንዲታይ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል።
2. ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ህግ እና የተከሳሽን ፈቃደኝነት አረጋግጦ ጉዳዩን ወደ ባህላዊ ስርአቱ ይመራዋል።

ምክንያቱም በባህላዊ ስርአት ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ በአንቀጹ የተካተቱን አካላት አነሳሽ መሆን እንዲችሉ ለማመላከት ነው።

5.168. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 186 ላይ ያለው ርዕስ የውሳኔ አሰጣጥ ተብሎ ድንጋጌዉ በአዲስ መልክ እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

<u>አንቀጽ **186**፡ የውሳኔ አሰጣጥ</u>

1.የባህላዊ ሥርዐቱ ጉዳዩን በሠላሳ ቀናት አጠናቆ ውሳኔ ይሰጣል።

2. በባሕላዊ ሥርዐት መሠረት የተሰጠ ውሳኔ ክሱ በተመሠረተበት ፍርድ ቤት የሥራ ቋንቋ ሆኖ በዐቃቤ ሕግ ወይም በአማራጭ ቅጣት አፈጻጸም ቦርድ በጽሑፍ ይቀርባል።

3.ፍርድ ቤት የቀረበው የባህላዊ ሥርዐት ውሳኔ ሕግን እና ሞራልን የማይቃረን፣ሰብዓዊ ክብርን የማይነካ መሆኑን፣ የሂደቱን ዓላማ ያሳካ መሆኑን በማረጋገጥ ያጸድቃል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ፍርድ ቤቱ ያላፀደቀው ከሆነ የክስ ሂደቱ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል። ምክንያቱም በባህላዊ መንገድ እልባት ያገኛል ተብሎ ፍትህ ሳይገኝ እንዳይቆይ የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

5.169. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 187 በባህላዊ ሥርዐት እልባት ያገኘ ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤቶች ያላቸው ስልጣን የሚለው ድንጋጌ ሙሉ በሙሉ ተሰርዟል።

ምክንያቱም - ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በባህላዊ ስርአት የታየውን ጉዳይ የሚያጸድቀው ከሆነ መዝገቡ እንደሚዘጋ የሚታወቅ ስለሆነ መደንገግ አስፈላጊ አይደለም።

5.170. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 188 ሙሉ በሙሉ ተሰርዟል። በተስተካከለው በአንቀፅ 186 ላይ ተጠቃሏል።

ምክንያቱም ሀሳቡ በተስተካከለው አንቀፅ 186 ላይ የተጠቃለለ ስለሆነ ነው ።

5.171. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 189 እስከ 196 በተስተካከለው ከአንቀጽ 187 እስከ 194 ሌሎች መፍትሄዎች የሚለው ተለዋጭ መፍትሄዎች በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም መፍትሄዎቹ ለፍርድ ሂደቱ ተለዋጭ ስለሆኑና እና ሌሎች የሚለው ቃል አሻሚ ስለሆነ ነው።

5.172. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 190 በተስተካከለው አንቀጽ 188 ከንዑስ አንቀጾቹ በላይ እንደ መንደርደሪያ ተፈጻሚ ይሆናል የሚለው ተፈጻሚ የሚሆነው ተከሳሹ፡- በሚል ተስተካክሏል። ንዑስ አንቀጽ 6 ሙሉ ለሙሉ ተሰርዟል።

ምክንያቱም ተለዋጭ መፍትሄ የሚፈለግላቸው ተከሳሽ ሆነው ከቀረቡ በኋላ ስለሆነ እና ንዑስ አንቀጽ 6 ራሱን በቻለ ክፍል በልዩ ሥነ ሥርዐት ስለተደነገገ ነው።

5.173. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 191 በተስተካከለው 189 1(ሀ) ለተጠርጣሪው ወይም የሚለው ቃል በተከሳሹ ተተክቷል።

ምክንያቱም ተለዋጭ መፍትሄዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት ተከሳሾች ላይ ስለሆነ ነው።

5.174. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 191 በተስተካከለው አንቀጽ 189 ንዑስ አንቀጽ 2 የነበረው ተሰርዞ 3 የነበረው ንዑስ 2 ሆኖ በተሸጋሸገው ንዑስ አንቀፅ 2 ለዐቃቤ ሕግ ይመራል የሚለው ማሳረጊያ ለሚመለከተው ተቋም ይመራል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም ከስር ያሉት ንዑስ አንቀፆች ስለተሰረዙ እና በዚህ ሕግ አማራጭ መፍትሄ እርምጃዎችን የሚያስፈፅሙ ተቋም እንዲቋቋም ታሳቢ ስለሚያደርግ መመራት ያለበት ለተቋሙ መሆኑን ለማመላከት ነው።

5.175. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 191 በተስተካከለው አንቀጽ 189 4 እና 5 ተሰርዟል

ምክንያቱም በልዩ ስነስርአት የተሸፈነ ስለሆነ ድጋሜ ስለሚሆን ነው።

5.176. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 192/1/ እና /2/ በተስተካከለው አንቀጽ 190/1/ እና /2/፣አንቀጽ 193/2//ለ/፣/ሐ/ እና /መ/ በተስተካከለው አንቀጽ 191/2//ለ/፣/ሐ/ እና /መ/ እንዲሁም አንቀጽ 193/3/

በተስተካከለው አንቀጽ 191/3/፣ አንቀጽ 194/1/በተስተካከለው 192/1/፣አንቀጽ 195 በተስተካከለው 193 ዐቃቤ ሕግ የሚለው እና ቅጣት አስፈፃሚ ቦርድ የሚሉት ተሰርዘዋል።

ምክንያቱም ተለዋጭ መፍትሄ እልባት እንዲያገኝ የመወሰን ሥልጣን የፍርድ ቤት ስለሆነ ነው።

5.177. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 192/1/ለ/ በተስተካከለው አንቀጽ 190/1//ለ/ መወሰን ይኖርበታል የሚለው ይወስናል በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም - በትዕዛዛዊ መንገድ መቀመጡ አግባብ ስለማይሆን ነው።

5.178. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 193 በተስተካከለው አንቀጽ 191 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 ተሰርዘዋል።

ምክንያቱም ደንብ የማውጣት ስልጣን የሚለው አንቀጽ ላይ ስለተካተተ ነው።

5.179. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 195 ንኡስ ቁጥር (1) በተስተካከለው አንቀጽ 193 በሚከተለው ተስተካክሏል።

193(1) በፍርድ ቤት የተወሰነ ተለዋጭ መፍትሔ ሳይፈጸም ወይም ውጤታማ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ መፍትሄውን እንዲያስፈፅም የታዘዘው ተቋም ወይም አግባብነት ያለው አካል በሚያቀርበው አስተያየት መሠረት ፍርድ ቤት ተገቢውን ይወስናል።

ምክንያቱም ድንጋጌው ግልፅነት የሚጎድለው ስለነበረ ነው።

5.180. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 196 በተስተካከለው አንቀጽ 194 በሚከተለው ተስተካክሏል።

አንቀጽ 194 በተለዋጭ መፍትሔ እልባት ያገኘ ጉዳይ ይግባኝ አይባልበትም።

ምክንያቱም የሰዋሰው ችግር ስለሚያመጣ ነው።

5.181. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 197 በተስተካከለው አንቀጽ 195 ንዑስ አንቀፆቹን ተጣምረው እንደሚከተለው ተስተካክሏል ።

<u>አንቀጽ **195** መርህ</u>

ዐቃቤ ህግ የምርመራ መዝገቡን መርምሮ ተጠርጣሪን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ ክስ ይመሰርታል ክሱም በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ሰልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይቀርባል።

ምክንያቱም ተመሳሳይ ሃሳብ እንድ ላይ መነበብ ስላለበት ነው።

5.182. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 198 በተስተካከለው አንቀጽ 196 ለይቶ እና፣ መግለጫ የሚለው ቃል ተሰርዟል፤ስለ ሁኔታው የሚለው ቃል አፈፃፀሙ በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም አላስፈላጊ ድግግሞሽ በመሆኑ ነው።

እዚሁ አንቀፅ ንዑስ 2/ሠ/ ተገቢ እንደሆነ የሚለው ሀረግ ተሰርዟል። 2/ሰ/ የሚመለከቱ ከሚለው ቀጥሎ ያለው ሀረግ የሚያቋቁመው በሚለው ተተክቷል 2/ሸ/ መጨረሻ ላይ መያዝ ይኖርበታል የሚለው ይይዛል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም የሰዋሰው ግድፈት ስላለው እና ድጋሜ ስለሆነ ነው።

5.183. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 199/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 197/3/ በተመሳሳይ የወንጀል ደረጃ ያሉ ተደራራቢ የሚለው እንዲሁም የሚመለከታቸው የዐቃቤ ሕግ ተቋማት ክሱን አጣምሮ የሚመሰርተውን የዐቃቤ ሕግ ተቋም በጋራ ይወስናሉ የሚለው ተሰርዟል፡፡

ምክንያቱም መወሰን ያለበት የፌዴራል ፍትህ ሚኒስቴር ነው አንዱ ክልል ከሌላ ክልል ጋር መገናኘት ከባድ ስለሚሆን ነው፡፡

5.184. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 200 በተስተካከለው አንቀጽ 198 ወይም ዐቃቤ ሕግ የሚለው ተሰርዟል፡፡

ምክንያቱም በዐቃቤ ሕግ ጠያቂነት ክስ የሚነጣጠል ከሆነ ክስ ማሻሻል ስለሚሆን ነው፡፡

5.185. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 202/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 200/2/ ወይም ለተፈፀሙ ደርጊቶች የሚለው ተሰርዟል፡፡

ምክንያቱም- ድጋሜ ስለሆነ እንዲሁም ሊረጋገጡ፣ በሚባሉት፣ ወንጀሎች የሚሉት በነጠላ አፃፃፍ ተቀይረዋል፡፡

5.186. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 202/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 200/3/ ተሰርዟል፡፡

ምክንያቱም ስለ ክስ ማሻሻል ስለሆነ ከአንቀጹ ጋር ሰለማይሄድ ነው፡፡

5.187. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 202/4/ በተስተካከለው አንቀፅ 200/4/ ለብቻው ቅጣትን የሚያከብዱ ወንጀሎች ክስ አቀራረብ የሚል ርእስ የያዘ አዲስ አንቀጽ /201/ ተሰጥቶት (ሀ) እና (ለ) አንቀጽ 201(1) እና (2) ሆነው ተስተካክሏል፡፡

ምክንያቱም አንቀጹ ከያዘው ስያሜ ጋር ስለማይሄድ ነው፡፡

5.188. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 203 በተስተካከለው አንቀጽ 202 ተከሶ የሚለው የተከሰሰ ሰው በሚል እና ንዑስ 3 የሚያንስ የሚለው ያነሰ በሚል የተተካ ሲሆን ወንጀል የሚለው ቃል ተሰርዟል፡፡

ምክንያቱም የቃል ድግግሞሽ ስላለው ነው፡፡

5.189. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 204/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 203/1/ በሚከተለው ተተክቷል፡፡

203/1/ ዐቃቤ ሕግ እንደወንጀሉ ክብደትና ውስብስብነት የምርመራ መዝገቡ በደረሰው በሀያ ቀናት ውስጥ ክስ ይመሠርታል፡፡

ምክንያቱም ክስ ለመመስረት የወሰነ እንደሆነ የሚለው የወሰነበትን ቀን ማወቅ ስለማይቻል እና አልወሰንኩም በሚል መዝገብ ላይ ሳይወስን አላስፈላጊ ጊዜ እንዳይወስድ ነው፡፡

5.190. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 205/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 204/3/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል፡፡

**204(3)** ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በበቂ ካለስረዳ ወይም በንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በአስር ቀን ውስጥ ክስ ካልመሠረተ እና ተጠርጣሪው ዋስትና ተከልክሎ የቆየ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪውን በዋስትና ወይም ያለዋስትና ይለቀዋል፡፡

ምክንያቱም የግልፅነት ችግር ስለነበረበት ነው፡፡

5.191. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 206 በተስተካከለው አንቀጽ 205 በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል፡፡

<u>አንቀጽ **205** ክስ ማቋረጥ እና ማንሳት</u>

1. ዐቃቤ ሕግ ክርክሩ ከሚቀጥል ክሱ ቢነሳ የሚያሳካው የሕዝብ ጥቅም አለ ብሎ ሲያምን ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ያቀረበውን ክስ ለፍርድ ቤቱ በጽሁፍ በማቅረብ ማንሳት ይችላል።
2. ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ከፍርድ በፊት ለፍርድ ቤቱ በጽሁፍ በማቅረብ ማቋረጥ ይችላል።
3. ዐቃቤ ሕግ በተከሳሹ ላይ ያቀረበውን ክስ ካነሳ ወይም ካቋረጠ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን በመዝጋት ክሱ ለጊዜው እንዲቋረጥ እና ተከሳሹ ማረፊያ ቤት የሚገኝ እንደሆነ እንዲለቀቅ ትእዛዝ ይሰጣል። በክሱ ምክንያት የተያዘ ኤግዚቢት ወይም የታገደ ንብረት ካለ የዐቃቤ ሕግን አስተያየት በመጠየቅ እንዲለቀቅ ወይም እግዱ እንዲነሳ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተነሳ ክስ ድጋሚ ሊንቀሳቀስ አይችልም።

ምክንያቱም ዐቃቤ ህግ ክስ ሲያነሳም ሆነ ሲያቋርጥ የራሱን ክስ በመሆኑ ክሱን ሲያቋርጥ ወይም ሲያነሳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንዲያውቀው የማድረግ ሀላፊነት ያለበት መሆኑን ክሱን ሲያነሳም ሆነ ሲያቋርጥ ከፍርድ ቤት በማንኛውም ጊዜ ማድረግ እንደሚችል እና ፍርድ ቤትም እግድን በተመለከተ ውሳኔ ሲሰጥ የአቃቤ ህግን አስተያየት መጠየቅ ያለበት መሆኑን ለማመልከት ነው።

5.192. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 207 በተስተካከለው አንቀጽ 206 ንዑስ አንቀጽ 4 እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

206/4/ በዚህ ሕግ የዐቃቤ ሕግ ክርክርና ክስ በሚመለከት የተደነገገው እንደ አግባብነቱ የግል ከሳሽንም ይመለከታል።

ምክንያቱም የአፃፃፍ ችግር ስለነበረበት ነው።

5.193. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 208 ተሰርዟል። ቀሪዎቹ እንደ ቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል። ምክንያቱም በግል አቤቱታ የሚቀርብ የወንጀል ክስ ወጪ በሚለው አንቀጽ 439 ስለተሸፈነ ነው።

5.194. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 209/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 207/1/ ዐቃቤ ሕግ ሲፈቅድ ወኪሉ የሚለው በጠበቃው የተተካ ሲሆን በተጨማሪም እዚሁ ንዑስ አንቀጽ ላይ ቅደም ተከተሉን በማስተካከል የትዳር ጓደኛው ቅድሚያ እንዲኖረው ተደርጓል። ንዑስ አንቀጽ 3 እንደ ነገሩ ሁኔታ የሚለው ለትርጉም ክፍት ስለሚሆን ወይም በሚል ቃል ተተክቷል።

ምክንያቱም ዐቃቤ ሕግ የሚፈቅደው የግል ክስ መቅረብ አለመቅረቡ ላይ ነው እንጅ ማን ያቅርበው የሚለው ላይ አይደለም።

5.195. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 210 በተስተካከለው አንቀጽ 208 መስጠት ይችላል የሚለው ይሰጣል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም የሰዋሰው ችግር ስለሚያመጣ ነው።

5.196. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 212/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 210/2/ ስምምነት የሚለው ቃል ተሰርዟል።

ምክንያቱም እርቅ በራሱ ስምምነት ስለሆነ ነው።

5.197. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 214 በተስተካከለው አንቀጽ 212 ርዕስ መሆኑ የሚለው መፈፀሙ በሚል እና ንዑስ አንድ ላይ ዐቃቤ ሕግ ወደ ፊት እንዲሆን ተደርጓል ።

ምክንያቱም ለወንጀል መፈፀም የሚለው ቃል ገላጭ ስለሆነ ነው።

5.198. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 215 በተስተካከለው አንቀጽ 213 ርዕስ በዐቃቤ ሕግ ስለሚቀርብ የፍትሐ-ብሔር ክስ ተብሎ የተስካከለ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ 2 ሙሉ የሚለው ቃል ተሰርዞ ማቅረብ ይኖርበታል የሚለው ያቀርባል፤ ንዑስ አንቀጽ 3 የሚከሰስ የሚለው የሚቀርብ በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ግልፅ አድርጎ መፃፍ በማስፈለጉ ነው።

5.199. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 219 በተስተካከለው አንቀጽ 217 በመቋረጡ የሚለው የተቋረጠለት፣ ወይም ከሚለው በኋላ ከተመሰረተበት ወንጀል ክስ የሚለው ተሰርዟል ፍርድ ቤቱ ከሚለው ቀጥሎ የቀረበውን የሚለው ተሰርዟል የፍትሐብሔር የሚለው የፍትሐብሔሩን በሚል ተስተካክሏል ውሳኔ የሚለው ለመወሠን፣ ሊሰጥ ይሰጣል የሚለው ይሰጣል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም የሰዋሰው ግድፈት ስለነበረበት ነው።

5.200. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 222/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 220/2/ **በሚከተለው ተስተካክሏል።** እንዲሁም ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ ያለው ሆኖም የሚለው ተከሳሹ በሚል ተተክቷል።

**220/2/** የክስ ማመልከቻ ለፍርድ ቤቱ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ መጥሪያ ወዲያውኑ ይሰጣል።

ምክንያቱም መጥሪያ የማድረስ ኃላፊነት የማን እንደሆነ ግልፅ ማድረግ ስለሚያስፈልግ ንዑስ አንቀፁ ላይ ዐቃቤሕግ መካተቱ መጥሪያ የማድረስ ኃላፊነት የዐቃቤ ሕግ ነው ለሚል ትርጉም ስለሚያጋልጥ ነው እና የሰዋሰው ግድፈት ስለነበረበት ነው።

5.201. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 223 የተሰረዘ ሲሆን ሌሎቹም እንደ ቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል።

ምክንያቱም በተስካከለው አንቀጽ 225 ላይ ስላለ ድጋሜ ስለሆነ ነው ።

5.202. በረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 226/1/ በተሸጋሸገው አንቀፅ 224/1/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

**224/1/** ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደ ነገሩ ሁኔታ ተለዋጭ ቀጠሮ ሊሰጥ፣በፖሊስ ተይዞ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ወይም መዝገቡን በጊዜያዊነት ሊዘጋው ይችላል።

ምክንያቱም መዝገቡን የሚዘጋው ተከሳሹ ተይዞ እስኪቀርብ በጊዜያዊነት እንዲሆን ነው። ሊዘጋው የሚለው ለወጣት ጥፋት አጥፊ መሆኑ በግልፅ ካልተመላከተ ለሌሎች ተከሳሾችም መጥሪያ ደርሷቸው ካልቀረቡ መዝገብ እንደሚዘጋ የሚያመላክት ስለሆነ ግልፅ ማድረግ ስለሚያስፈልግ ነው።

5.203. በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 227 በተስተካከለው አንቀጽ 225 በሚከተለው መልኩ በአዲስ እንዲቀረፅ ተደርጓል።

አንቀጽ 225 ተከሳሽ በሌለበት የሚታይ ክስ

1. የቅጣቱ መነሻ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ሰባት አመትና ከዛ በላይ ሚያስቀጣ የወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ሊታይ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ክርክሩ ተከሳሹ በሌለበት የሚታየው ተከሳሹ መጥሪያ ደርሶት በቀጠሮው ቀን ሳይቀርብ በመቅረቱ ፍርድ ቤቱ ታስሮ እንዲቀርብ የሰጠው ትእዛዝ መፈጸም አለመቻሉ ሲረጋገጥ ነው።

3. ፍርድ ቤት ተከሳሹ እንዲቀርብ የሚያዘውን መጥሪያ ለተከሳሽ መድረስ አለመቻሉ ሲረጋገጥ፤በሀገሪቱ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ፤በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን በሚነገር ማስታወቂያ ተሰራጭቶ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ክርክሩ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /1/ መሰረት ተከሳሹ በሌለበት ይታያል። የተሰራጨው ማስታወቂያ ቀጠሮውን ቀን የያዘ ሆኖ በቀጠሮው ቀን ባይቀርብ ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ የሚታይ መሆኑን የሚገልጽ መሆን አለበት።

4. ተከሳሹ ክርክሩ በሌለበት በመታየት ላይ እያለ ተይዞ ወይም በራሱ ፈቃድ የቀረበ እንደሆነ ጉዳዩ በደረሰበት ደረጃ ገብቶ ክርክሩን ይቀጥላል። ሆኖም ተከሳሹ ሳይቀርብ የቀረው በበቂ ምክንያት ከሆነ፤አስቀድሞ የተደረገው ክርክር የተከሳሹን መብት የሚያጣብብ ወይም ፍትሕን የሚያጓድል ሲሆን ፍርድ ቤቱ ቀድሞ የተደረገው ክርክር ቀሪ ሆኖ የክርክሩ ሂደት እንደገና እንዲከናወን ያዛል።

5. ጉዳዩ ከአንድ በላይ ተከሳሾች ያሉበት ሆኖ የጉዳዩ እንደገና መታየት የሌሎች ተከሳሾችን የመከላከል መብት የሚነካ ወይም የተፋጠነ ፍትሕ ለመስጠት የሚያዳግት እንደሆነ ተነጥሎ ሊታይ ይችላል።

ምክንያቱም አብዛኛው የወንጀል ድርጊቶች ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ በሚያስችል መልኩ እንዲቀረፅ ለማድረግ፤ የኢኮኖሚ እና ከባድ ወንጀሎችም በዚህ ስርዓት ውስጥ በምን አግባብ እንደሚስተናገዱ በግልፅ ለማመልከት ነው።

5.204. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 228/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 226/2/ ራሱ ወይም በጠበቃው የሚለው ተሰርዟል።

ምክንያቱም የቃላት መደጋገም ስለሚሆን ነው።

5.205. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 230 ንኡስ አንቀጽ/1/ ላይ ያለው ማጣቀሻ አንቀጽ 227 ይል የነበረው 225 እና **226** በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ጊዜው ሂደቱን ብቻ ሳይሆን ፍርድ ሲሰጥም መቅረብ ያለበት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መሆን ስላለበት ነው።

5.206. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 231(2) በተስተካከለው አንቀጽ 229/2/ ተሰርዟል ።

ምክንያቱም ጉዳዩ አይታይም ከተባለ በቂ ስለሆነ ነው።

5.207. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 232 በተስተካከለው አንቀጽ 230 ዐቃቤ ህግ የሚለው ከሳሽ በሚል ተተክቷል። እንዲሁም እና የማስረጃዎች ዝርዝርና መግለጫ ጉዳዩን የማየት የዳኝነት የሚለው ሀረግ ተሰርዟል።

ምክንያቱም የክስ ማመልከቻ ሊይዝ የሚገባው ነገር በሌላ አንቀጽ ስለተሸፈነ ነው።

5.208. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 233 በተስተካከለው አንቀጽ 231 ርዕስ ስለ የሚለው ተሰርዟል።

ምክንያቱም ትክክለኛው አፃፃፍ ስለሆነ ነው።

5.209. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 234 በተስተካከለው አንቀጽ 232/ለ እና ሐ ቅደም ተከተላቸው ተቀያይሯል እንዲሁም ረ ላይ ትክክለኛነት የሚለው እና ንዑስ 2 ላይ ተግባር የሚለው አስፈላጊ ስላልሆነ ተሰርዟል፤ንዑስ 5 ፍርድ ቤቱ የሚል ተካቷል ፡፡

ምክንያቱም በክስ ሂደቱ በቅድሚያ የሚታየው በ ሐ ያለው ስለሆነና ዐረፍተ ነገሩ ጎዶሎ ስለሆነ እንዲሁም ውሳኔ የሚሰጠው አካል በግልፅ መቀመጥ ስላለበት ነው፡፡

5.210. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 235(1) በተስተካከለው አንቀጽ 233(1) ዐቃቤ ህግ የሚለው ከሳሽ በሚለው ተተክቷል ፡፡ እንዲሁም አዘጋጅቶ እንዲሰጥ የሚለው እንዲደርሳቸው በሚል ተስተካክሏል፡፡ 233(2) ፍርደኛ ሆኖ የሚለው ተሰርዟል ፡፡

ምክንያቱም ማረሚያ ቤት የሚለው በቂ ስለሆነ ነው፡፡

5.211. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 237 በተስተካከለው አንቀጽ 235/ሀ፣ለ፣ሐ እና ሰ ተሰርዘዋል መ፣ሠ፣ረ ሀ፣ለ፣ሐ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **2** በጽሑፍ የሚል ቃል እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ምክንያቱም የዋናው የክስ ሂደት ተግባራት ስለሆኑና ዐረፍተ ነገሩ ሙሉ እንዲሆን ነው፡፡

5.212. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 238 ተሰርዟል፡፡ ሌሎቹ እንደቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል፡፡

ምክንያቱም በተስተካከለው አንቀጽ 233 ላይ ስላለ ድጋሜ እንዳይሆን ነው፡፡

5.213. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 239/ለ/ በተስተካከለው አንቀጽ 236/ለ/ የቅድመ ክስ መስማት ተግባራትን ክንውን መሠረት አድርጎ በተለይም የሚለው ተሰርዞ ጠበቃ የሚል ተጨምሯል፡፡ እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ/ ያልተሟሉ እንደሆነም ምክንያቱን ጠይቆ ከተረዳ በኋላ የሚለው ተሰርዟል፡፡

ምክንያቱም ጠበቃ እና አስተርጓሚ መሟላታቸውን ማረጋገጥ ስላልሆነ አላማው መሠረት ያደረገው ቅድመ ክስ መሆኑን መግለፅ አግባብ ስላልሆነ ነው፡፡

5.214. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 239/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 236/3/ ተጠርጣሪው እና በቅድመ ክስ መስማት ሂደት የሚሉት ተሰርዘዋል፡፡

ምክንያቱም ጊዜ ቀጠሮ ላይ የሚቀርበው ተጠርጣሪ እንደሆነ ስለሚታወቅ እና የቅድመ ክስ መስማት ሂደት ተግባራት ስለተዘረዘረ ድጋሜ ስለሚሆን ነው፡፡

5.215. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 241 በተስተካከለው አንቀጽ 238/1/ ወይም በሌላ የሚለው ተሰርዟል እንዲሁም 238/2/ ውሳኔ የሚለው እልባት በሚል ተስተካክሏል፡፡

ምክንያቱም ሌላ ሥነ ሥርአት ካለ በዚያው የሚደነገግ ስለሚሆን ነው፡፡ እንዲሁም የሚቀጠረው ለውሳኔ ብቻ ሳይሆን ለተለያዩ ጉዳዮች ስለሚሆን ነው፡፡

5.216. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 242 በተስተካከለው አንቀጽ 239/3 እና 4/ ተሰርዘዋል፡፡

ምክንያቱም መመሪያ የማውጣት ስልጣን ላይ ስለተካተተ ነው፡፡

የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 243/2/ተ/ በተስተካከለው አንቀጽ 240/2/ተ/ ስር መጨረሻ ላይ የተደነገገው ለሚከናወነው ተግባር በቂ ነው ብሎ ያመነበትን ወደ ፊት መቷል። እዚሁ አንቀጽ 2/ረ/ ላይ በድንገት ፣ ለመስማት ወይም ለመመርመር የሚሉት ሀረጎች ተሰርዘው የቀረበ ብቻ ሆኗል።

ምክንያቱም  የተቆራረጠ ሀሳብ ስለነበረ እና አዲስ ማስረጃ ከቀረበ በኋላ ሂደቱ ስለሚታወቅ ነው።

5.217. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 243/4/ በተስተካከለው አንቀጽ 240/4/ ተሰርዟል።

ምክንያቱም የቀጠሮ ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ ቀጠሮ አያሰጥም መባሉ በአጋጣሚ ቀጠሮ መስጠት ቢያስፈልግ በሕግ መከልከል እንዳይሆን ነው።

5.218. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 244/7/ በተስተካከለው አንቀጽ 241/7/ የተከሳሽ ጠበቃ ባለበት ክርክርን መርቶ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል የሚለው ተሰርዞ በዚህ ሕግ መሠረት ተለዋጭ መፍትሄ እንዲያገኝ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል የሚል ተጨምሯል ።

ምክንያቱም እንደዚህ  ዓይነት ተከሳሾች የሚያስፈልጋቸው ተለዋጭ መፍትሄ ስለሆነ ነው።

5.219. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 245 በተስተካከለው አንቀጽ 242/2/ መ እንደሆነ የሚለው ቃል ተሰርዟል። እንዲሁም ንዑስ 2/ሠ/ ላይ ሆኖ ይኸው መብት በሕግ መሠረት ያልተነሳ እንደሆነ የሚለው ተሰርዞ ከሆነ ወይም ክስ ለመመስረት ልዩ ፈቃድ የሚያስፈልግ እንደሆነ በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም ቃሉ በመግባቱ የሚጨምረው ነገር ስለማይኖር እና በሕግ መሠረት ካልተነሳ ያለመከሰስ መብት አለው ማለት ስለሆነ ነው።

5.220. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 245 በተስተካከለው አንቀጽ 242/2/ኀ /ላይ ወይም የሚል አያያዥ ቃል ተጨምሯል እንዲሁም ነ ተሰርዞ ኘ የነበረው እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

**242/2/**ነ/ እድሜ እና ሌሎች መሰል ወደ ፍሬ ነገር ገብቶ ለማየት የማያስችሉ ጉዳዮችን መሰረት ያደረገ ከሆነ

ምክንያቱም በወንጀል ሕጉ መሠረት ክስ የማይቀርብባቸው ጥፋት አጥፊዎች ክስ ተመስርቶባቸው ሲገኝ መቃወሚያ ሆኖ መቅረብ እንዲችል ለማድረግ ነው።

5.221. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 246 በተስተካከለው አንቀጽ 243/1/ ሀ እና ለ ተሰርዞ ንዑስ 1 ሆኖ በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል።

238/1/ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ ያቀረበው የክስ መቃወሚያ ላይ የአቃቤ ህግን አስተያየት ተቀብሎ ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል።

ምክንያቱም - አጭር እና ግልፅ አድርጎ ለመፃፍ ነው።

5.222. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 247 በተስተካከለው አንቀጽ 244 የሚያጣብበ ከሚለው ቀጥሎ፣ የተቀላጠፈ የሚል ቃል ተጨምሯል።

ምክንያቱም የክስ መነጣጠል ዋናው ዓለማ ቅልጥፍና ስለሆነ ነው፡፡

5.223. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 248 በተስተካከለው አንቀጽ 245 ርዕስ በክስ ላይ የሚለው ቃል ተሰርዟል እንዲሁም ንዑስ 1/ሀ/ መጨረሻ ላይ ወይም የሚል አያያዥ ቃል ተጨምሯል፡፡

ምክንያቱም የሠዋሰው ችግር ስለሚያመጣ እና ድጋሜ ስለሆነ ነው፡፡

5.224. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 249 በተስተካከለው አንቀጽ 246/3/ እና መመዝገብ ይኖርበታል የሚለው ይመዘግባል በሚል ተተክቷል፡፡

ምክንያቱም በትዕዛዝ መንገድ መቀመጥ ስለሌለበት ነው፡፡

5.225. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 250/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 247/3/ እንዲሰማ ያዛል የሚለው ይሠማል በሚል ተስተካክሏል፡፡

ምክንያቱም በትዕዛዝ መንገድ መቀመጥ ስለሌለበት ነው፡፡

5.226. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 252/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 249/3/ ምስክሮች ከሚለው ቀጥሎ ስም ፆታ እድሜ ዜግነት ስራና አድራሻ የሚሉት ተሰርዘዋል፡፡ እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ 2 ማመልከት ይኖርበታል የሚለው ይገልፃል በሚል ተስተካክሏል፡፡

ምክንያቱም የክርክር መክፈቻ አጭር መግለጫ ስለሆነ እና እነዚህ ነገሮች በክሱ ላይ ስለተገለፁ በድጋሚ መዘርዘራቸው አስፈላጊ ባለመሆኑ እና የቃላት ግድፈት ስለነበረበት ነው፡፡

5.227. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 253/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 250/1/ ይረጋገጣል የሚለው ያስረዳል በሚል ፤ ንዑስ **2** እንደነገሩ ሁኔታ የሚለው ተሰርዟል፤ ንዑስ 3 በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር የሚለው ተሰርዟል ፤ንኡስ 4 እና 5 የወጡ ሲሆን በተጨማሪም ንዑስ **4** እና **5** ወደ አንቀጽ **2** ዋና የትርጉም ክፍል ላይ ተደንግጓል፣

ምክንያቱም ትርጉም ስለተሰጠውና ድጋሜ ስለሚሆን ነው፡፡

5.228. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 254/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 251/1 / እንደሚከተለው ተስተካክሏል፡፡

**251/1/**በጭብጥ የተያዘውን ወይም አግባብነት ያለውን ፍሬ ነገር የሚያስረዳ ወይም የሚያስተባብል የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ አግባብነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡

ምክንያቱም የግልፅነት ችግር ስለነበረበት ነው፡፡

5.229. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 254 በተስተካከለው አንቀጽ 251 /2/ ረ የሆነ ፍሬ ነገር የሚለው እና "ሰ" ላይ ፍሬ ነገር የሚለው ተሰርዟል፡፡

ምክንያቱም- የአካባቢ ሁኔታ በራሱ ፍሬ ነገር ስለሆነ ነው፡፡

5.230. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 255 በተስተካከለው አንቀጽ 252 በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል፡፡

**<u>አንቀፅ 252 ጠቅላላ</u>**

በተከሳሹ በግልጽ የታመነ ፍሬ ነገር ፣ፍርድ ቤት ግንዛቤ የሚወስድበት ወይም የሕግ ግምት የሚወስድበት ፍሬ ነገር ለማስረዳት ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልግም ፡፡

ምክንያቱም የሕሊና ግምት የሚለው በሕግ ግምት መተካት ስላለበት ነው፡፡

5.231. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 256 በተስተካከለው አንቀጽ 253 ንዑስ 3 ሆኖ የሚከተለው አዲስ ድንጋጌ ተጨምሯል፡፡

253/3/ ተከሳሹ በምርመራ ወቅት ለፖሊስ የሰጠው ቃል እንደታመነ ፍሬ ነገር አይቆጠርም፡፡

ምክንያቱም በፍርድ ቤት እንደታመነ ይቆጠራል ከተባለ ተከሳሹ ለሠብዓዊ መብት ጥሰት እንዳይጋለጥ ለማድረግ ነው፡፡

5.232. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 257(1) በተስተካከለው አንቀጽ 254/1/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል፡፡ እዚሁ ንኡስ አንቀጽ 3 ላይ ማቅረብ ይኖርበታል የሚለው ያቀርባል በሚል ተስተካክሏል፡፡

254(1) በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ወይም በክልል ጋዜጣ ታትመው የወጡ ህጎች፣ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠባቸው የታተሙ ውሳኔዎች ወይም በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረገፅ የተጫኑ ውሳኔዎች እንደተረጋገጡ ይቆጠራሉ፡፡

ምክንያቱም በፍርድ ቤት ግንዛቤ የሚወሰድባቸው ፍሬ ነገር የፌ/ጠ/ቤት ሰበር ሰሚ የህግ ትርጉም እንዲካተት መደረጉ የመጀመሪያው የሰበር ውሳኔዎች እንደ ሕግ ስለሚቆጠሩ ሲሆን ሁለተኛው ውሳኔዎች ካልታተሙ ተደራሽ ስለማይሆኑ ነው እንዲሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የታተሙ አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞችም የሚለው የታተሙ የሚለው በድረ ገፅ የታጫኑትንም እንደሚያካትት በግልፅ መደንገግ ስላለበት ነው፡፡

5.233. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 258 በተስተካከለው አንቀጽ 255 ከርእሱ ጀምሮ ያለው የህሊና ግምት የሚለው ቃል እንዲሁም በሶስቱም ንኡስ አንቀጾች ላይ የተቀመጠው የህሊና ግምት የሚለው ቃል የህግ ግምት በሚል ተስተካክሏል፡፡

ምክንያቱም በተለምዶ የሕሊና ይባላል እንጅ የሚወሰደው የሕግ ግምት ስለሆነ ነው፡፡

5.234. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 260 በተስተካከለው አንቀጽ 257 /1/ሀ/ በሚከተለው ተስተካክሏል፡፡

በማስገደድ የተገኘ የእምነት ቃል እና ሌላ ማስረጃ፣ እንዲሁም ፊደል ተራ ለ ላይ ያለው በምርመራ ላይ የሚለው ተሰርዟል፡፡ እንዲሁም ፊደል ተራ መ ላይ ተከሳሽ ተጎጂን ለመርዳት ወይም አንድን ጉድለት ለማሻሻል ያደረገው ተግባር ወይም የወሰደው የእርምት ርምጃ፣በሚል ተስተካክሏል፡፡

ምክንያቱም ልዩ ማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ለምርመራ እንደሚያገለግል ስለሚታወ እና የግልፅነት ችግር ስለነበረበት፡፡

5.235. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 260/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 257/2/ በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል። በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀፅ/1/ የተደነገገው ቢኖርም ማስረጃው የዐቃቤ ህግ ምስክር ምስክርነቱን በሚሰጥበት ጊዜ የምስክርነት ቃሉን ለማስተባበል ተቀባይነት ይኖረዋል፡

ምክንያቱም የግልጽነት ችግር ስለነበረበት ነው።

5.236. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 261/1/ እና /2/ በተስተካከለው አንቀጽ 258/1/ እና /2/ የሆነውን ወይም የሚለው ተሰርዟል። ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 በሚከተለው አግባብ ተስተካክሏል።

258(2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም አቃቤ ህግ የተከሳሹ ጠባይ መልካም መሆኑን ለማሳየት የቀረበ ማስረጃ ወይም ክርክር ለማስተባበል የተከሳሹን መልካም ያልሆነ ፀባይ ማስረዳት ይችላል።

258(3) **ተከሳሽ የተጎጅውን መልካም ያልሆነ ጠባይ ለማሳየት ማስረጃ ወይም ጥያቄ ካቀረበ ዐቃቤ ሕግ የተጎጅውን መልካም ጠባይ ወይም የተከሳሹን መልካም ያልሆነ ጠባይ ማስረዳት ይችላል፡፡**

ምክንያቱም በአቃቤ ህግ የወንጀል ተግባርን ለማስረዳት መልካም ጠባይን ማስረዳት ስለማይገባ እና ለድርጊቱ ጋር ግንኙነት ስለማይኖረው ነው። እንዲሁም በንዑስ ሁለት ተከሳሹ መልካም ጠባይ እንዳለው እንደመከራሪያ ካቀረበ አቃቤ ህግ ማስረጃው ለማስባበል መልካም ጠባይ እንደሌለው ማስረዳት ይችላል።የተጎጅን ጠባይ ማስረዳት ወንጀል ለመፈፀም ምክንያት መሆን ስለማይገባ ነው።

5.237. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 262 በተስተካከለው አንቀጽ 259 ይኖረዋል የሚለው አለው በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም የሰዋሰው ግድፈት ስለነበረበት ነው።

5.238. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 263 እና 266 በተስተካከለው አንቀጽ 260/1/ እና 2/ እና 263/1/ የዐቃቤ ሕግ የሚለው ቃል እና 263/2/ ላይ የሚመለከት መሆን አለመሆኑን የሚለው ሀረግ ተሰርዟል።

ምክንያቱም ምስክር የመሆን ብቃት እና ግዴታ ለተከሳሽም ስለሚያገለግል ነው።

5.239. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 264 በተስተካከለው አንቀጽ 261 በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል።

1. የተከሳሹ የሀይማኖት አባት ጠበቃ ወይም ሀኪም በሚሰጠው ሀይማኖት ወይም የሙያ አገልግሎት አጋጣሚ ባገኘው መረጃ ላይ አንድ ሰው በትዳር ዘመኑ ከትዳር አጋሩ ባገኘው መረጃ እና ከወላጅ ወይም ከልጁ ባገኘው መረጃ ላይ የአቃቤ ህግ ምስክር ሆኖ በተከሳሹ ላይ እንዲመሰክር አይገደድም።
2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ቢኖርም አንደኛው የትዳር አጋር ወይም ወላጅ ወይም ልጅ በሌላኛው ላይ ወንጀሉን በፈፀመ ጊዜ ይህ ልዩ መብት ተፈፃሚ አይሆንም።
3. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ቢኖርም ሚስጥር የመጠበቅ የሙያ ግዴታን ወይም ልዩ መብትን በምክንያትነት መጠቀም የማይቻል ስለመሆኑ በህግ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

ምክንያቱም በሌላ ህግ በግልፅ እነዚህን ጉዳዮች እንደመከላከያ ወይም አንደ ምክንያት ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ በተደነገገ ጊዜ እነዚያ ህጎች ከዚህ ህግ ጋር ተነባቢ መሆን ስላለባቸው እና የቤት ውስጥ ጥቃት በትዳር አጋር እና በወላጆችና በልጅ መካከል በሚፈፀምበት ጊዜ ምስክር ማግኘት አስቸጋሪ እንዳይሆን ነው።

5.240. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 265 በተስተካከለው አንቀጽ 262/1/ ተሰርዟል።

ምክንያቱም በልዩ ዘዴ ማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የተሳተፈ ሰው ብቸኛ ምስክር በሚሆንበት ጊዜ ማስመስከር እንዲቻል ለመፍቀድ ነው።

5.241. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 266 በተስካከለው 263/2/ ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 263/3/ ሆኖ ተጨምሯል።

አንቀጽ 266/3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሠረት ጉዳዩ በግልፅ ችሎት ቢታይ የሀገርን ደሕንነት፣ የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ ነው ተብሎ ሲወሰን ጉዳዩ በዝግ ችሎት ይታያል።

ምክንያቱም የሀገርን ደህንነትን የሚጎዳ መሆኑን አለመሆኑን ብቻ ሳይሆን የሚጎዳ ሆኖም ከተገኘ በዝግ ችሎት እንዲታይ ለማድረግ ነው።

5.242. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 267/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 264/1/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

264/1/ በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት የምስክርነት ቃል የሠጠ ሰው የሞተ እንደሆነ፣ የአእምሮ ጉድለት ካገኘው፣ ምስክሩን ማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት ፍርድ ቤት መቅረብ ያልቻለ እንደሆነ የሰጠው የምስክርነት ቃል ተነቦ በማስረጃነት ይያዛል።

ምክንያቱም የሰዋሰው ግድፈት ስለነበረበት ነው።

5.243. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 268 በተስተካከለው አንቀጽ 265/2/ የፖሊስን የምርመራ መዝገብ የሚለው 'የምስክሩን ቃል' በሚል ተተክቷል። በተጨማሪም የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የአቃቤ ህግ ምስክር ከሚለው በፊት የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ በሚል እንዲስካከል ተደርጓል።

ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ እንዲያየው የተፈለገው ሙሉ በሙሉ የምርመራ መዝገቡን ሳይሆን የምስክርነት ቃሉን ስለሆነ እና በተጨማሪም ግልጽነት እንዲኖረው ለማድረግ ነው።

5.244. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 270 በተስተካከለው አንቀጽ 267 ርዕስ ላይ ስለ የሚለው ቃል ተሰርዟል። እንዲሁም በንዑስ **1** መፈፀም የሚለው ቃል ይፈፅማል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም የሠዋሰው ግድፈት ስለነበረበት ነው

5.245. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 271/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 268 /3/ የሚያስከትለውንም ቅጣት የሚለው ተሰርዟል።

ምክንያቱም የቃሉ መግባት አላስፈላጊ ነው

5.246. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 272 በተስተካከለው አንቀጽ 269 /2/ሐ/ ማንኛውም የሚለው አስፈላጊውን በሚለው ተተክቶ ወይም የሚለው ተሰርዞ በነጠላ ሰረዝ ተተክቷል።

ምክንያቱም የሠዋሰው ግድፈት ስለነበረበት ነው።

5.247. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 274 በተስተካከለው አንቀጽ 271(1) ሁለተኛው መስመር ላይ ምስክሩም በጭብጥ ስለተያዘው ወይም አግባብነት ስላለው ፍሬ ነገር በቀጥታ ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚል ሀረግ እንዲጨመር ተደርጓል።

ምክንያቱም ምስክር ሁልጊዜ በቀጥታ ያየውን ብቻ ሳይሆን ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ስላየው ወይም ስላወቀው ጉዳይ እንዲመስክር ማድረግ አስፈላጊ ነው። ምስክርነቱን የመመዘን ሀላፊነት የፍርድ ቤቱ ይሆናል።

5.248. ረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 275 በተስተካከለው አንቀጽ 272 /2/ ወይም አስተያየት የሚለው ሀረግ ተሰርዟል።

ምክንያቱም ሀረጉ አስፈላጊ ስላልሆነ ነው።

5.249. የረቂቅ ህጉ አንቀጽ 276 በተስተካከለው አንቀጽ 273 ባሕርይን የሚለው የፊደል ግድፈት ስላለበት ባሕሪ በሚል፣ ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ትክክለኛው የቃሉ አጻጻፍ ለመጠቀም ነው።

5.250. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 277/4/ በተስተካከለው 274/4/ ተሰርዟል።

ምክንያቱም መሪ ጥያቄ በድጋሚ ጥያቄ ጊዜ መፈቀዱ ስህተት ስለሆነ ነው።

5.251. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 278 በተስተካከለው አንቀጽ 275 በማናቸውም ጊዜ የሚለው ተሰርዟል።

ምክንያቱም ለቃላት አጠቃቀም ምቹ ባለመሆኑ ነው።

5.252. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 279 ንኡስ/4/ በተስተካከለው 276/4/ ቃሉን የሰጠ ከሚለው ቀጥሎ የአቃቤ ህግ የሚለው ተሰርዟል።

ምክንያቱም ምስክሩ የአቃቤ ህግ ብቻ ሳይሆን የተከሳሽም ሊሆን ስለሚችል ነው።

5.253. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 281(2) በተስተካከለው አንቀጽ 278 /2/ ላይ ማረጋገጥ ይኖርበታል የሚለው ያረጋግጣል በሚል፣ ንዑስ 5 መመዝገብ ይኖርበታል የሚለው ይመዘግባል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም ትክክለኛውን አገላለጽ ለመጠቀም ነው።

5.254. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 282 በተስተካከለው አንቀጽ 279 ርዕስ ላይ ስለ የሚለው ቃል ተሰርዟል። እንዲሁም አንቀጽ 282/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 274/2/ ተከሳሽ አግባብ ሆኖ የተገኘ መቃወሚያ ያነሳ እንደሆነ የሚለው ተቃውሞ ከቀረበበት በሚል ሲተካ፤ ዐቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃን በማስረጃነት ከማሰማቱ በፊት የሚለው ይሰረዛል። እንዲሁም ማሰሪያ አንቀፁ ማረጋገጥ ይኖርበታል የሚለው ያረጋግጣል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም ማስረጃ ከተሰማ በፊትም ሆነ በኋላ ሰነዱ ተቃውሞ ከተነሳበት ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ መደንገግ ተገቢ ስለሆነ ነው።

5.255. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 282/4/ በተስተካከለው አንቀጽ 279/4/ ወይም በሰነዱ ግዙፍነት ምክንያት ፍርድቤት ሊቀርብ የማይችል እንደሆነ የሚለው ቋንቋውን በማስተካከል ግዙፍነት ወይም በሚል ሲተካ፤ ንዑስ 5 ስለይዘቱ የሚለው የሰነዱን ይዘት እንዲሁም ንዑስ 6 ዐቃቤ ሕግ የሚለው በስህተት የገባ ስለሆነ ተከሳሽ በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም የሰዋሰው ግድፈት ስለነበረበትና አፃፃፉንም ለማስተካከል ነው።

**5.256.** የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 283 በተስተካከለው አንቀጽ 280 ርእስ ላይ ስለ የሚለው ተሰርዟል። እንዲሁም በንኡስ 1 ማስረዳት ይችላል የሚለው ያስረዳል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም ትክክለኛው አገላለፅ ይህ በመሆኑ ነው።

5.257. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 284 በተስተካከለው አንቀጽ 281/1/ በተቀመጠው ከሚለው ቀጥሎ ጊዜ የሚለው ቃል ተሰርዟል።

ምክንያቱም ሁለት ጊዜ ስለተፃፈ ነው።

**5.258.** የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 285/2/ እና 288/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 282/2/ እና 285/2/ ተቃዋሚው የሚለው ቃል በተቃራኒው ተተክቷል።

ምክንያቱም ትክክለኛው ቃል ስለሆነ ነው።

5.259. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 288 በተስተካከለው አንቀጽ 285 ርዕስ እና አንቀፅ 289 በተስተካከለው አንቀጽ 286 ርዕስ እና ንዑስ 1/ሐ/ የሕሊና የሚለው የሕግ በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም የሕሊና ሳይሆን የሕግ መሆን ስላለበት ነው።

5.260. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 290 ተሰርዟል።

ምክንያቱም ዐቃቤ ሕግ ክስ ከመመስረቱ በፊት ማስረጃዎቹ በሕግ አግባብ መሰብሰባቸውን ማረጋገጥ ስላለበትና የተከሳሾችን መብት በእጅጉ ስለሚያጠብ ነው።

5.261. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 292 በተስተካከለው አንቀጽ 288/1/ ፍሬ ነገር ፣ በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር የሚሉት ተሰርዘዋል። በዚሁ አንቀጽ ንዑስ 2 ውስጥ የሚለው ቃል ተሰርዟል፤ እንዲሁም ማስረጃ ያካትታል የሚለው ማሠሪያ አንቀጽ ፍሬ ነገር ነው በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም የቃላት ድግግሞሽ ስላለው ነው።

5.262. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 293 በተስተካከለው አንቀጽ 289 ርዕስ ስለ የሚለው ተሰርዟል ፤ እንዲሁም ንዑስ 2 ላይ ወረቀት የሚለው ሰነድ በሚል የተተካ ሲሆን ንዑስ 4 እና 5 ቅደም ተከተላቸው እንዲቀያየር ሆኗል።

ምክንያቱም የማስረጃ ዓይነት ሰነድ እንጅ ወረቀት በመባል ስለማይታወቅ ነው።

5.263. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 295 በተስተካከለው አንቀጽ 291/1/ ማረጋገጥ ይኖርበታል የሚለው ያረጋግጣል በሚል ሲስተካከል፤ንዑስ 2 ላይ እንደ የሚለው ቃል ተሰርዞ ማሳየት ከሚለው ቃል በኋላ ወይም የሚል የተጨመረ ሲሆን ምስክር ማስመስከር የሚለው በምስክር ማስረዳት በሚል ቃል ተተክቷል፡፡

ምክንያቱም ድንጋጌው የሰዋሰው ችግር ስለነበረበት ነው ፡፡

5.264. ከረቂቅ ሕጉ ንኡስ ክፍል 5 የአቃቤ ህግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ብይን ከሚለው ርእስ ቀጥሎ አንቀጽ 296 በፊት የተስተካከለው አንቀጽ 292 ሆኖ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ላይ የሚሰጥ አስተያየት በሚል አዲስ ድንጋጌ ተጨምሯል፡፡

<u>አንቀጽ **292** በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ላይ የሚሰጥ አስተያየት</u>

የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተሠምቶ እንዳበቃ ተከሳሽ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ላይ አስተያየት ሊሠጥ ይችላል፡፡

ምክንያቱም ለተከሳሹ በቀረበበት ማስረጃ ላይ ያለውን አስተያየት እንዲያቀርብ እድል ለመስጠት ነው፡፡

5.265. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 297 በተስተካከለው አንቀጽ 293 ርዕስ የፍርድቤት ብይን የነበረው ብይን ብቻ ሆኗል፡፡ ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ወይም በአማራጭ ሊያስከስሰው ወይም ሊያስቀጣው የሚችል የሚል ሀረግ ተጨምሯል፡፡

ምክንያቱም ብይን በፍርድ ቤት እንደሚሰጥ ስለሚታወቅ እንዲሁም ክስ እና ቅጣት በአማራጭ ሊቀርብ ወይም ሊያስቀጣ ስለሚችል ነው፡፡

5.266. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 298/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 294/2/ የቀረበው የመከላከያ ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ጭብጥ እና የማስረጃ የሚል ሀረግ ተጨምሯል፡፡ እንዲሁም የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 298/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 294/3/ ውሳኔውንም የሚለው ይህንንም በሚል ተተክቷል፡፡

ምክንያቱም በተከሳሽ የሚቀርብ ጭብጥ የተዘለለ ስለነበር እና መግለጫ የሚለው የማስረጃ መግለጫ መሆኑን እንዲያመለክት ነው፡፡

5.267. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 299 በተስተካከለው አንቀጽ 295/1/ ምስክሮች ከሚለው ቀጥሎ ከመቅረባቸው የሚለው ቃል ከመሰማታቸው በሚል ተተክቷል፡፡

ምክንያቱም የተሻለው አገላለጽ ይሄ ስለሆነ ነው፡፡

5.268. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 300/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 296/2/ በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል፡፡

296/2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 ቢኖርም ተከሳሽ በዐቃቤ ሕግ ወይም በፖሊስ እጅ የሚገኝ ማስረጃን በመለየት ወይም በጥቅሉ እንዲሰጠው በማንኛውም ጊዜ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

ምክንያቱም ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ ፍርድቤቱ ትዕዛዝ የመስጠት ሥልጣን እያለው ግምት መውሰዱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ስለማይረዳ ነው፡፡

5.269. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 301 በተስተካከለው አንቀጽ 297/3/ አለመሆን ወይም አለመፈፀም የሚሉት ቃላቶች መከሰት ወይም አለመከሰት በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ለማስረጃ አገላለፅ ተገቢ የሆነ መከሰት ወይም አለመከሰት የሚለው ስለሆነ ነው።

5.270. የረቂቅ ሕጉ ከአንቀፅ 302 በተስተካከለው አንቀጽ 298 በምዕራፍ ሁለት የሚለው በምእራፍ ሶስት በሚለው ተተክቷል።

ምክንያቱም ስለአቃቤ ህግ ማስረጃ የሚደነግጉት አንቀጾች የሚገኙት በምእራፍ 3 ላይ በመሆኑ ነው።

5.271. ከረቂቅ ህጉ አንቀጽ 302 በተስተካከለው አንቀጽ 298 ቀጥሎ ምእራፍ ሶስት የተጻፈው ምእራፍ 5 በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም የምዕራፉ ቅደም ተከተል ለማስተካከል ነው።

5.272. የረቂቅ ሕጉ ከአንቀፅ 307 በተስተካከለው አንቀጽ 303 ይስተካከላል የሚለው ቃል ያስተካክላል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም የሠዋሰው ግድፈቱን ለማረም ነው።

5.273. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 310/5/ በተስተካከለው አንቀጽ 307/5/ ማጣቀሻ ቁጥሮቹ 3 እና 4 ሆነው የተስተካከሉ ሲሆን የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚለው መሠረት በሚል ተተክቷል። በተጨማሪም በንዑስ 6 የሚከተለው ተጨምሮ ንዑስ 6 የነበረውንዑስ 7 ሆኗል።

307/6/ ፍርድ ቤቱም የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ማስረጃዎችን በፍትሐብሔር የማስረዳት መጠን ይመዝናል።

ምክንያቱም መሠረት የሚለው የተተካው ልዩ ሁኔታ ስላልሆነ እና የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ የሚመዘንበት አግባብ የተደነገገ ስላልነበረ ነው።

5.274. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 311 በተስተካከለው አንቀጽ 308/2/ በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል። በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ቅጣቱን ለመወሰን ቀጠሮ ሲሰጥ ተከሳሽ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ወይም በገንዘብ መቀጮ ብቻ የሚያስቀጣ ከሆነ በዋስ እንዲቆይ ሊያዝ ይችላል።

ምክንያቱም የጥፋተኝነት ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በዋስ እንዲቆይ ማድረግ ቅጣቱን እንዳይፈፅም እድል የሚሰጥ ነው በተጨማሪም እስራትን የማያስከትል ከሆነ ግን ለገንዘብ መቀጮ ብቻ ተከሳሽን ወደ ማረፊያ ቤት መላክ አግባብነት ስለሌለው በልዩ ሁኔታ እንዲደነገግ ሆኗል።

5.275. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 312/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 309 /1/ በነጠላ አፃፃፍ ርምጃዎቹ የሚለው እርምጃ በሚል ሲተካ፤ ንዑስ 2 በዚህ ህግ ከሚለው እና በወንጀል ሕግ የሚል ተጨምሯል።

ምክንያቱም ቅጣት የሚተላለፍበት አግባብ በወንጀል ሕግም ጭምር ስለተደነገገ ነው።

5.276. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 314/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 311/1/ ማስተላለፍ ይኖርበታል የሚለው ያስተላልፋል በሚል የተተካ ሲሆን ይግባኝ ከተባለበት ወይም የሚለው ተሰርዟል፤ ያልተባለበት እንደሆነ የሚለው ካልተባለበት በሚል የተስተካከለ ሲሆን ማሰሪያ አንቀጹ ላይ ፍርድ ቤቱ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያለው ስልጣን ይኖረዋል የሚል ተጨምሯል።

ምክንያቱም ይግባኝ ከተባለበት በይግባኝ ሠሚው የሚታይ ሲሆን ይህን መደንገግ ያስፈለገው የሞት ቅጣት ስለሆነ እና ይግባኝ ካልቀረበበት አግባብነቱ በድጋሜ መታየት ስላለበት ነው።

5.277. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 314/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 311/2/ ተሰርዟል። በመሆኑም ንዑስ አንቀፆቹ ተሸጋሽገዋል።

ምክንያቱም በንኡስ አንቀፅ 1 ስለተሸፈነ ነው።

5.278. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 317/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 313/3/ መስጠት ይኖርበታል የሚለው ይሰጣል በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም በትዕዛዝ መልክ ማስቀመጥ አግባብ ስላልሆነ።

5.279. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 318/1/ለ/ በተስተካከለው አንቀጽ 314/1/ለ/ በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል። ህጻን ልጅ ያላት እናት ልጁ ሰላሳ ወር እስኪሞላው ድረስ፣ እንዲሁም ንዑስ ሐ ላይ ሕፃኑ እንዲሁም ሠ ላይ ጀምሮ የሚል ቃል ተጨምሯል።

ምክንያቱም 18 ወር ያልሞለው ልጅ ያላትን እናት ቅጣት ስለማስተላለፍ በሂደት የተሳሳተ ውጤት እንዲኖረው ሆኖ የተደነገገ በመሆኑ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ 30 ወራት ያልሞላው ልጅ ያላት እናት ልጁ 30 ወራት እስኪሞላው ድረስ ቅጣቱን ማስተላለፉ አመክንዮ ያለው ሆኖ በመገኘት ነው እና ሕፃኑ የሚለው ዐረፍተ ነገሩን የተሟላ ለማድረግ ነው።

5.280. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 318/1/ረ/ በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል። ቤተሰቡን የሚንከባከብ ሌላ ሰው ከሌለና ባልና ሚስት በተመሳሳይ ወይም በተለያየ ጊዜ የተፈረደባቸው እንደሆነ የአንደኛው ወላጅ ቅጣት ለሶስት ወር ላልበለጠ ጊዜ፣

ምክንያቱም አገላለጹን የተሻለ ለማድረግ ነው።

5.281. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 319/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 315/2/ የሚከተለው አዲስ ድንጋጌ ተጨምሯል። ቀሪዎች ንኡስ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል።

315/2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ፍርድ ቤቱ ቀሪ ከማድረጉ በፊት የፍርደኛውን አስተያየት ይቀበላል።

ምክንያቱም በእኩል የመሰማት እድልን ለመስጠት ነው።

5.282. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 319/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 315/3/ ውስጥ ስለ አመክሮ እና ስለ ዋስትና የተደነገገው ተሰርዟል።

ምክንያቱም  የዋስትናው በንዑስ 4 ላይ ስለተደነገገ ድጋሜ ስለሚሆን እና የአመክሮ ጉዳይ በፍሬ ነገር ሕግ የሚገዛና የሚተዳደር ስለሆነ እና በዚህ የስነስርዓት ሕግ ውስጥ መደንገግ ስለሌለበት ነው። እንዲሁም አመክሮ የሚሰጠው የቅጣቱን 2/3 ኛ ለጨረሰ ታራሚ ሲሆን አላማው የታራመሚው አመል የበለጠ እንዲሻሻል እድል መስጠት ነው ስዚህ አንድ ታራሚ የቅጣቱን 2/3 ኛ ከጨረሰ በኋላ መልካም ጸባይ ካሳየ/ከኖረው የአመክሮ እድል ቢሰጠው ጸባዩን የበለጠ ሊያሻሽለው የሚችል ይሆናል እጂ አይጎዳውም፤ እንዲሁም የታራሚዎች አስፈላጊውን መስፈርቶች ካሟሉ በኋላ በአመክሮ መለቀቅ በርካታ አስተዳደራዊ ችግሮችን ከመቅረፍ አልፎ የመንግስትን (የህዝብን) ወጪ የሚቀንስ ይሆናል።

5.283. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 324/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 320/3/ ሰው ከሚለው ፊት ማንኛውም የሚል ተጨምሯል እንዲሁም ከሚያረጋግጥ የሚለው ከሚያሳይ በሚል እና ተያይዞ የሚለው አያይዞ እንዲሁም መቅረብ ይኖርበታል የሚለው ያቀርባል በሚል እንዲሁም ንዑስ 5 ላይ መስጠት ይኖርበታል የሚለው ይሰጣል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም  የሠዋሰው ግድፈት ስለነበረበት ነው።

5.284. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 324 በተስተካከለው አንቀጽ 320/6/ሀ/፣ሐ እና መ ላይ የንብረቱ መኖር ከዕውቅና ውጭ መሆኑና የንብረቱ ዝርዝር ያልቀረበው ከአቃቤ ህግ እውቅና ውጭ በሆነ ሥህተት በመሰራቱ ወይም የሚለው ተሰርዟል።

ምክንያቱም በአንድ ወንጀል ድጋሚ ያለመክሰስ መርህን ስለሚጥስ ነው።

5.285. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 328/2/ሀ/ በተስተካከለው አንቀጽ 324//2/ሀ/ መጨረሻ ላይ ያለው ከሆነ የሚለው ቃል መሆኑ በሚል ተተክቷል፡፤

ምክንያቱም ትክክለኛው አገላለጽ ይህ ስለሆነ ነው።

5.286. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 333/1/ለ/  በተስተካከለው አንቀጽ 329/1/ለ/ ሊነገር የሚለው ቃል ሊገለፅ በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ትክክለኛው የቋንቋ አጠቃቀም ይኸኛው ስለሆነ ነው ።

5.287. ከረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 333 በተስተካከለው አንቀጽ 329 ቀጥሎ የምእራፍ አንድ ርእስ ስለማየት የሚለው ማየት በሚለው ተተክቷል።

ምክንያቱም ትክክለኛው አገላለጽ ይህ ስለሆነ ነው።

5.288. የረቂቅ ሕጉ ከአንቀፅ 338 /3/ በተስተካከለው አንቀጽ 334/3/ ይሆናል የሚለው በ ነው ተተክቷል።

ምክንያቱም ዓላማ የሚገፈው በዚህ መልኩ ስለሆነ ነው።

5.289. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 338/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 334/1/ ጠበቃው ከሚለው ቀጥሎ ብቻ የሚለው ተሰርዟል፤ ይሆናል የሚለው ናቸው በሚል ተተክቷል እንዲሁም 338/3/ ፍርድ ቤት ከሚለው ቀጥሎ ይሆናል የሚለው ነው በሚለው ተተክቷል ።

ምክንያቱም ትክክለኛውን አገላለጽ ለመጠቀም ነው።

5.290. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 339/1/ለ/ በተስተካከለው አንቀጽ 335/1/ለ/ የተከሳሽ የዋስትና መብት ላይ በተሰጠ ውሳኔ በሚል ተስተካክሏል።።

ምክንያቱም ዋስትና ሕገ መንግስታዊ መብት ስለሆነ ይግባኝ እንደሚባልበት ለማመላከት ነው።

5.291. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 340/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 336/1/ ሐ፣ሠ፣ረ፣ሰ፣ሸ፣ቀ የተሰረዙ ሲሆን መ እና ሠ ሐ እና መ ሆነው ተሸጋሸገዋል። ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) በተሸጋሸገው ንዑስ አንቀጽ 1(መ) ተከሳሽ በሌለበት በተሰወነ ጉዳይ ክርክሩ እንዲገባ በተሰጠ ውሳኔ፤

ምክንያቱም የተሰረዙት ዝርዝሮች ይግባኝ ሊቀርብባቸው ስለሚችሉ ነው።

5.292. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 341/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 337/1/ **3** የሚለው በ 5 ተተክቷል።

ምክንያቱም አጭር ጊዜ ነው የሚል በርካታ አስተያየት ስለተሰጠበት ነው ።

5.293. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 342 በተስተካከለው አንቀጽ 338/1/ በማንኛውም ጊዜ የሚለው ተሰርዟል።

ምክንያቱም በድጋሚ የተፃፈ ስለሆነ ነው።

5.294. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 344/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 340/1/ መስጠት ይኖርበታል የሚለው በይሰጣል ተተክቷል፤ ንዑስ 5 ማጣቀሻው 3 የነበረው በ 4 ተተክቷል፤ እንዲሁም በነባሩ 345 በተስተካከለው 341/1/ መጨረሻ ላይ መልክ የሚለው መልኩ በሚል መቅረብ ይኖርበታል የሚለው ይቀርባል፤ንዑስ 2 መግለፅ ይኖርበታል የሚለው ይገልፃል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም የሰዋሰው ግድፈት እና ማጣቀሻው ስህተት ስለነበረበት ነው።

5.295. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 346/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 342/2/ መጀመሪያ ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የሚል ተጨምሯል።

ምክንያቱም ትክክለኛው የድንጋጌው አገለጽ ይህ ስለሆነ ነው።

5.296. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 347/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 343/3/ ሆኖ አዲስ ንኡስ አንቀጽ እንደሚከተለው ተጨምሯል። ንኡስ አንቀጽ 3 የነበረው ወደ ንኡስ አንቀጽ 4 ተሸጋሽጓል።

አንቀፅ 343 /3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ ይግባኝ ለመጠየቅ ያልቻለበት በቂ ምክንያቱ ከተወገደለት በኋላ በ 1 ወር ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ማቅረብ አለበት።

ምክንያቱም የይግባኝ ማስፈቀጃ የሚባልበትን የጊዜ ገደብ ለማስቀመጥ ነው።

**5.297.** የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 348/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 344/2/ እንደሆነ ከሚለው ቀጥሎ ይግባኙን ሰርዞ የሚለው ሀረግ ተሰርዞ እና ይግባኝ ባዩ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ይዘጋል በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም መዝገቡን ስለመሰረዝ ሳይሆን መዝገቡን ስለመዝጋት ለመደንገግ ነው፡፡

5.298. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 355/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 351/1/ የፌዴራል የሚለው ተሰርዟል፡፡

ምክንያቱም የፌዴራል ብቻ ሳይሆን የክልልንም ስለሚጨምር ነው፡፡

5.299. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 357 ተሰርዟል፡፡ ሌሎቹ እንደ ቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል፡፡

ምክንያቱም የይግባኝ ሥርዐትን የተከተለ ስላልሆነ ነው፡፡

5.300. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 358/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 353/1/ ሠበር የሚለው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠበት በሚል ተተክቷል፡፡ በተጨማሪም በአዲስ ንዑስ አንቀጽ 3፣6፣7 እና 8 የሚል ተጨምሯል፤ ንዑስ አንቀፆች እንደ አግባብነታቸው ተሸጋሽገዋል፡፡

353 /3/ የወንጀል ሕግ በጠቅላላው ክፍል የተደነገጉ መርሆችን በመጣስ፤

353/6/ ለክርክሩ አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለው ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፤

353/7/ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ውድቅ በማድረግ የተወሰነ፤

353/8/ በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት ወይም፤

ምክንያቱም አስገዳጅ የሆነውን መጣስ ነው እንደ ሕግ ጥሰት የሚቆጠረው፡፡ አዲስ የተጨመረው ንዑስ አንቀፅ ሕግ ሙሉ በሙሉ ዓላማውን እንዲያሳካ መርሆቹ በአግባቡ መተርጎም አለባቸው ስለሆነም መርሆቹ በተጣሱ ጊዜ በሰበር ለማስተካከል እንዲቻል ነው፡፡

5.301. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 359 በተስተካከለው አንቀጽ 354 ርዕሱ ለሰበር የማይቀርብ ጉዳይ ተብሎ ተስተካክሏል፡፡

ምክንያቱም የሰዋሰው ግድፈት ስለሚያመጣ ነው፡፡

5.302. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 361 በተስተካከለው አንቀጽ 356 በሆነ ሁኔታ ያካተተ መሆን ይኖርበታል የሚለው ተሰርዞ ይሆናል በሚል ተተክቷል፡፡

ምክንያቱም የሰዋሰው ግድፈት ስለሚያመጣ ነው፡፡

5.303. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 363 በተስተካከለው አንቀጽ 358 ለይቶ የሚለው ቃል እና በሚል ቃል ተተክቷል፡፡

ምክንያቱም የሰዋሰው ግድፈት ስለሚያመጣ ነው፡፡

5.304. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 364/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 359/1/ ውሳኔ የሚለው ፍርድ በሚል ተተክቷል፤ ንዑስ አንቀጽ 2 መጨረሻ ላይ አስገዳጅ የሚሆነውም ፍርዱ ከታተመበት ቀን ጀምሮ ይሆናል የሚል ተጨምሯል፡፡

ምክንያቱም የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 257 በተስተካከለው አንቀጽ 254 ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ነው፡፡

5.305. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 366/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 361 /1/የሚያሳምን በቂ የሚለው ተሰርዞ የሚያሳይ በሚል፤ንዑስ አንቀጽ 2 በቂ ማስረጃ ማለት የሚለው የሚቀርበው በሚል ተስተካክሏል፡፡

ምክንያቱም በስህተት የተሰጠ ፍርድ ከሆነ ስህተት መሆኑን የሚያሳይ ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ነው ሊቀርብ የሚገባው ።

5.306. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 367/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 362/1/ ይችላል የሚለው ይቻላል በሚል ተተክቷል። ምክንያቱም ትክክለኛ የሆነ አገላለጽ ለመጠቀም ነው።

5.307. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 368 በተስተካከለው አንቀጽ 363/2 እና 3/ የተከራካሪ ወገን የሚለው በአቃቤ ህግ ተተክቷል። ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የፍርደኛውን የሚል ቃል ተጨምሯል። ንዑስ አንቀጽ 363/3/ የአቃቤ ህግ መልስ እና የፍርደኛውን ማስረጃ መርምሮ ፍርድ ይሰጣል።

ምክንያቱም ፍርድ እንደገና የሚታይለት ፍርደኛ ስለሆነ እና ተከራካሪ ወገን የሚለውን ግልፅ ለማድረግ ነው።

5.308. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 369/4/ በተስተካከለው አንቀጽ 364/4/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል።

364/4/ የዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ዝርዝር በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል። ደንቡ እስኪወጣ ድረስ አግባብ ያለው ህግ ተፈጻሚ ይሆናል።

ምክንያቱም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መውጣቱ ለካሳ አፈጻጸሙ ከፍ ያለ ፋይዳ ያለው በመሆኑ ነው።

5.309. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 370 በተስተካከለው አንቀጽ 365 ሀ እና ለ ጉዳዮች የሚሉት ቃላት ተሰርዘው ንዑስ 1 ሆነው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 2 የሚከተለው ተጨምሯል።

አንቀፅ 365(2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **1** እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መጽሐፍ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ መደበኛው የክርክር ሥነሥርዓት ተፈፃሚ ይሆናል።

ምክንያቱም ልዩ ሥነሥርዓት ስለሆነ እና በሂደት ክፍተት ቢያጋጥም በመደበኛው ሥነሥርዓት ጉዳዩ እንዲመራ ለማስቻል ነው።

5.310. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 371 በተስተካከለው አንቀጽ 366/1/ መመራት ይኖርበታል የሚለው ይመራል በሚል ፤ ንዑስ 2/ሀ/ መስጠት ይኖርበታል የሚለው ይሠጣል፤ 2/ለ/ ይኖርበታል የሚለው አለበት ፤2/ሐ መታገዝ ይኖርበታል የሚለው ይታገዛል በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ትክክለኛው አገላለጽ ይህ ስለሆነ ነው።

5.311. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 372/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 367/1/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል። የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች በወንጀል ህጉ በተደነገገው አግባብ በወንጀል ነገር ገብተው በተገኙ ወጣቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። የአንቀጹ ንኡስ ቁጥር 2 እና 3 ተሰርዟል፤ንኡስ 4 የነበረው ንኡስ 2 ሆኗል። ምክንያቱም በወንጀል ድርጊት ውስጥ የተገኙ ልጆችን እድሜ በሚመለከት የሚከፋፈለው ወንጀል ሕጉ ስለሆነ ሲሻሻልም በዛው መሰረት እንዲሄድ ለማስቻል ነው።

5.312. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 373 በተስተካከለው አንቀጽ 368/3/ በመቀበል ምርመራ አያደርግም የሚለው አይቀበልም በሚል ሲተካ፤ ንዑስ አንቀጽ 4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚለው

ተሰርዟል። ንዑስ አንቀጽ 6/ሀ/ ተመልሶ የሚለው ቃል ተሰርዟል፤ ሊቀላቀል አለመቻሉ የሚለው እንዳይቀላቀል በሚል ተተክቷል 6/ሐ/ ፈፀመ ተብሎ የሚለው ተሰርዟል።

ምክንያቱም የሰዋሰው ግድፈት ስለነበረበት እንዲሁም አፃፃፉን ለማስተካከል ነው።

5.313. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 376 ተሰርዟል። ሌሎቹም እንደ ቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል።

ምክንያቱም ድጋሚ ስለሆነ ነው።

5.314. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 377 በተስተካከለው አንቀፅ 371/1/ መስጠት የለበትም የሚለው አይሰጥም በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም የተሻለ አገላለጽ ይህ ስለሆነ ነው።

5.315. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 379/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 373/2/ መጨረሻ ላይ ፍርድ ቤት የሚለው ሀረግ እንዲወጣ ተደርጓል።

ምክንያቱም ድግግሞሽን ለማስቀረት ነው።

5.316. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 379/4/ በተስተካከለው አንቀጽ 373/4/ ተነሳሽነት የሚለው ቃል አስተያየት በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም አግባብነት ያለው አገላለጽ ይህ ስለሆነ ነው ።

5.317. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 380/1/ እና /2/ በተስተካከለው አንቀጽ 374/1/ እና /2/ ይኖርበታል የሚለው ቃል ያቀርባል እና ያዛል በሚል ተተክተዋል።

ምክንያቱም አጻጻፉ ትእዛዛዊ ስለነበር ለማስተካከል ነው።

5.318. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 382/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 376/1/ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ክሱ የሚለው ተሰርዞ ጉዳይ በሚል ተተክቷል። እንዲሁም አቃቤ ህግ ክስ የተመሰረተ እንደሆነ መገኘት ይኖርበታል የሚለው ክስ የተመሰረተ እንደሆነ አቃቤ ህግ መገኘት ይኖርበታል በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም የቃላት ድግግሞሽ ስላለው ነው እና ትክክለኛውን አገላለጽ ለመጠቀም ነው።

5.319. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ **386** በተስተካከለው **380** በሚከተለው አግባብ ተስተካክሏል።

<u>**380.**ተፈፃሚነት</u>

1. ደንብ መተላለፍን የሚመለከት ጉዳይ በልዩ ሕግ በተደነገገበት አግባብ ይመራል።
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ 1 ያልተሸፈነ የደንብ መተላለፍን የሚመለከት ጉዳይ በዚህ ክፍል በተደነገገው አግባብ ይመራል
3. በዚህ ምእራፍ የሚለው በዚህ ክፍል በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ደንብ መተላለፍ የሚመራው በልዩ ህጎች ሲሆን በልዩ ህጎች ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ብቻ በልዩ ሁኔታ ይህ ህግ ተፈፃሚ እንዲሆን ነው በተጨማሪም ስለደንብ መተላለፍ የተደነገገው በምእራፍ ሳይሆን በክፍል ስለሆነ ለማስተካከል ነው፣ ፤

5.320. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 393/1/ረ/ በተስተካከለው አንቀጽ 387/1/ረ/ መመለስን የሚለው ቃል ተሰርዟል፣ በአንቀጽ 387/1/ሰ/ በወንጀል ሕጉ በ ማረፊያ ቤት እስራት የሚያስቀጡ በሚል ተተክቷል። ንዑስ አንቀጽ 5 ተሰርዟል። ምክንያቱም ይግባኝ አይባልበትም ማለት ሕገ መንግስታዊ ስላልሆነ ነው።

5.321. የረቂቅ ሕጉ ዘጠነኛ መጽሐፍ አንቀፅ 394 በተስተካከለው አንቀፅ 388 ስምንተኛ መፅሀፍ አንቀጽ 388 ጀምሮ ያሉት ድንጋጌዎች ላይ ሀገሪቱ የሚለው በኢትዮጵያ ተተክቷል። እንዲሁም ጠቅላይ አቃቤ ህግ የሚለው በፍትሕ ሚኒስቴር ተተክቷል።

ምክንያቱም በሌሎች ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ በሚል በመገለጹ እና የሕግ ሰነድ የሚመለከተውን አካል በቀጥታና በማያሻማ መግለጽ ስላለበት ነው። እና በተቋሙ የስያሜ ለውጥ ስለተደረገ ነው።

5.322. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 394 **በተስተካከለው** አንቀፅ 388 ንዑስ 2 እና 389 /2/ በዚህ ክፍል የሚለው በዚህ መፅሐፍ በሚል ተተክቷል ፣እንዲሁም ንዑስ 2 ላይ በፈረመቻቸው የሚለው በአፀደቀቻቸው በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም ስምምነት ተፈፃሚ እንዲሆን ከመፈረም በኋላ በሀገሪቱ ሕግ አውጭ አካል ቀርቦ መፅደቅ ስላለበት ነው።

5.323. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 394/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 388/3/ እንደቅደም ተከተሉ እና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚሉት ተሰርዘዋል። በተጨማሪም የአንቀፁ ርዕስ አላማና ትርጓሜ በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም አንቀፁ ላይ መደንገግ የተፈለገው የዓለም ዓቀፍ ትብብር የሚመለከቱ ጉዳዮች የሚታዩት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድቤት መሆኑን ለማመላከት እና ድንጋጌው ስር ትርጓሜ ስላካተተ ነው።

5.324. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 395/1/ በተስተካከለው 389/1/ ላይ መንግስት የሚለው ቃል ተሰርዟል፣ በፈረመቻቸው ወይም በተቀበለችው የሚለው ተቀብሎ በአፀደቀቻቸው በሚል ተተክቷል። ንዑስ አንቀጽ 3 ሕዝቦች የሚለው በብሔራዊ ተተክቷል።

ምክንያቱም አደረጃጀቱ በመፅሐፍ ስለሆነ እና "የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም" የሚለው ሰፊ ማዕቀፍ ባለው እንዲተካ ማድረግ ስለሚያስፈልግ ነው።

5.325. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 395/2/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 389/2/ ግልጽ የሆነ ዓለም አቀፍ ስምምነት የሌለ ወይም ያልተሟላ እንደሆነ ትብብሩ.... ከሚለው ቀጥሎ 'በሰቶ በመቀበል መርህ እና በዚህ መጽሐፍ በተመለከቱ ድንጋጌዎች መሰረት' የሚል ተጨምሯል።

**ምክንያቱም በሰቶ መቀበል** መርህ ስለሚያገለግል እና በረቂቁ ከተቀመጡት ውጭ ታሳቢ እንዲደረግ ነው።

5.326. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 395/4/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 389/4/ የወራሹን የካሳ ከሚለው ቀጥሎ በነጠላ ሰረዝ ‘የቅን ልቦና ሦስተኛ ወገኖች መብትን’ የሚል ተጨምሯል።

***ምክንያቱም*** የሦስተኛ ወገኖችን መብት ለመጠበቅ ነው።

5.327. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 396/1/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 390/1/ መጀመሪያው ላይ ከመንግስት ጋር የሚለው ተሰርዟል። እንዲሁም የዚሁ አንቀፅ /1/ሐ/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል ‘ለተጠየቀው ትብብር መነሻ የሆነው ጉዳይ በወታደራዊ ሕግ ብቻ የሚያስቀጣ እንደሆነ፣’

***ምክንያቱም*** ትክክለኛ አገላለፁ የጦር ሕግ ሳይሆን ወታደራዊ ሕግ ስለሆነ እና የተሰረዘው ድንጋጌ ደግሞ ቅጣት የመወሰን ሥልጣን ስላለው ፍርድ ቤት ስለሆነ ከድንጋጌው ጋር አብሮ አይሄድም።

5.328. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 396/1/መ/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 390/1/መ/ ይቅርታ በተደረገበት ከሚለው ቀጥሎ በነጠላ ሰረዝ ምሕረት በተደረገበት የሚል ተጨምሯል፣ እንዲሁም ቅጣት ከተጣለበት የሚለው እና መጨረሻ ላይ ያለው ወይም የሚለው ተሰርዟል።

***ምክንያቱም*** ምህረት የተሰጠበት ወንጀል ክስ ስለማይቀርብበት ነው።

5.329. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 396/1/ረ/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 390/1/ረ/ ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል። ‘በሌሎች ሕጎችና ሀገራችን ተቀብላ ባፀደቀቻቸው ስምምነቶች ውስጥ በተካተቱ ሌሎች ምክንያቶች፤’ እንዲሁም ንዑስ 2 ተሰርዟል ፣ ንዑስ 3 የነበረው ንዑስ 2 ሆኗል።

***ምክንያቱም*** ትብብር የማይፈቀድባቸው ጉዳዮች እንደ የሁኔታው ሊለያይ ስለሚችል በሙሉ ዘርዝሮ ማስቀመጥ ስለማይቻል እና ወደፊት በሚኖሩን ስምምነቶች መስፈርቶች ሊጨመሩ ስለሚችሉ ነው።

5.330. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 397/5/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 391/5/ በሚከተለው ተስተካክሏል። ከሦስተኛ ሀገር የሚቀርብ በወንጀል የሚፈለግ ሰው የማስተላለፍ ትብብር መፈጸምን፣

***ምክንያቱም*** የማስተላለፍ ጥያቄ በርካታ ዓይነት ስለሆነ በይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ነው።

5.331. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 397/7/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 391/7/ በሚከተለው ተተክቷል፣ ፍርደኛንና ጅምር የምርመራ እና የክስ ሂደትን ማስተላለፍ፣

***ምክንያቱም*** የተያዘ ሰው ልውውጥ የሚባል የትብብር ዓይነት ባለመኖሩ እና ግልፅ በሆነ መልኩ ለማስቀመጥ ነው።

5.332. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 398/1/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 392/1/ መቅረብና መፈፀም የሚለው ‘ና መፈፀም’ የሚለው ተሰርዟል።

***ምክንያቱም*** የዲፕሎማሲ መስመሩ የመገናኛ መስመር እንጅ ትብብሩን በቀጥታ የሚያስፈፅም ባለመሆኑ ነው።

5.333. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 398/3/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 392/3/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል። ‘በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ዓለም አቀፍ ትብብርን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ፍትህ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ባለስልጣን በመሆን

ይመራል፣ይከታተላል፣ ይወስናል። ይህንንም ሲፈፅም እንደ አግባብነቱ ከሀገር ደህንነትና ፀጥታ አካላትና ሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመመካከር ይሆናል።

**ምክንያቱም** ባፀደቅናቸው የባለብዙ እና የሁለትዮሽ ስምምነቶች ይህን የማስፈፀም ስልጣን የተሰጠው ለፍትህ ሚኒስቴር ስለሆነ እና ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በግልፅ ማስቀመጥ ስላስፈለገ ነው።

5.334. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 401/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 395/2/ በፋክስ ከሚለው ቀጥሎ ወይም መሠል መገናኛ ዘዴዎች የሚል ተጨምሯል።

ምክንያቱም ወደፊት የሚመጡ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችን እንዲሸፍን ስለሚያስችል እንዲካተት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

5.335. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 402/4/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 396/4/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል። ጥያቄው ከንብረት ጋር የተያያዘ እንደሆነ የተወረሰ ወይም የታገደ የንብረት ዐይነትን እና ንብረቱ የሚገኝበት ቦታ፣ በንብረቱ ላይ የተሰጠን ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የፍርድ ቤት የውርስ ውሳኔ ወይም የዕግድት ትዕዛዝ፣'

**ምክንያቱም** በወንጀል የጥፋተኝነት ውሳኔን መሰረት ያላደረገ የንብረት ውርስ ወይም የእግድ ትዕዛዝ ስለሚኖር ነው።

5.336. የረቂቅሕጉአንቀፅ 402/5/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 396/5/ መግቢያው ላይ የወንጀል ጉዳይ እንደሆነ የሚለው ተሰርዟል እንዲሁም ንዑስ 7 መጠናቀቅ የሚለው መፈፀም በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም መጽሐፉ በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ዓለም ዓቀፍ ትብብርን የሚደነግግ ስለሆነ ነው።

5.337. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 403/3/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 397/3/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል። ጥያቄው ተቀባይነት ያለው እንደሆነ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ትብብር ለሚቀርብለት አካል ይልካል።

**ምክንያቱም** ድንጋጌው ክልሎች በራሳቸው ከውጭ ሀገር ጋር ግንኙነት ማድረግ የሚፈቅድ ስለሚመስል እንዲሁም ሕገ መንግስታዊ ስላልሆነ ነው።

5.338. የረቂቁ ሕጉ አንቀፅ 404/1/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 398/1/ ሆነው ከሚለው ቀጥሎ ያለው ሰው ተላልፎ የሚሰጠው የሚለው ተሰርዞ ለትብብር የሚላከው ምስክር በሚል ተተክቷል እንዲሁም እዚሁ አንቀጽ ንዑስ(1)(ሀ) ላይ በጊዜያዊነት ከሚለው ቀጥሎ የተሰጠው የሚለው የሚሰጠው በሚል ተተክቷል፣ተጠያቂ እንደማይሆን ከሚለው ቀጥሎ <<ተላልፎ የተሰጠው ግለሰብ ከትብብር አድራጊ ሀገር ፈቃድ ውጭ ለሌላ ሶስተኛ ሀገር ተላልፎ እንደማይሰጥ>> የሚል ተጨምሯል።

ምክንያቱም በዓለም አቀፍ ደረጃ ካለው አሰራር አንጻር ከሚሰጡ ማረጋገጫዎች ውስጥ አንዱ ይህ ስለሆነ ነው።

5.339. የረቂቁ ሕጉ አንቀፅ 404/1/ለ/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 398/1/ለ/ በሰጠው የሚለው በሚሰጠው በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም የሰዋሰው ችግር ስለነበረበት ነው።

5.340. የረቂቁ ሕጉ አንቀፅ 404/1/መ/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 398/1/መ/ ተሰርዞ ንዑስ ሠ የነበረው 'መ' ሆኗል።

ምክንያቱም ከሀገራት ጋር በሚፈጸም ስምምነት መሰረት የሚወሰን ስለሆነ ነው።

5.341. የረቂቁ ሕጉ አንቀፅ 404/3/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 398/3/ ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል። ለተጨማሪ ጊዜያት ግለሰቡ ወይም ሰነዱ ለትብብር እንዲቆይ ጥያቄ ከቀረበ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይህንኑ ጥያቄ በመመርመር ይወስናል።

ምክንያቱም ለተጨማሪ ጊዜያት እንዲቆይ የሚፈለገው ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች ሊሆኑ ስለሚችል ነው።

5.342. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 406/3/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 400/3/ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚለው ፍትህ ሚኒስቴር በሚል ተተክቷል እንዲሁም ከድርብ ሰረዝ በኋላ ያለው ተሰርዟል። ምክንያቱም በውስጥ አሰራር የሚሸፈን ጉዳይ ስለሆነ ነው።

5.343. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 407/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 401/1/ የነበረው ንዑስ 2 ሲሆን ማሳረጊያው ሊያደርግ ይችላል የሚለው ተሰርዞ በሚከተለው ተተክቷል። ለፍርድቤት ያመለክታል፣ ፍርድ ቤቱም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

ምክንያቱም ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የፍርድቤት ብቻ ስለሆነ።

5.344. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 407/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 401/3/ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው እንደሆነ ከሚለው በኋላ በጊዜያዊነት ሊተላለፍ የሚችለው ፈቃደኛ ሲሆን ብቻ ነው በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ዜጋ የሆነን ሰው ለሌላ ሀገር ለመስጠት ፈቃደኝነት መጠየቅ ስላለበት ነው።

5.345. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 410/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 404/1/ ሪከርዶችን የሚለው መዛግብትን በሚል መስጠት የሚለው መሰጠት በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ሪከርዶች የሚለው የአማርኛ ቃል ስላልሆነ ነው።

5.346. የረቂቁ ሕጉ አንቀፅ 412/1/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 406/1/ መጀመሪያ ላይ ያለው የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ በምትክነት ተፈፃሚ በሚሆንባቸው ወንጀሎች ላይ የሚለው ተዘርዟል።

ምክንያቱም የውጭ ሀገር ዜጋ ኢትዮጵያ ውስጥ ወንጀል ፈጽሞ ወደ ሌላ ሀገር ቢሸሽ እና ተፈላጊው የሚገኝባት ሀገር አሳልፋ በማትሰጥበት ሁኔታ ተፈላጊው ግለሰብ በዚያው ሀገር ተጠያቂ እንዲሆን ጅምር የምርመራ ወይም የክስ ሂደቱ ወደዚያ ሀገር ሊተላለፍ ስለሚችል ነው።

5.347. የረቂቁ ሕጉ አንቀፅ 413/4/ **በተስተካከለው አንቀጽ 407/4/ /በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል።** የተላለፈ ፍርደኛን ቅጣት በማስፈጸም ሂደት ፍርዱ እንዲከለስ ወይም የመጨረሻ ፍርድን እንደገና የማየት ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ፍርዱን የሰጠው ሀገር ይሆናል።

ምክንያቱም ፍርድን የመከለስ ስልጣን ፍርዱን የሰጠው አካል ስለሆነ ነው።

5.348. የረቂቁ ሕጉ አንቀፅ 413/5/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 407/5/ ሆኖ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ተጨምሯል። ንዑስ አንቀፆችም ቁጥራቸው ተሸጋሽጓል። 'በስምምነት በልዩ ሁኔታ ካልተመላከተ በስተቀር አመክሮ፣ ቅጣት መቀነስ ወይም መለወጥ ፣ ይቅርታ እና ምህረት ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን ፍርድ ከሰጠው ሀገር ጋር በመነጋገር ፍርዱን የሚያስፈፅመው ሀገር ይሆናል።'

ምክንያቱም እነዚህ ጉዳዮች በግልጽ መደንገግ አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

5.349. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 414/2/ በተስተካከለው አንቀጽ 408/2/ ንብረቱ የሚለው ንብረት፤ መንግሥት የሚለው ሀገር በሚል ተተክቷል እንዲሁም ንዑስ 3 'በሀገራት ስምምነት' የሚል መጀመሪያው ላይ ተካቷል።

**ምክንያቱም** ጠያቂው መንግስት ይሁን ሌላ አካል ግንኙነት የሚያደርገው በሀገር ደረጃ ስለሆነ በተጨማሪም በተቃራኒው ሊወሰን የሚችለው በሀገራት መካከል በስምምነት ስለሆነ መገለፅ ስላለበት ነው።

5.350. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 414/3/ በተስተካከለው አንቀጽ 408/3/ መጀመሪያ ላይ ያለው ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚለው ካልተወሰነ በስተቀር ከሚለው ሀረግ በኋላ ፍትህ ሚኒስቴር በሚል የተካተተ ሲሆን ማሠሪያ አንቀፁ ይሆናል የሚለው እንዲሆን ይደረጋል በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ንብረት እንዲወረስ ውሳኔ የሚሰጠው ፍርድቤት ስለሆነ እና የፍትህ ሚኒስቴር ሚና ውሳኔውን ማስፈፀም ስለሆነ ድንጋጌው ይህን በሚገልፅ መልኩ ለማስቀመጥ ነው።

5.351. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 415/4/ በተስተካከለው አንቀጽ 409/4/ የሚከተለው ተጨምሯል። **በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት** በኢትዮጵያ ግዛት ክልል እንዲተላለፍ ፈቃድ ያልተሰጠበት ሰው ኢትዮጵያዊ ከሆነ እና ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ እንዲለቀቅ ይደረጋል።

ምክንያቱም ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው ተላልፎ አይሰጥም የሚል ድንጋጌ ስላለ ከሱ ጋር ማጣጣም ስላስፈለገ ነው ።

5.352. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 417/1//ሀ/ እና /2/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 411/1//ሀ/ እና /2/ ሁለት ዓመት የሚለው በአንድ ዓመት ተተክቷል።

**ምክንያቱም** ዓለም አቀፍ ልምድ፣ሀገራችን አባል የሆነችባቸው የሁለትዮሽና ባለብዙ ሀገራት ስምምነቶች የሚጠቀሙበት የቅጣት መጠን በመሆኑ ነው።

5.353. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 419/4/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 413/4/ ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል። **ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈፀመ ወንጀል ወይም በኢትዮጵያ የዳኝነት ስልጣን ስር በሚወድቅ ጉዳይ የሚፈለግ ከሆነ ይህ ሥርዐት**

**አስከሚያልቅ፣ እንዲሁም ንዑስ**/5/ ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል። 'ሀገራችን አባል በሆነችባቸው ስምምነቶች ላይ የተጠቀሱት ሌሎች ምክንያቶች'፤

***ምክንያቱም አንድ ተፈላጊ አሳልፎ ከመሠጠቱ በፊት ቅድሚያ ሀገር ውስጥ ለሚፈለግበት ወንጀል መሰጠት ስላለበት እና*** ዝርዝሩን መጨረስ ስለማይቻል እና ከተዘረዘሩት ውጭ አሳልፎ ለመስጠት የማያስችል ጉዳይ ሲያጋጥም ስራ ላይ ለማዋል እንዲያግዝ ነው።

5.354. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 420 በተስተካከለው አንቀጽ 414 በላይ ያለው የክፍሉ ርዕስ የአሳልፎ መስጠት ሥነሥርዐት በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ክፍሉ የሚደነግገው ስለ ሰነዶቹ ብቻ ሳይሆን በጥቅሉ ስለአሳልፎ መስጠት ሥነ ሥርዐት ነው።

5.356. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 420/2/መ/ በተስተካከለው አንቀጽ 414/2/መ/ ጥፋተኛ ተብሎ የሚለው ቅጣት የተጣለበት በሚል ተስተካክሏል፤ እዚሁ ንዑስ አንቀፅ /ሠ/ ላይ የሚያስችለው 'ን' የሚለው ፊደል ተሰርዟል።

ምክንያቱም ቅጣት ተጥሎበት ቅጣቱን ለማስፈፀም ተላልፎ እንዲሰጥ ጥያቄ ሲቀርብ መያያዝ ያለበት ያልፈፀመው ቅጣት ስለሆነ ነው። የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 421/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 415/1/ የ የሚል ፊደል እና ድርጊት የሚለው ቃል ተሰርዟል፡ ንዑስ ለ እና ሐ ላይ ን የሚል ፊደል ተጨምሯል። ንዑስ ሠ ላይ የተከሳሹን የሚለው የተፈላጊው በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ተላልፎ ይሰጠኝ ጥያቄ የቀረበበት ተፈላጊ ስለሚባል።

5.357. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 422/3/ሀ/ በተስተካከለው አንቀጽ 416/3/ሀ/ ተፈላጊው ከሚለው ቀጥሎ ሰው የሚል እና ንዑስ መ ለማምለጥ የሚለው እንዳያመልጥ በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም የሰዋሰው ችግር ስለሚያመጣ ነው።

5.358. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 428/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 422/1/ በሚከተለው አግባብ ተስተካክሏል። በዚህ ሕግ መሠረት በፍርድ ቤት በተሰጠ የአሳልፎ መስጠት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሊባልበት ወይም እንደገና እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብበት ይችላል። እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዟል። ንዑስ አንቀጽ 3 በሚከተለው አግባብ ተስተካክሏል። በዚህ ሕግ ስለ ይግባኝ እና ፍርድን እንደገና ስለማየት የተደነገገው እንደ አግባብነቱ በዚህ አንቀጽ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ምክንያቱም ንዑስ አንቀጽ 1 የሰዋሰው ችግር ስለነበረበት፣ አንቀጽ ንዑስ 2 እርስ በርሱ የሚጋጭ ጉዳይ ስለያዘ እና በአንቀጹ ለመደንገግ ከታሰበው ዓላማ ውጪ ስለሆነ እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ 3 ፍርድን እንደገና ማየትን ያላካተተ ስለነበር ነው። እንዲሁም ይግባኝ መብት ስለሆነ ሊፈቀድ ስለሚገባ እና ፍርድ እንደገና እንዲታይ በዚህ ሥነሥርዐት አዲስ ስለሆነ እሱንም ተፈፃሚ ለማድረግ ነው።

5.359. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 430/2/ **በተስተካከለው** አንቀፅ 424/2/ ተፈላጊ ከሚለው ቀጥሎ ሰው የሚል እና አንቀፅ 431/1/ሀ/ የጤና መታወክ ከሚለው ቀጥሎ ያጋጥመዋል የሚል ተጨምሯል።

ምክንያቱም ሀሳቡን የተሟላ ለማድረግ ነው።

5.360. የረቂቅሕጉ አንቀፅ 432 **በተስተካከለው** አንቀፅ 426 መዝጊያ ላይ ያለው ዐረፍተ ነገር በሚከተለው ተስተካክሏል። 'በዚህ ሕግ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሠረት ተገቢው እንዲፈፀም ትእዛዝ ይሰጣል።'

**ምክንያቱም** ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀበት ወንጀል በዚህ ሀገር ያልተፈፀመ እንደመሆኑ መጠን እና ቀዳሚ መብት የማይኖረን ስለሆነ ክስ እንዲመሰረትም ሆነ ቅጣት እንዲወሰን ትእዛዝ ለመስጠት ፍርድቤቱ ሕጋዊ መሠረት አይኖረውም።

5.361. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 434 በተስተካከለው አንቀጽ 428 ርዕስ የተፈላጊው ሰው እና ማስረጃ ርክክብ በሚል ተስተካክሏል፤ ንዑስ 2 /ለ/ ሰነድ ወይም ማናቸውም ማስረጃ የሚል ተጨምሯል።

ምክንያቱም ዕቃ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ነገሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ ለማካተት ነው።

5.362. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 434/2/ሀ/ በተስተካከለው አንቀጽ 428/2/ሀ/ ቅጣቱን ሲያጠናቅቅ ከሚለው ቀጥሎ እንደ አግባብነቱ የሚል ተጨምሯል።

ምክንያቱም ከሀገር የመውጣቱ ሁኔታ ሁልጊዜ ተፈፃሚ ላይሆን ስለሚችል ነው።

5.363. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 434/2/ለ/ በተስተካከለው አንቀጽ 428/2/ለ/ እንደሚከተለው ተስተካክሏል። በማስረጃነት የቀረበ ሰነድ፣ ወይም ማናቸውም ማስረጃ በተገቢው መንገድ መያዙን ወይም የቀረበለት ዓላማ ሲጠናቀቅ በሕግ መሠረት መመለሱን፣ ማረጋገጥ ይኖርበታል።

ምክንያቱም ሰነድ፣ ወይም ማናቸውም ማስረጃ ነው መመለሱን ማረጋገጥ የሚያስፈልገው።

5.364. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 435/1/ በተስተካከለው አንቀጽ 429/1/ መጀመሪያ ላይ ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ፣ የአሳልፎ መስጠት የሚለው የትብብር በሚል የተስተካከለ ሲሆን ያቀረበው ሀገር የሚለው ተሰርዟል።

ምክንያቱም አፃፃፉ ስህተት ስለነበረበት ነው።

5.365. **የረቂቁ ሕጉ አንቀጽ** 438 **በተስተካከለው** 432 **ከንዑስ አንቀጽ** /1/ **በኋላ የሚከተለው ተጨምሯል፡፡**

**438/2/** በተፈረደበት ሰው ክርክር ምክንያት ዐቃቤ ሕግ የተለየ ወጪ ያወጣና የተፈረደበት ሰው የመክፈል አቅም ያለው እንደሆነ ከተወሰነበት ቅጣት በተጨማሪ ዐቃቤሕግ የሚያቀርበውን የወጪ ዝርዝር ተመልክቶ የተፈረደበት ሰው በሙሉ ወይም በከፊል ልዩ ወጪውን እንዲከፍል ፍርድቤቱ ትዕዛዝ ይሰጣል።

**438/3/** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **2** ኃላፊ የሆኑ የተፈረደባቸው ሰዎች ከአንድ በላይ የሆኑ እንደሆነ ወጪው በተለየ ኃላፊ የሚሆን ሰው የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር ሁሉም በአንድነት ወይም በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ።

**438/4/** ፍርድቤቱ ወጪው እንዲከፈል ከማዘዙ በፊት የተፈረደበት ሰው በቀረበው የወጪ ዝርዝር ላይ አስተያየቱን እንዲሰጥ ማድረግ አለበት።

ምክንያቱም በነባሩ ሥነሥርዐት ሕግ የነበረ እና ምንም እንኳን በስራ ላይ እየዋለ ባይሆንም ወደፊት አስፈላጊነቱ የጎላ ስለሚሆን መካተት ስላለበት ነው።

5.366. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 442 በተስተካከለው አንቀጽ 436 መግቢያ ላይ ያለው በዚህ ሕግ የተደነገገው ደንብ የማውጣት ስልጣን የሚለው ተሰርዞ በሌላ ሕግ የተደነገገው በሚል ተተክቷል። እንዲሁም 442/1/ ላይ አማራጭ የሚለው ተለዋጭ በሚል ተተክቷል። እንዲሁም አፈጻጸምና የሚለው ቃል ተሰርዟል። እንዲሁም ማሳረጊያ ላይ ያለው የተመለከቱ ደንቦች የሚለው ደንብ በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም በረቂቅ ሕጉ ተለዋጭ በሚል ስለተስተካከለ እና የሰዋሰውንም ችግር ለማስተካከል ነው።

5.367. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 442 መጨረሻ ላይ ሊያወጣ ይችላል የሚለው ያወጣል በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ትክክለኛው አገላለጽ ስለሆነ ነው።

5.368. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 442/4/ በተስተካከለው አንቀጽ 436 /4/ ቀጥሎ አዲስ 2 ንኡስ አንቀጾች እንደሚከተለው ተጨምረዋል።

436/5/ የተለዋጭ ቅጣት አስፈፃሚ ቦርድ ማቋቋሚያ ፣

436/6/ የተከላካይ ጠበቃ ተቋም ማቋቋሚያ

***ምክንያቱም በሥነሥርዐት ሕጉ በደንብ የሚቋቋሙ ስለሆነ የተካተተ ስለሆነ ነው፡፡***

5.369. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 443/1/ሀ/ በተስተካከለው አንቀጽ 437/1/ሀ/ የጉዳዮች የሚለው ተሰርዞ የጉዳይ ፍሰት አስተዳደር የሚል ተጨምሯል፤ ንዑስ ሐ ተሰርዟል፤ ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ፣ሠ፣ረ እና ኘ ተሰርዘዋል፤ እንዲሁም ሰ የአማራጭ መንገዶች አፈፃፀም በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም የአማራጭ መንገዶች አፈፃፀም በሚል የተጠቀሰው መመሪያ የተሰረዙትን ማቀፍ ስለሚችል እና ነው።

5.370. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 443/1/ ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል። የፍትህ ተቋማት በዚህ ሕግ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነትን ለማስፈጸም መመሪያ ማውጣት ይችላሉ። ንዑስ 2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፡- ረቂቁ ላይ የነበሩት ንዑስ ፊደሎቹ ይቀጥላሉ። በተጨማሪም ንዑስ ፊደል መ ከፊት ለፊት የግልጽ እና የሚል ተጨምሯል፣ ንኡስ ፊደል ረ ሆኖ የሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀጽ ተጨምሯል። 'የቅጣት አወሳሰንና ተለዋጭ መፍትሔ አፈጻጸም መመሪያ' ማውጣት ይችላሉ።

ምክንያቱም ንዑስ ፊደል ተራ ረ ሆኖ የተጨመረው መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ስለሆነ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣኑም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለሆነ ነው።

5.371. የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 443 በተስተካከለው አንቀጽ 437 ንዑስ 1 እና 2 ሀ ፣ለ እና ሐ... ቅደም ተከተሉ ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ማስቀመጥ ለአገላለጽ የተሸለ ስለሆነ ነው።

5.372. የረቅቅ ሕጉ አንቀጽ 443/2/ የነበረው 3 ሆኖ የዚህ ንኡስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ የህትህ ሚኒስቴር ፡- በሚል ተስተክክሏል።በተጨማሪም አዲስ ንዑስ ፊደል ቸ ሆኖ የሚከተለው ተጨምሯል በሴቶችና ሕጻናት የሚፈጸሙ ወንጀሎች እና በሌሎች የተለዩ ወንጀሎች ላይ የወንጀል ምርመራና ክስ አመሰራረት

ምክንቱያቱም በተደጋጋሚ ከሴቶችና ሕጻናት መብት አንፃር ሲሰጡ የነበሩ አስተያቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት በአሰራር የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት እንዲቻል ለማድረግ ነው።

5.373. የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 444 በተስተካከለው አንቀጽ 438 ማሠሪያ አንቀፁ መቅረብ ይኖርበታል የሚለው እንዲፀድቅ ይቀርባል በሚል ተስተካክሏል።

ምክንያቱም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለመፅደቅ መላክ ስላለበት እና ትክክለኛው አገላለፅ ስለሆነ ነው።

5.374. በአጠቃለይ በረቂቅ ሕጉ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በሚል የተካተቱት ፍትሕ ሚኒስቴር በሚል ተተክቷል።

ምክንያቱም በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት የተቋሙ ሥያሜ ለውጥ ስለተደረገ ነው።

5.375. _በረቂቅ ህጉ በማጣቀሻነት የተገለጹት አንቀጾች በሙሉ በተሸጋሸገው መሰረት ተስተካክሏል።

ምክንያቱም አንቀጾቹ ስለተሸጋሸጉ በማጣቀሻነት የተገነለጹት አንቀጾች በተሸጋሸገው መሰረት ማስተካከል በማስፈለጉ ነው

5.376. የረቂቅ ህጉ የፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን የሚደለድለው ሠንጠረዥ እንደሚከተለው ተስተካክሎ አባሪ ተደርጓል።

ምክንያቱም የወንጀል ደረጃ የሚያስፈልገው ለዋስትና ፣ ለጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ጉዳዮች ስለሆነ ሠንጠረዡ ላይ የወንጀል ደረጃን ከባድ መካከለኛ ቀላል ብሎ ማስቀመጡ ተገቢ ባለመሆኑ እንዲሁም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በክልሎች እስኪቋቋሙ ድረስ ስልጣኑ በውክልና ለክልል ፍርድ ቤቶች መሰጠቱ ስለሚታወቅ በድጋሚ መግለጹ አስፈላጊ ስላልሆነ ነው እና ሕገ መንግስቱ እና የፍርድቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ውክልና የሚለው ቃል አልተጠቀሙም። በተጨማሪም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ዓ.ም አንቀጽ 4/16/ መሰረት ለከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ወንጀልን የማየት ስልጣን ስለተሰጠ በዚያው መሰረት ለማስተካከል ነው።

## ሠንጠረዥ ሀ

## የፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን

| የአንቀጽ ቁጥር | የወንጀሉ ርዕስ | ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድቤት | |
|---|---|---|---|
| | | የፌዴራል ፍርድቤት | የክልል ፍርድቤት |
| 238 | በሕግ መንግሥትና በሕገመንግሥት ሥርዓት ላይ | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የሚደረግ ወንጀል | | |
| 239 | የሕገ መንግሥታዊ ሥልጣንን ተግባራዊነት ማሰናከል | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 240 | የጦር መሳሪያ ይዞ በማመጽ ወይም የእርስ በርስ ጦርነት በማስነሳት በመንግስት ላይ የሚደረግ ወንጀል | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 241 | የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት የሚደረግ ወንጀል | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 242 | የአገሪቱን የግዛት ወይም የፖለቲካ ሉዓላዊነት በመጣስ የሚደረግ ወንጀል | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 243 | በሕገ ወጥ መንገድ ከአገር መውጣት፣ ወደ አገር መግባት ወይም በአገሪቱ ውስጥ መኖር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 244 | የአገሪቱን መንግስት እንዲሁም የአገሪቱን ምልክቶችና በመንግሥት የታወቁ ሌሎች ምልክቶችን መድፈር፣ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 245 | በታወቁ ምልክቶች ያለአግባብ መገልገል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 246 | በአገር ነፃነት ላይ የሚደረግ ወንጀል | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 247 | የአገር መከላከያ ኃይልን መጉዳት | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 248 | ከፍ ያለ ክዳት | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 249 | ክዳት | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 250 | የኢኮኖሚ ክዳት | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 251 | ከጠላት ጋር መተባበር | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 252 | ስለላ | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 254 | በተዘዋዋሪ መንገድ መርዳትና ማበረታታት | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 255 | ለወንጀል ሥራ ማነሳሳትና አባሪነት፣ የማነሳሳትና የአባሪነት ሙከራ | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 256 | የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ ዓይነት ማሰናዳት | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 257/258 | መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር እና ከባድ ሁኔታ | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 261 | በውጪ አገር መንግስት ላይ የሚደረግ የተቃዋሚነት ድርጊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 262 | በውጭ አገር መንግስታት መሪዎች፣ መልዕክተኞች እና ሌሎች በዓለም አቀፍ ሕግ ጥበቃ ባገኙ ሰዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 263 | የውጪ አገር መንግስትን ግዛት መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 264 | የውጭ አገር መንግስታትን ማዋረድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 265 | የታወቁ የውጭ አገር ምልክቶችን ማዋረድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 266 | በመንግስታት መካከል የተቋቋሙ ድርጅቶችን ማዋረድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 269 | ዘርን ማጥፋት | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 270 | በሠላማዊ ሕዝብ ላይ የሚፈፀም የጦርነት ወንጀል | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 271 | በቁስለኞች፣ በበሽተኞች፣ በባሕር ወይም በአየር አደጋ ላይ ባሉ ሰዎች ወይም በጤና አገልግሎት ላይ የሚፈፀም የጦርነት ወንጀል | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 272 | በታሰሩ የጦር ምርከኞች እና በተጋዙ ሰዎች ላይ የሚፈፀሙ የጦርነት ወንጀሎች | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 273 | በጦርነት ጊዜ የሚደረግ ገፈፋ፣ ዘረፋና የባህር ውንብድና | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 274 | መገፋፋትና ማሰናዳት | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 275 | ለጠላት ሊደረግ የሚገባውን ተግባር መጣስ | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 276 | ሕገ-ወጥ በሆኑ የጦር መሳሪያዎች መገልገል | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 277 | የጦርነት ማቆም ውልን ወይም የሰላም ስምምነትን ማፍረስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 279 | በቁስለኞች፣ በበሽተኞችና በእስረኞች ላይ መጨከን ወይም የሚገባቸውን ማጓደል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 280 | ፍትሕን መከልከል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 281 | በዓለም ዓቀፍ ሰብዓዊ ድርጅቶች ላይ የሚፈፀም የጠላትነት ድርጊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 282 | በዓለም ዓቀፍ ሰብዓዊ ድርጅቶች አርማዎችና መለያ ምልክቶች ያለአግባብ መገልገል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 283 | በእርቅ መልዕክተኛ ላይ የጠላትነት ድርጊት መፈፀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 284 | ወታደራዊ አገልግሎትን እምቢ ማለት | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | - |
| 285 | የጥሪ ትዕዛዝን አለማክበር | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 286 | ከአገልግሎት ግዴታ ለማምለጥ ታስቦ የሚደረግ የችሎታ ማጣት | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 287 | ከወታደራዊ አገልግሎት ለማምለጥ የሚፈፀም ማጭበርበር | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 288 | ኩብለላ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 289 | ያለአግባብ መቅረት | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 290 | አስቦ ወደ ጦር ክፍሉ ተመልሶ አለመምጣት | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 291 | ከአገልግሎት ግዴታ ያለአግባብ ነፃ ማድረግ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 292 | በበታች ላይ የሚፈፀም ዛቻና የኃይል ድርጊት | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 293 | ጠቅላላ የአገልግሎት ደንቦችን መጣስ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 294 | ያልተሟላ ወይም ትክክል ያልሆነ መረጃ መስጠት | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 295 | ሰክሮ መገኘት | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 296 | ከሥነሥርዓት ወይም ዲሲፕሊን ውጪ መሆን | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 297 | በበላይ አለቃ ወይም በማዕረግ እኩያ በሆነ አባል ላይ የሚፈፀም ስድብ፣ ዛቻ እና የእጅ እልፊት | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 298 | ለበላይ አለመታዘዝ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 299 | ወታደራዊ አመፅ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 300 | ወታደራዊ አመፅ ለማስነሳት የሚደረግ አድማ ወይም መተባበር | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 301 | ወታደራዊ አመፅ እንዲደረግ ማነሳሳትና የማነሳሳት ሙከራ፣አባሪነት፣የአባሪነት ሙከራ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 302 | በዘብ፣በዘብ ጠባቂ እና በቃኚ ዘብ ላይ የሚፈፀም ወንጀል | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 303 | የጥበቃ ግዴታን መጣስ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 304 | ወታደራዊ ትዕዛዝን መጣስ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 305 | ትዕዛዝን ያለአግባብ መግለፅ ወይም መለዋወጥ ወይም በአግባቡ አለማስተላለፍ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 306 | በዕቃዎች ያለአግባብ መገልገል ወይም ማባከን | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 307 | የማይገባ ጥቅምን ማግኘት ወይም ያለአግባብ ማጥፋት | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 308 | አደጋን አለማስታወቅ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 309 | አስፈላጊ የሆነውን የደህንነት ጥንቃቄ አለማድረግ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 310 | ሐሰተኛ የአደጋ ምልክት መስጠት | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 311 | የመከላከያ ሠራዊቱን ተስፋ ማስቆረጥ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 312 | ፈሪነት | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 313 | ለጠላት እጅን መስጠት | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 314 | የጦር መሣሪያዎችን እንደተሟሉ መተው | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 315 | በጠላት የደንብ ልብስ ወይም የጦር መሣሪያ ያለአግባብ መገልገል | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 316 | የቆሰለ ወይም የተሰዋ አባልን ትቶ መሄድ | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 317 | የቆሰለ ወይም የተሰዋ አባል በያዘው ንብረት ላይ የሚፈፀም ወንጀል | ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድቤት | |
| 323 | የስራ ግዴታ በማይገባ ሁኔታ እንዲፈፀም ወይም እንዲጣስ ማስገደድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 324 | ስራውን በማከናወን ላይ ያለ የመከላከያ ሰራዊት አባል ላይ የሚፈፀም ጥቃት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 325 | ከባድ ሁኔታዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 326 | የሕግ ወይም የውል ግዴታዎችን መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 327 | የተንኮል ሥራ /አሻጥር/ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 328 | በወታደራዊ ዕቃዎች መነገድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 329 | የመከላከያ ሰራዊት የደንብ ልብስን ፣ ምልክትና ሽልማትን ያለአግባብ ማምረትና ለንግድ ማዘዋወር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 330 | የመከላከያ ሰራዊት የደንብ ልብስን ፣ ምልክትና ሽልማትን በማይገባ መልበስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 331 | ወታደራዊ የጥንቃቄ ዕርምጃዎችን መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 332 | ወታደራዊ ትዕዛዞች እንዲጣሱ ለማድረግ ሌላውን ሰው ማነሳሳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 333 | የተወሰኑ ወታደራዊ ስፍራዎችንና እቃዎችን ለመጠበቅ የወጡ ክልከላዎችን መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 334 | ጠቅላላ ትዕዛዞችን ወይም መመሪያዎችን ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም ማጥፋት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 335 | በመከላከያ ሰራዊት እና በወታደራዊ ግዴታዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን አለማስታወቅ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 336 | ወታደራዊ ሚስጥርን መግለጽ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 337 | የሐሰት ወይም የሚያደናግር መረጃ | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 346 | በወርቅ ፣ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ አገር ገንዘብ በሕገ-ወጥ መንገድ መነገድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 347 | በከበሩ ማዕድናት ሕገወጥ በሆነ መንገድ መነገድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 348 | በመንግሥት ገንዘብ አስተማማኝነት ላይ የሚደረግ | ከፍተኛ ፍርድቤት | ጠቅላይ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የተንኮል ድርጊት | | |
| 349 | ሕገወጥ በሆነ መንገድ የመንግሥትን ቀረጥ ወይም ግብር የመክፈል እምቢተኝነት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 350 | ግብር እንዳይከፈል ማነሳሳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 351 | በመንግሥት የገቢ ምንጮች ላይ ጉዳት ማድረስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 252 | ኬላ መስበር /ኮንትሮባንድ/ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 353 | በአገር ኢኮኖሚና በመንግስት ሞኖፖል ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 354 | ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 356 | መስራት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 357 | ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 358 | ዋጋውን ዝቅ ማድረግ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 359 | ወደ አገር ማስገባት፣ ከአገር ማስወጣት፣መያዝ፣ ማስቀመጥ እና ማቅረብ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 361 | ማዘዋወር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 362 | ቀላል ሁኔታ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 363 | የመንግሥት ማሕተሞችን ወደ ሐሰተኛ መለወጥ ወይም በማሕተሞች ያለአግባብ መገልገል | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ጠቅላይ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑት ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ፍርድቤት) |
| 364 | የሌሎች የሕዝብ አገልግሎት ወይም የግል ድርጅቶችን ማሕተም ወደ ሐሰት መለወጥና በማሕተሞቹ ያለአግባብ መሥራት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 365 | የታወቁ ምልክቶችን ወደ ሐሰት መለወጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 366 | ዋጋ ያላቸውን የታወቁ ቴምብሮች ወደ ሐሰተኛ መለወጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 367 | የመመዘኛ ክብደቶችንና መለኪያዎችን ወደ ሐሰት መለወጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 368 | ከአገር ማስወጣት፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ መግዛት፣ በአደራ ማስቀመጥና ማቅረብ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 369 | የማታለል ሃሳብ ሳይኖረው አስመስሎ መስራት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | የከፍተኛ ፍርድቤት ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 370 | በገንዘብ፣ በግዴታ ወይም በዋስትና ሰነዶች ወይም በታወቁ ምልክቶች፣ ቴምብሮች ወይም ማሕተሞች አደጋ ማድረስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት(የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 371 | ሐሰተኛ ነገሮችን ለመስራት የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና መሥሪያዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 375 | በግዙፍ የሚፈጸም ሐሰት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 376 | ረቂቅ በሆነ መንገድ የሚፈጸም ሐሰት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 377 | ልዩ ሁኔታዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 378 | በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 380 | ሰነዶችን ማጥፋት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 380 (2) | ሰነዶችን ማጥፋት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 382 | የንግድ ወይም ተላላፊ የዋስትና ሰነዶችን ወደ ሐሰት መለወጥና ማጥፋት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 384 | የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ወረቀቶችን ወደ ሐሰት መለወጥና በነዚሁ መገልገል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች ላይ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 385 | ሐሰተኛ ምስክር ወረቀቶች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስቱ ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)። | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 386 | ሐሰተኛ የሆነ ኦፊሴላዊ ምስክርነት በማጭበርበር ማግኘት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስቱ ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)። | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 387 | ሐሰተኛ የሕክምና ምስክር ወረቀት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስቱ ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)። | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 389 | ሐሰተኛ የቃል አሰጣጥና ምዝገባ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስቱ ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)። | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 390 | የሐሰት ሥራ ለመፈጸም የሚያገለግሉ መሳሪያዎችና መስሪያዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስቱ ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)። | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 391 | እቃዎችን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥና ጥራታቸውን ማርከስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስቱ ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)። | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 392 | ማዘዋወር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስቱ ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)። | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 393 | እቃዎችን ወደ አገር ማስገባት፣ ወደ ውጪ መላክ፣ በእጅ ማድረግና ማከማቸት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 396 | ወታደራዊ ሚስጥርን መግለጽ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 397 | የሥራ ምስጢርን መግለጽ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 399 | በሞያ ወይም በሥራ ምክንያት የታወቀ ምስጢርን መግለጽ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 401 | የሳይንስ የኢንዱስትሪ ወይም የንግድ ምስጢርን መግለጽ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 420 | የሥራ ኃላፊነትን ባለመወጣት የሚፈጸም ወንጀል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 421 | ሕገወጥ የሥራ ማቆም አድማ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑት ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 422 | የሰውን ንብረት የመበርበር ወይም የመያዝ ስልጣንን ያለአግባብ መገልገል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 423 | ሕገወጥ በሆነ መንገድ ሰውን መያዝ ወይም ማሰር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 424 | በማይገባ የአሰራር ዘዴ መጠቀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 425 | እሥረኛን ሕገወጥ በሆነ መንገድ መፍታትና እንዲያመልጥ መርዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 426 | የጦር ምርኮኞችንና የወታደር ግዞተኞችን መፍታትና እንዲያመልጡ መርዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 432 | መንግሥታዊ የሆኑ ማስታወቂያዎችንና ሕጎችን መድፈር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 433 | ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ውጭ መስራት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 434 | የማስመዝገብ ግዴታን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 435 | እንዳይገለፁ የተከለከሉ መንግሥታዊ ውይይቶችን ወይም ሰነዶችን መግለጽ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 436 | ሕገወጥ በሆነ መንገድ መብትን ማስከበር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 437 | ሥልጣንን በማይገባ መያዝ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 438 | የመንግሥት ሥራን ማሰናከልና የመተባበር ግዴታን መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 439 | እሽጎችን መቅደድ መሰበርና ዕቃዎችን መውሰድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 440 | መቃወምና አለመታዘዝ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 441 | የኃይልና የማስገደድ ተግባር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 443 | ወንጀልን አለማስታወቅ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 444 | በጠቋሚዎች እና በምስክሮች ላይ የሚፈጸም ወንጀል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 445 | መሸሸግና መርዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 446 | የፍትሕን ሥራ ማሳሳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 447 | በሐሰት መወንጀል ወይም መክሰስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 448 | ለፍትሕ እርዳታ መስጠትን እንቢ ማለት | ጉዳዩን እየተመለከተ ያለው ፍርድቤት ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች) | ጉዳዩን እየተመለከተ ያለው ፍርድቤት ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት |
| 449 | ፍርድቤትን መድፈር | ጉዳዩን እየተመለከተ ያለው ፍርድቤት | ጉዳዩን እየተመለከተ ያለው ፍርድቤት |
| 450 | የፍርድ ሒደትን ምስጢር መግለጽ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 451 | የፍርድ ሒደትን በተመለከተ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተከለከለ ዘገባን መግለጽ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት |
| 452 | አንድ ተከራካሪ ወገን የሚሰጠው ሐሰተኛ ቃል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት |
| 453 | ሐሰተኛ ምስክርነት፣ አስተያየት ወይም ትርጉም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 455 | መገፋፋትና ማግባባት | የመጀመሪያ ደረጃፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 456 | በሙግት ጊዜ ማጭበርበር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 457 | የፍትሕን ሒደት ለማዛባት በተንኮል የሚፈጸም የወሬ መግለጽ ድርጊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 458 | በአንድ ወገን ተከራካሪ ጥቅም ላይ የክህደት ተግባር መፈፀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 459 | ተጨማሪ ቅጣቶችን የመከላከልና የመጠበቅ የጥንቃቄ እርምጃዎችን አለማክበር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳፍርድቤት |
| 460 | የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ማሰናከል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 461 | የእሥረኛ ማምለጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች፣ በፌዴራል መንግስቱ ጉዳይ ላይ ሲሆን)፣ | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 462 | እሥረኛ እንዲያመልጥ ማመቻቸትና መርዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች፣ በፌዴራል መንግስቱ ጉዳይ ላይ ሲሆን)፣ | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 464 | የእስረኞች አመጽ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች፣ በፌዴራል መንግስቱ ጉዳይ ላይ ሲሆን)፣ | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 465 | አካባቢያዊ ክልከላን መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ | የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | |
| 466 | ለምርጫ የሚደረግ ስብሰባንና የምርጫ ሒደትን ማወክና ማሰናከል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 467 | የምርጫ ድምጽ የመስጠትን ወይም የመመረጥን መብት መንካት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 469 | የማይገባ አሰራር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 470 | በአመዘጋገብ ላይ የሚፈጸም ማጭበርበር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 471 | በድምጽ አሰጣጥ ጊዜ የሚፈጸም ማጭበርበር ድርጊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 473 | የድምጽ አሰጣጥ ምስጢር አጠባበቅን መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 474 | የድምጽ መስጫ ወረቀቶችንና የምርጫ ሳጥኖችን መውሰድና ማጥፋት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 477 | አደገኛ የሆነ ስራ ፈትነት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 478 | የከፋ አድራጊዎች ማሕበርተኛነት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 479 | የከፋ አድራጊዎች መጠጊያና ረዳት መሆን | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት) |
| 480 | ወንጀል እንዲፈፀም በአደባባይ መገፋፋት ወይም ወንጀልን በጅቷል ማለት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | |
| 481 | በጦር መሣሪያ መነገድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 482 | የተከለከሉ ማህበሮችና ስብሰባዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 483 | ሕቡዕ የሆኑ ማሕበሮች ወይም መሣሪያ የታጠቁ ቡድኖች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 484 | የተከለከሉ ስብሰባዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 485 | በወሬ ሕዝብን ማሸበር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራልመንግስትተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 487 | የማነሳሳት ጠባይ ያላቸው የሐሳብ መግለጫዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 488 | ረብሻ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 490 | ስብሰባን ወይም ጉባኤን ማወክ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት(የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት) |
| 491 | በራስ ጥፋት ከኃላፊነት ውጭ በመሆን የሚፈፀም የሁከት ተግባር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 492 | የሃይማኖትን ሰላምና ስሜት መንካት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 493 | የሙታንን ሰላምና ክብርመንካት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | |
| 494 | የእሳት ቃጠሎ ማድረስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 495 | የተፈጥሮ አደጋዎችን ማድረስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 496 | ግዙፍ ስራዎችን ወይም የመጠበቂያ ስራዎችን መጉዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 497 | ማፈንዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 498 | በቸልተኝነት የሚፈፀሙ ወንጀሎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 499 | በሚፈነዱ፣ በሚቀጣጠሉ ወይም በሚመርዙ ነገሮች አደጋ ማድረስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 500 | ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ የሚፈነዱ፣ የሚቀጣጠሉ የሚመርዙ ነገሮችን መሥራት፣ መያዝ፣ መደበቅ፣ ወይም ማጓጓዝ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 501 | የሕንጻ ሥራ ደንቦችን መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 502 | የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችን ወይም ዕቃዎችን ማንሳት ወይም አለማደራጀት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 503 | በሕዝብ ላይ የሚደርስ ከባድ አደጋን አለማስታወቅ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 505 | ለሕዝብ ጥቅም በተቋቋሙ ግዙፍ ሥራዎችና አገልግሎቶች ላይ ጉዳት ማድረስ | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 506 | መገናኛዎችንና ማጓጓዦዎችን በከባድ አደጋ ላይ መጣልና ማበላሸት | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 507 | በኮንቲኔንት ሸልፍ የሚገኝን ቋሚና የተተከለ ስፍራን፣አይሮፕላን ወይም መርከብን ያለአግባብ መያዝ | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 508 | በኮንቲኔንት ሸልፍ የሚገኝን ቋሚና የተተከለ ስፍራን፣አይሮፕላን ወይም መርከብን አስጊ ሁኔታ ላይ መጣል | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 509 | በኮንቲኔንት ሸልፍ የሚገኝን ቋሚና የተተከለ ስፍራን፣አይሮፕላን ወይም መርከብ ላይ አደጋ ማድረስ | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 510 | ምልክቶችንና የእርዳታ ጥሪዎችን ያለአግባብ ማድረግ | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 511 | አደገኛ የሆኑ ነገሮችን ወይም መሳሪያዎችን በሕገወጥ መንገድ ማስቀመጥ ወይም መጫን | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 512 | ከባድ ሁኔታ | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት |
| 514 | የሰውን በሽታ ማሰራጨት | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት፤ ከፌዴራል ጉዳይ ውጪ የሆኑት በከፍተኛ ፍርድቤት |
| 515 | የእንስሳት በሽታን ማሰራጨት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 516 | የሰብልን ወይም የደንን ተባይ ማራባት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 517 | ውሃን መበከል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 518 | ግጦሽን መበከል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ፍርድቤት |
| 519 | አካባቢን መበከል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 520 | አደገኛ የሆነ ቆሻሻንና ሌላ ቁስን በአግባቡ አለመያዝ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 521 | የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማን የሚፃረሩ ድርጊቶችን መፈፀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 522 | ጤናን ለመጠበቅና ለመንከባከብ በሕግ የተደነገጉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 523 | ችግር ወይም ረሐብ እንዲደርስ ማድረግ | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 525 | መርዛማ ወይም የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ወይም ዕፆችን ማምረት፣ መሥራት፣ ማዘዋወር ወይም መጠቀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 526 | ዶፒንግ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 527 | የሚጎዱ ወይም የተበላሹ እቃዎችንና ምግቦችን መሥራትና መሸጥ እንዲሁም ጥራታቸውን ማርከስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 528 | የከብት ድርቆሽና ሌላም መኖ ጉዳት እንዲያደርስ አድርጎ መሥራት ጥራትን ማርከስና መሸጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 531 | በአልኮል ወይም በአስፒርቶ መጠጦች የሌላውን ሰው ጤንነት ለአደጋ ማጋለጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 532 | አእምሮን በሚነኩ ድርጊቶች ሰውን ለአደጋ ማጋለጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | |
| 533 | በድግምት በጥንቆላ ወይም ይህን በመሳሰሉ ነገሮች በሰው ላይ አደጋ ማድረስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 534 | ከባድ ሁኔታዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 535 | በሕክምናና በጤና አጠባበቅ ሙያ ሕገወጥ በሆነ መንገድ መሥራት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 536 | መርዛማና አደገኛ የሆኑ ነገሮችን ያለአግባብ ማቅረብ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ (የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት) |
| 537 | የሕክምና እርዳታን ያለምክንያት መከልከል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 539 | ከባድ የሰው ግድያ | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 540 | ተራ የሆነ የሰው ግድያ | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 541 | ቀላል የሆነ የሰው ግድያ | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 542 | ሌላ ሰው እራሱን እንዲገድል ማነሳሳትና መርዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 543 | በቸልተኝነት ሰውን መግደል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 544 | ሕፃንን መግደል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 546 | አንድት ሴት በራስዋ ላይ የምትፈፅመው የማስወረድ ድርጊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | |
| 547 | በሌላ ሰው የሚፈፀም የማስወረድ ድርጊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 552 | ጽንስ የሚቋረጥበትሥነ-ሥርዓትናሥነ-ሥርዓቱን መጣስ የሚያስከትለው ቅጣት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 555 | ታስቦ የሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 556 | ታስቦ የሚፈፀም ቀላል የአካል ጉዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 559 | ቸልተኝነት የሚፈፀሙ የአካል ጉዳቶች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 560 | የእጅ እልፊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 561 | በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በእርጉዝ ሴቶችና ሕፃናት ህይወት ላይ ጉዳት ማድረስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 562 | በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በእርጉዝ ሴቶች ወይም በሕፃን አካል ላይ ጉዳት ማድረስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ |
| 565 | ሴትን መግረዝ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች /ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት |
| 566 | የሴትን ብልት መስፋት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 569 | በጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ተካፋይ መሆነ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 570 | ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች እንዳይፈፀሙ ማነሳሳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 571 | የሰውን ሕይወት ለአደጋ ማጋለጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 572 | የትራፊክ ደንብን በመጣስ ለአደጋ ማጋለጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 573 | የሰውን አካል ለአደጋ ማጋለጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 574 | ሰውን ለአደጋ ማጋለጥ ወይም መተው | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 575 | በአደጋ ላይ የሚገኝ ሰውን አለመርዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 576 | ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን መጉዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 577 | አምባጓሮ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 578 | የፀዋጣልን ፍልሚያ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 579 | የፀዋጣልን ፍልሚያ እንዲደረግ መጠየቅ፣ ማነሳሳትና መርዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 580 | ዛቻ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 581 | የመክሰስ ወይም የማዋረድ ዛቻ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 582 | ማስገደድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 583 | የመወሰን ችሎታን ማሳጣት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 585 | ከሕግ ውጪ ይዞ ማስቀመጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 586 | ሰውን መጥለፍ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 587 | ሴትን መጥለፍ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 588 | የአይምሮ ሕመምተኛ የሆነችን ወይም የመከላከል አቅም የሌላትን ሴት መጥለፍ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 589 | ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን መጥለፍ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 590 | ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 591 | ሕፃንን ማለዋወጥ እና የራስ ያልሆነን ህፃን መውሰድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 592 | ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን አለማቅረብ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 593 | ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆችን በሚመለከት ልዩ ሁኔታ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 594 | ከባድ ሁኔታዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 595 | በፖለቲካ ምክንያት ሰውን መጥለፍ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 596 | ሰውን አገልጋይ ማድረግ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 597 | በሴቶችና በልጆች መነገድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 598 | በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጪ አገር መላክ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 599 | በሰው ነጻነት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች የሕገ ወጥ ማህበርና የሕግ ሰውት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 601 | በሲቪል መብቶች በነፃ መጠቀምን መከልከል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 602 | የመዘዋወር ነፃነት መብትን መድፈር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 603 | የስራ ነፃነት መብትን መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 604 | የግል ቤቶችን ወይም የተከለከሉ ቦታዎችን መድፈር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 605 | ወንጀሉን የሚያብዱ ሁኔታዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 606 | የመፃፃፍ ወይም የግንኙነት ግላዊነት መብትን መድፈር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 613 | ስም ማጥፋትና የሐሰት ሀሜት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 615 | ስድብና ማዋረድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 618 | ወንጀሉን የሚያከብዱ ልዩ ሁኔታዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 619 | የጠፉ ወይም የሞቱ ሰዎችን ክብር የመንካት ወንጀል ሲፈፀም ክስ የሚቀርብበት ሁኔታ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 620 | አስገድዶ መድፈር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 621 | አንድን ወንድ አስገድዶ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈፅም ማድረግ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 622 | በንጽሕና ክብር ላይ የሚፈፀም የኃይል ድርጊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 623 | አእምሮአቸውን በሳቱ ወይም የአእምሮ ደካማ በሆኑ ወይም ለመቃወም በማይችሉ ሰዎች ላይ የሚፈፀም የክብረ ንፅህና ድፍረት በደል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 624 | ሆስፒታል ውስጥ በተኙ፣ በተጋዙ ወይም በታሰሩ ሰዎች ላይ የሚፈጸም የክብረ ንጽሕና ድፍረት በደል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 625 | አንዲት ሴት ያለባትን ከፍያ ለችግር ወይም ጥገኝነቷን ምክንያት በማድረግ የሚፈፀም ድርጊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 626 | እድሜአቸው 13 ዓመት በሆነና 18 ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረሥጋ ድፍረት በደል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 627 | በሕፃናት ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረሥጋ ድፍረት በደል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 628 | ወንጀሉን የሚያከብዱ ሌሎች ምክንያቶች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 629 | ግብረ-ሰዶም እና ለንፅሕና ክብር ተቃራኒ የሆኑ ሌሎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ድርጊቶች | (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | |
| 630 | ወንጀሉን የሚያከብዱ ጠቅላላ ሁኔታዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 631 | ለአካለመጠን ባልደረሱ ልጆች ላይ የሚፈፀሙ የግብረ-ሰዶም ጥቃትና ለክብረ ንፅህና ተቃራኒ የሆነ ሌላ ድርጊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 633 | በእንስሳት ላይ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መፈፀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 634 | የሌላውን ሰው የዝሙት ድርጊት የዘወትር መጠቀሚያ ማድረግ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 635 | ሴቶችንና ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን ለዝሙት አዳሪነት በማቃጠር መነገድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 636 | ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 637 | ሴቶችንና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ለዝሙት ለማቅረብ የሚደረጉ ዝግጅቶች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 639 | ለመልካምሥነ-ምግባርና ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ ብልግናና አሳፋሪ ስራን በአደባባይ መፈፀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 640 | ፀያፍ ወይም የብልግና ወይም ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ለሕዝብ መግለጽ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 641 | ፀያፍ ወይም ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ለሕዝብ ማሳየት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 643 | ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆኑ መግለጫዎችና ማስታወቂያዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | |
| 644 | ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን አደጋ ላይ ከሚጥሉ ስራዎች መጠበቅ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 646 | ጋብቻን በተንኮል ወይም በማታለል መፈፀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 647 | በሕግ የተከለከለ ጋብቻን ማስፈፀም ወይም መፈፀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 648 | ያለእድሜ ጋብቻ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 650 | በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈፀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 652 | አመንዝራነት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 653 | የአቤት ባዩ መሞት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 654 | በዘመዳሞች መካከል የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ግንኙነት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 655 | በዘመዳሞች መካከል የሚፈፀም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ የብልግና ድርጊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | |
| 656 | የሕፃን መወለድን ወይም ተጥሎ መገኘትን አለማስታወቅ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 657 | የክብር መዝገብን በሐሰት መለወጥ፣ አስመስሎ ሕፃንን ማቅረብ ወይም መለወጥ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 658 | የቀለብ መስጠት ግዴታን አለመፈፀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 659 | የልጅ ማሳደግ ግዴታን አለመፈፀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 665 | ስርቆት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 666 | ኃይልን መስረቅ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 667 | የጋራ ንብረት የሆኑትን እቃዎች መስረቅ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 668 | በሙታን ላይ የሚፈፀም ስርቆት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 669 | ከባድ ስርቆት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 670 | ውንብድና | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 671 | ከባድ ውንብድና | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል | ጠቅላይ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በሆኑ ጉዳዮች) | ጉዳዮች ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 672 | ዘረፋ | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 673 | የባህር ውንብድና | ከፍተኛ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ጠቅላይ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች ከፍተኛ ፍርድቤት |
| 675 | እምነት ማጉደል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 677 | በመንግሥት ወይም በሕዝብ ንብረት ያለአግባብ መገልገል ወይም ማባከን | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 678 | በሌላ ሰው ሃብት ያላአግባብ መገልገል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 679 | አግኝቶ መደበቅ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 680 | ወድቆ የተገኘውን ንብረት ለራስ ማድረግ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 682 | መሸሸግ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 683 | ከባድ የመሸሸግ ወንጀል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮችየመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 685 | በከብት መንጋ አማካኝነት በሌላሰው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 686 | በሰው ንብረት ላይ ሁከት ማድረግ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 687 | በሰው ይዞታ ላይ ጉዳት ማድረስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | |
| 688 | የወሰን ምልክቶችን ከስፍራቸው ማዛወርና ማጥፋት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 689 | ጠቅላላ ድንጋጌዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 690 | ከባድ ሁኔታዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 691 | ከባድ ዘዴዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 692 | አታላይነት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 693 | የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 694 | በተጭበረበረ ሁኔታ የአክስዮን ገበያ ንግድ ማካሄድ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 695 | በአክስዮኖች ወይም በሸቀጦች መቆመር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 696 | ከባድ አታላይነት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 697 | ሌሎች ወንጀሎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | |
| 698 | ኢንሹራንስ በሚመለከት የሚፈፀም የአታላይነት ድርጊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 700 | በሕዝብ እምነት በመጠቀም ማታለል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 701 | ሌሎች የማታለል ድርጊቶች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 702 | በሌላ ሰው ጥቅም የስራ አመራር ላይ የተፈፀመ ጉዳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 703 | ከባድሁኔታ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 704 | ጥቅም ታገኛለህ በማለት ሌላውን ሰው በመደለል ማነሳሳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 705 | ችሎታ የሌላቸውን ሰዎች ንብረታቸውን የሚጎዳ ስራ እንዲፈፅሙ ማነሳሳት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 712 | አራጣ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 713 | በማስገደድ መጠቀም | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 714 | ጥቅም ለማግኘት ማስፈራራት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | |
| 715 | ከባድ ሁኔታ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 717 | በሌላሰው መልካም ስም ላይ ጉዳት ማድረስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 718 | ጉዳትን የሚያደርሱ ሐሰተኛ መግለጫዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 719 | ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 720 | ምልክቶችን፣የመገኛ ምንጭ ማስታወቅን፣ዲዛይኖችን ወይም ሞዴሎችን መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 721 | የድርሰት፣የኪነ-ጥበብ ወይም የአዕምሮ ሥራ ፈጠራ መብቶችን መጣስ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራልባልሆኑጉዳዮችየመጀመሪያደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 725 | በማጭበርበር እዳ ለመክፈል አለመቻል | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 726 | አላግባብ መክሰር | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች ) | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 727 | በማጭበርበር ኪሳራ እንዲደርስ ማድረግ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (የፌዴራል በሆኑ ጉዳዮች) | ከፍተኛ ፍርድቤት፤ የፌዴራል ባልሆኑ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |
| 728 | በፍርድ አፈፃፀም ላይ የሚፈፀም የማጭበርበር ድርጊት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 729 | በመያዣነት ወይም በሕግ አግባብ የተያዘ ንብረት ያለአግባብ መውሰድ ወይም ማጥፋት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 730 | በፍርድቤት ትዕዛዝ የተያዘን ንብረት ያለአግባብ መውሰድ ወይም ማጥፋት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 731 | በገንዘብ ጠያቂዎች መካከል ተገቢ ያልሆነ አድልዎ ማድረግ | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 732 | የድምጽ ብልጫን ለማግኘት መደለያ መስጠት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 733 | ስምምነትን በማጭበርበር ማግኘት | የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ቦታዎች)፣ | የመጀመሪያ ደረጃ /ወረዳ ፍርድቤት |
| 776 እና ተከታዮች | የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች | በሌሎች ሕጎች ወይንም ደንብ የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት (ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች/ የከተማ አስተዳደር ፍርድቤቶች )፣ | በሌሎች ሕጎች ወይንም ደንብ የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ የመጀመሪያ ደረጃ/ወረዳ ፍርድቤት |

II. <u>የውሳኔሃሳብ</u>

ረቂቅ አዋጁ የህገ መንግስቱ ግቦች የሆኑት የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ እና ዘላቂ ሰላምና ልማትን ማምጣት ሊሳኩ የሚችሉት የሃገር፣ የሕዝብና የግለሰቦች ሰላምና ደህንነት ሲጠበቅ በመሆኑ መንግስት በዚህ መልኩ የሚገለፁትንና መሠረታዊ የሆኑትን የግለሰብና የቡድን መብት እና ጥቅም የማሟላት፣ የማክበርና የማስከበር ግንባር ቀደም ኃላፊነት ተጥሎበታል።

ረቂቅ አዋጁ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስትን እና ኢትዮጱያ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች፣ መርሆዎችን እና እሴቶችን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ ለሀገሪቱ የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ አወንታዊ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችልና የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስርአትን ለማዘመን የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ እንዲሁም በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስርአቱ በተጠርጣሪ፣በተከሳሽና በተጐጂዎች ላይ የሚደርሰውን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በማስቀረት እና የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን በማድረግ አወንታዊ ሚና የሚጫወት፤ ሁሉንም ዜጐች በእኩልነት የሚዳኝ ሲሆን አገሪቱን የጠንካራ ፍትህ ተቋም ባለቤት በማድረግ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ አበርክቶት ያለው፤ አሁን ስራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአትና ላይ የሚታዩ በርካታ ጉድለቶችን የሚቀርፍ፤ በዘመኑ ከሚፈጸሙት ውስብስብና የረቂቁ ወንጀሎች አንጻር እንዲሁም ዘመኑ ከደረሰበት የወንጀል ሳይንስ ጋር የተጠጣመ በርካታ ድንጋጌዎች የተካተቱበት እና የአገራችንን የፍትህ ስርአት በማዘመን ሂደት ጉልህ አስተዋጽኦ ያለው የሕግ ማእቀፍ በመሆኑ ቋሚ ኮሚቴው ረቂቅ አዋጁን ከነማሻሻያዎቹ በሙሉ ድምጽ ተቀብሎታል።

ስለሆነም የተከበረው ምክር ቤት ረቂቅ አዋጁን ከነማሻሻያዎቹ እንዲያፀድቀው ይህንን ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ አቅርበናል።

የህግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ